የኮንያ አበቦች ክፍል ■①

✍ አይመኒ

(🍃ይምረኝ ይሆንን ያላነበባችሁ ቤተሰቦች፡ 2ቱ ታሪኮች ትሥሥር ስላላቸው ቀድማችሁ የሂልዋን ታሪክ ብታነቡ እላችኋለው መልካም ንባብ)

<<ሐሱዬ ዱንያን አሁንም ታምናታለህ እንዴ? እባክህን መሞኘትህን አቁም?!>> የምሰማው የሂልዋ ድምጽ በሀዘን ድሪቶ የሞቀ ነበር <<እባክህን ውዴ ተዋት>> ከፊት ለፊቴ ያለችው ጽጌሬዳ አበባ እጅጉን ታምራለች.....ቀነጠስኳት መዐዛዋ መንፈስን ያድሳል.....እሾኋ ግን ጣቶቼን ሸረካክቷቸው ነበር ።ከሀይቁ ጀርባ የሚሰማው የሂልዋ ጩኸት እየበረታ ሄደ።

ከእንቅልፌ የነቃሁት የተኛሁባት በደርቅ ሳር የታጨቀች የከብቶች ፉርሽካ ማመላለሻ ተንቀሳቃሽ ጋሪ ስታንጫግጨኝ ነበር።ፀሃዩኣ ከማለዳው ማቃጠሏን ይዛለች። <<ሐሰን ተነሳህ እንዴ እስከ እርሻ ቦታው እንደተኛህ እየንተትኩ ልወስድህ ነበርኮ>> አባህ ኡመር ናቸው።ላያቸው ዘመን ያለፋቸው ሸማግሌ ይመስላሉ ዋ ጥንካሬአቸው...

ከዘመን በአንዱ <<ሀሰን ጃን ተነስ ቁርስ ብላልኝ>> የሚለውን የኡሚን መረዋ ድምጽ እሰማ ነበር....ድሮ የካይት ውድድር በሚያሳስበኝ የልጅነት ግዜዬ።

የኢራንን ምድር ለቅቄ የወጣሁት በደመነፍስ እንጂ እራሴን እየመራሁ አልመስልህ አለኝ። እልህ አስጨራሽ የባቡር ጉዞዎች....ረሃብ ጥማት ፡ የሐይቅ ላይ ታንኳ....ብርድ እና ቸነፈር።ቱርክ!

ወደ ቱርክ ከገባሁ አመት አልፎ በቀጣዩ የማይታወቅ ዘመን ሊደረብ ነው። በዚህ ማለቂያ በሌለው የእርሻ ሥፍራ ላይ ቀሪዋን ህይወቴን ከአዝመራዎች ጋር ሸው ሥል ከፍሬው አድጌ ከቅጠሉ ልረግፍ ወስኛለሁ። ማለዳውን በባዶ ልብ እነቃለሁ ሰዎች <<አልሐምዱሊላህ>> ብለው ፈጣሪያቸውን ሲያመሰግኑ እገረማለሁ፡ ምናልባት እኔ ባመሰግን ቃሌ ሰማይ ቤት ስትደርስ አሸሙር ተብላ ትያዝብኛለች ለዚያም ይሆናል ዝምታዬን የታጠቅሁት ።ምሸቱን ከጭለማው ጋር ስፎክር አድራለሁ <<ዋልህ
አንተ ጽልመት ነኝ ባይ የልቤን ጥቁር አሻራ አሳይህና እኔ የጠዋት ንጋት ነኝ አስብልሃለው>>።

አብዛኛዎቹን ቀናቶች እህል በመሰብሰብ፡በመከመር፡ በትላልቅ ማዳበሪያዎች ውስጥ በመጠቅጠቅ እና እህሎቹን አልጋዋ ጋሪዬ ላይ በመጫን አሳልፋለሁ።ያለሁበትን ቦታ ስም ግን እስካሁን በቅጡ አላወቅሁትም።

<<ዛሬ ብዙም ሥራ የለብንም ልጄ ጥቂት የምንተክላቸው የማንሳ ችግኞች አሉ እነሱን ጨርሰን እዛው ከአውድማው ላይ እያወጋን እንውላለን>> አባህ ኡመር ናቸው። በህይወት ያሉ አባት። <<እሺ አባህ እሺ>> አልኳቸው በጋሪዋ ላይ እንደተኛው እሳቸው ከፊት ሆነው እየንተቱኝ። ወደ እርሻው ቦታ እንደደረስን ዶማ ጨብጠው በላብ ተጠምቀው የሚቆፍሩትን ሰራተኞች ሰላም እያልን የሰፊው እርሻ ቦታ አካል ሆንን።ብዙ የሚባሉ የማንሳ ተክሎችን ለሰዐታታ ያህል ስንተክል ከቆየን በኋላ <<እንረፍ ቢቃ ልጄ ሐሰን ነገ እንጨርሰዋለን>> አሉኝ የግንባራቸውን ላብ እያንጣፈፉ <<ሁፍፍ እሺ አባህ ሳላስበው ደከመኝ እኮ>> አልኳቸው።ፈገግታቸው ፍፁም አባታዊ ነው።

አቧራማውን የጋሪውን ጎን ተደግፈን የያዝናቸውን ቂጣዎች በቀረችን ወተት ማጣጣም ጀመርን፡ከቱርክ ትኩስ የኤደን አየር ጋር። የመጀመሪያዬ ጉርሻ ላይ አባህ ኡመር ጉሮሮኣቸውን ጠራርገው ወሬ ጀመሩ <<ልጄ ግን እስከዛሬኮ ታሪክህን ነግረኸኝ አታውቅም እስኪ ዛሬን ትንሽ አጫውተኝ>> ።ጥያቄያቸው ትን አስባለኝ <<ኡኹ ኡኹ ታሪክ? >> እኩያዬን የማወራ ነው የምመስለው << ታሪክ ከመሃል ሲሰማ ጥሩ አይመስለኝም አባህ ኡመር>> በእርሻዎቹ መሃል በተዘረጋው የአፈር መንገድ አቧራው ሲነሳ ከሩቁ ይታያል <<ታሪክ የሚያምረው ካለቀ በኋላ ሲተረክ ነው ማለትም በመቃብር ድንጋይ ላይ ተለብጦ ከሞት በኋላ>> ።አባህ ኡመር አተኩረው እያዩኝ እንደሆነ ጥላቸው ያሳብቃል <<ልጄ ንግግሮችህ አይደለም ለብላቴናው አንተ ለእድሜ ጠገቡ እኔም ይከብዳሉ>>
<<አባህ እሺ ምን ልንገራችሁ ጠይቁኝ እመልሳለሁ>> በቆሪጥ ሳያቸው ፈገግ አሉ።
<<ደግ ደግ ከየት ነው የመጣኸው ሀሰን?>>።

ሲፈን የምትባል መንደር ነበረች አይደል? ያ የቱሊፕ ዛፍ ፡የበረዶ ሜዳዎች ፡ ካይት አብራሪ ህፃናት
<< ምነው ዝም አልክ ሀሰኔ?>> አሉኝ ድምፀታቸው እየተለወጠ <<አስጨነኩህ እንዴ?>>
<<ኸረ በፍፁም አባህ እ እ ከኢራን ነው የመጣውት ኩቴህራን ከተማ>>

<<ኢራን ኢራን ባለቅኔዋ? ምነው ልጇ ሩቅ ሀገር ጠራህሳ>> ያመኑኝ አልመሰለኝም <<የምርህን ነው አይደል>> አሉኝ በአግራሞት እየጎነተሉኝ
<<አዎ አባህ አዎ>>
<<ጥራት ይገባህ ጌታዬ ! አንተ ሊጋ ቀንበጥ ምን እዚህ እግር ጣለህ ታዲያ?>> አፋቸውን እየሸፈኑ ያስላሉ <<ቤተሰብ የለህም?>>
እስከመቼ ይሆን ይህንን ቃል በሰማሁ ቁጥር የልብ ምቴ ግልብያዋን ምታደራው?። ምን ልበላቸው ይሆን? ውብ እናት ነበረችኝ ለይላ የተባለች አይኗ ሀዘል አረንጓዴ ጉንጮቿ ጦረኛ ፀጉሯ በተፈጥሮ ጥቁር ሂና የደመቀ ደግሞም የፍቅር ንግስት የናፍቆት ጎተራ። አባትም ነበረኝ ውይ እሱማ! መብረቅ እሱማ ብልጭታ ተጠብቆ የሚቀር የቢጋ ዝናብ። እህቴ...
<< ቤተሰብ ነበረኝ አባህ ግን ....>> ከአቧራማው መንገድ የሚመጡ የፈረስ ኮቴዎች ከመልሴ አሰናከሉኝ ። ቦርካካ አመዳም ሱሪ በቦቲ ጫማ ያደረገ ባለሰፊ የቴከሳስ ኮፊታ ሰውዬ ከቡኒው ፈረስ ላይ ወረደ።አይኖቹን በኔ ላይ እንደተከለ ከሩቁ ያስታውቃል።
አባህ ኡመር ድንጋጤ በተቀባ ድምጽ እየተነፈሱ <<ይሄ አረመኔ በድጋሚ መጣ>> ብለው ለራሳቸው አወሩ።

ትምባሆውን እየለኮሰ ነበር።አይኖቹ አሁንም እኔ ላይ ናቸው <<ጋሽ ኡመር ማነው ደሞ ይሄ አይነግቡ ብላቴና ቀልጣፋ ይመስላል ባክህ>>
አባህ ኡመርን አየኋቸው። በስስት አይን አይኔን እያዩ << እኔም በወጉ ያላወቅሁት ልጅ ነው ወዳጇ እህሎችህን ደግሞ...>> አላስጨረሳቸው።
<< እቸኩላለሁ እቸኩላለሁ ሰማህ ኡመር እኔ ወደዚህ እርሻ ጎራ ብዬ ባዶ እጇን ስመለስ አይተከኝ አታውቅም መቼስ>> የትምባሆው ጢስ ከአፉ ስር ይንቦለቦላል ፡አተኩሮ ላየው ስጋ በል ይመስል ነበር። << ለዛሬ አዝመራዎችህን አቅፈሃቸው ተኛ መልከመልካሙን ጉብልህ እኔ አሳድርልሃለው>>
ጮክ ብሎ ተጣራ ....ማነህ ሚዛር ናና ልጃችንን አቅፈህ ከሰረገላው አስገባው..... የአባህ ኡመር አይን እንባ ስታቀር አይቼአት አላውቅም ነበር፡ይህን ጠንካራ አባት ተላምጇው ነበር፡ልክ እንደምጋደምባት ጋሪ። <<እባክህን ሺምር እሱ እርሻው ላይ የሚያግዘኝ ቀኝ ክንዴ ነው የፈለግከውን ያህል የእህል ክምር አስጭነህ ንዳ እባክህን እሱን አትውሰድብኝ ተለመን>>..... የእርሻው መንደር አባቴ።

ቱርክ ከሰፋፊ አውድማዎች ላይ

ቀ

ቀ ክፍል ሁለት ይቀጥላል

የኮንያ አበቦች ክፍል 2

አይመኒ

አንተ ሰው ከደቂቃዎች በኋላ የሆነውን ትዕይንተ ዐለም ሳታውቅ ለምን ነገ ትላለህ? ለምን?

ጮክ ብሎ ተጣራ ....ማነህ ሚዛር ናና ልጃችንን አቅፈህ ከሰረገላው አስገባው..... የአባህ ኡመር አይን እንባ ስታቀር አይቼአት አላውቅም ነበር <<እባክህ እሱ እርሻው ላይ የሚያግዘኝ ቀኝ ክንዴ ነው የፈለግከውን ያህል የእህል ክምር አስጭነህ ንዳ እባክህ ተለመን>>
<<ይሄን የመሰለ ልጅማ እዚህ ከሸማግሌዎች ጋር አይጃጃልም ባይሆን ቅልጥፍናውን አይተን ወፋፍራም ረብጣዎችን እናስልክልሃለን ሰላም ሁን ወዳጇ>> ሁለተኛው ሰው እጇን አጥብቆ ይዞ እየጎተተ ነበር ወደ ሰረገላው ያስገባኝ።በሰረገላው መስኮት በኩል ጋሪዬን ተደግፈው የተቀመጡት ሽማግሌ የስንብት እጃቸውን አነሱልኝ...እኔም። ..አይኔን አዘቀዘቅሁ።

ለደቂቃዎች ከነፍን።ያልተረዳሁትን ዐረብኛ የተቀላቀለበት ቋንቋ እየወሸከቱ ከቆዩ በኋላ ባለኮፊታው ሰው <<ተጫወት እንጂ >> የሚመስሉ ምቶችን ጀርባዬ ላይ አሳረፈብኝ።
<< እ ሷሂብ ወዴት ነው ግን የምንሄደው>> አልኩት ኩምትር ብዬ እንዳለሁ። ሁለቱ ሰዎች ከተያዩ በኋላ <<ኮንያ>> አሉኝ በአንድ አፍ።
<<ብዙም አትጓጓ ደርሰናል ትምህርት ቤትህን ታየዋለህ>>

ከተኮማተርኩበት ፈታ እያልኩ ቀጥ ብዬ እንደመቀመጥ አልኩ <<ትምህርት ቤት ? እውነታችሁን ነው>> ለምን ጉጉት እንዳደረብኝ አላውቅም
<< እንዴታ! አጃግሬ ወንድ ሆነህ የምትወጣበት ቤት ነው የምንወስድህ።የጥበብ ቤት በለው እንደውም>> ብለው እየተያዩ ማሽካካት ጀመሩ።

መልሶቻቸው ሥርዐት የላቸውም።ምናልባት ሁሉም የቱርክ ሰዎች እንደዚህ ይሁኑ? ግልቢያዬስ የት ያደርሰኝ ይሆን ...በመስኮቱ በኩል የፈጣሪ የእጅ ሥራዎች ነምርተው ይታያሉ።እያሻቀብነው ባለው መንገድ ዳር እና ዳር ደመና ሰንጣቂ ረዣዥም ዛፎች ይወዛወዛሉ።ከኋላቸው የሚሰማው የፏፏቴ ድምጽ በዋናተኛ ዳክዬዎች ታጅቦ የተፈጥሮን ውብ ዳንኪራ ይሞዝቃል። እንጨት ተሸክመው ቁልቁለቱን የሚወርዱ እናቶች አንድ በአንድ ያዘግማሉ። << ደርሰናል ደርሰናል>> ግንድ የሚያክለውን ትንባሆውን በግራ እጁ እንደያዘ ከሰረገላው ይዞኝ ወረደ።

በተራራዎች መሃል የቆምኩ ቡችላ የሆንኩ መሰለኝ።ባለሁበት ዙሪያዬን አማተርኩ ቦታው በተገነዳደሱ ዛፎች በእህል ክምሮች የተሞላ ነበር።ከረጃጅም የእንጨት አጥሮች ፊት ለፊት ከአንዲት በር አጠገብ ቆመናል። በሩ ተከፍቶልን ወደ ውስጥ ዘለቅን።በቀይ ለስላሳ ጣውላዎች የተገነባ አናቱ ላይ ጢስ ማውጫ ያለው መኖሪአ ቤት ኢልቡርዚን መስሎ ቆሟል። <<ትምህርት ቤቱ ይሄ ይሆን?>> አልኩኝ በውስጤ።
<< ወደ ክፍሉ ይግባ በቃ>> ብሎ እጄን ይዞ ከጣውላ ቤቱ ፊትለፊት በኩል ወዳለ የደከረተ ጎጆ እያመናጨቀው ወሰደኝ።

ኳ ኳ ኳ የከፈተን ግዙፍ ሰው ወደ እኔ አያየ << እዚ የሚገባ ነው አለቃዬ? >> አለ።ወደ ውስጥ ገፈተረኝ <<ሰማህ የትም እንዳይወጣ። ባይሆን ከውስጥ ቆልፍበት እራስህም ላይ ጭምር>>።

ወደ ውስጥ በሚሰረጉድ ሸካራ ምንጣፍ ላይ በጉልበቴ ተደፋሁ።ክፍሉ በጫጫታ የተሞላ ነው።በጭላንጭል ብርሃን የሚታዩ ብዝሃ ፍጥረቶች ክፍሉ ሥር ተሰግስገዋል። መሃል ላይ በቆመው የእንጨት ምሶሶ ላይ 2ፋኖሶች ተንጠልጥለው ከስራቸው እንጨቱን በዙሪያ የታከኩ ሰፋ ያሉ የእንጨት ጠረጴዛዎች ይታያሉ። <<ተነስ ካሁኑ ቦታህን ብትይዝ ይሻልሃል>> አለኝ ግዙፉ በርች ከፋች።በክብ ቅርጽ የተቀለሰቺን ጎጆ አማትሬ አየኋት።በስተግራ ያሉት ሰዎች ጥቋቁር እና አነስ ያለች ክብ ሰርተው የጡንቻ ውድድር የሚያደርጉ ነበሩ። <<ፍጠን ፍጠን ፋኖሷ ከጠፋች እዚው ማደርህ ነው>>።
አይኔን ወደቀኝ ግድም አዞርኩ።ተረጋግተው የተቀመጡ ወጣቶች ይበዛሉ።አንደኛው ወጣት ወደ እኔ ሲመለከት አይን ለአይን ተጋጨን።ጎንበስ አልኩኝ. ..እንደገና ቀና ስል <<ና እዚህ ጋር>> ብሎ በአይኑ አመላከተኝ።መሬት መሬቱን እያየሁ ጥቁሩ ወጣት ጋር ደረስሁ። ሲያነብ የነበረውን ኪታብ በቀስታ ዘግቶ አጠገቡ እንድቀመጥ ተጠጋጋልኝ። <<ተዐል ኢቅኡድ መኢየ ሁና>> ጥርት ያለ ዐረብኛ ነበር የሚያወራው <<ና ከኔ ጋር እዚህ ተቀመጥ>>።

ከተቀመጥኩ በኋላ በቆሪጥ ወደ ጎን ለማየት ሞከርሁ። ትከሻው ከፍ ያለ እና ሰፊ ስለነበር አንጋጥጬ ነበር እይታ የምሰርቀው።አንድ ጎርናና ድምጽ <<ጸጥታ ጸጥታ >> ሲል ደብዛዛው ክፍል ላይ ዝምታ ነገሰ።<<ዛሬ አንድ አዲስ ወዳጃችን ተቀላቅሎናል >> ስለኔ እያወራ መሆኑን ሳውቅ ከፍ ተደርጎ ከተሰቀለው የእንጨት መስኮት አይኔን ነቅዬ ወደ እኔ የሚመጣውን ግዙፍ ሰው ማየት ጀመርኩ።
🌹

🌹ክፍል 3 ይቀጥላል..

★彡🌹የኮንያ አበቦች ክፍል ③

✍አይመኒ

ህይወት አንፃራዊ ናት።ምናልባት የኮንያ ባላቅኔ የኢራን ተረት ነጋሪ ሊሆንም ይችላል።

ግዙፉ ሰው አጠገቤ መጥቶ ቆሟል።እጁን እንድይዘው ሲዘረጋልኝ ፍርሃት ፍርሃት አለኝ።ከተሸንጥኩባት ቦታዬ ባያነሳኝ ብዬ እየተመኘሁ ጥቁሩን ባለሰፊ ትከሻ ሰው አይን አይኑን አየሁት። <<ሷሂብ አሏህ ካለ ነገ እራሱን ያስተዋውቃል አሁን ፊርቷል መሰለኝ >> ጎርናና እና በእርጋታ የተሞላ ድምጽ። ግዙፉ ሰው ጥቁት አዘቅዝቆ ካየኝ በኋላ << ያ ቢላል እሺ ነገ ግን ምንም አይነት ምክንያት አልቀበልም>> ብሎ ወደ ጎጆው መሃል ተመለሰ።አጠገቤ ያለው ጥቁር ፈገግተኛ ሰው ቢላል እንደሚባል አወቅሁ።

ደክሞኝ ስለነበር ከፍሉ ውስጥ የተካሄደውን በቅጡ አላስታውሰውም።በጀርባ ለመጣጣል የሚላፉ ወጣቶች...የሚያንኮራፉ ፍጥረታት.....በዝግታ ቁርዐን የሚያነብ ጎርናና ድምጽ፡ቢላል።

ጠዋቱን የነቃሁት በጋሪዬ ላይ ተጋድሜ አልነበረም። <<ቶሎ ቶሎ በልታችሁ ወደ ሥራ!>> ይላል አንድ ድምጽ።አይኔን እያሻሸው ወደ ጎን ሳይ ቢላል እያነበበ ነበር።<<ተነሳህ እንዴ ና ቁርስ እንብላ>> አለኝ ልክ እንደትናንቱ በፈገግታ እያየኝ። የት ነው ያለሁት? በአንዲት ደሳሳ ጎጆ ስር የታጎርኩት ከነማን ጋር ነው? ለምንስ ወደዚህ አመጡኝ? ።ግራ በተገባ አኳኋን ምንም ስላመልስ ተነስቼ ቁጭ አልኩ። <<አይዞህ እሺ ትለምደዋለህ>> አለኝ ቢላል።

<<ስምህ ግን ማነው>> አለኝ ከምሶሶው ጋር በተከረቸመው ጠረጴዛ ትይዩ የእንጨት ዱካ ላይ እየተቀመጠ። << ሐሰን >> አልኩት የስሜ ትርጉም ከማንኑቴ ስላልተጣጠመ እየተሸማቀቅሁ። <<አ ማሻ አሏህ ምን ያማረ ስያሜ።የረሱላችን የልጅ ልጅ ስም ነበር የአሏህ ሰላም በእርሳቸው እና በቤተሰቦቻቸው ላይ ይስፈንና>>።

❦

የቀረበውን ደረቅ የገብስ ቂጣ ከሻሂ ጋር በዝምታ መብላት እንደጀመርን የኡሚ ትኩስ ነአን እና የሩማን ጭማቂ መዓዛ ከአፍንጫዬ ስር ከትውስታ ንፋስ ጋር ተላወሱ ።<< ሐሱዬ ቁርስህን በደንብ ብላልኝና ወደ በረዶው ሜዳ ሂድ ልጆቹ እየጠበቁህ ነው>> ኡሚ።እማ አንቺም ጣፋጩ ማዕድሽም ከልቤ አዘቅት ስትወረወሩ ንፍቅ ትሉኛላቹ እማዬ።

ቢላል እየሰረቀ ያየኝ እንደነበር ይታወቀኛል። በልተን ከጨረስ በኋላ የበላንበትን ሳህን ከትልቅ የሳህን ክምር ላይ አስቀምጠን በተበረገደው በር በኩል ወጣን።ከጣውላው ቤት ደረጃ ፈቀቅ ብሎ ወደ ጎጆው ማጎሪያ ያመጣኝ ትምባሆ የያዘው ሰው በእጆቹ ጠራኝ።ቢላል ሰውየውን ሲያይ <<ማታ እንገናኝ በቃ አሏህ ይጠብቅህ>> ብሎኝ ከአጠገቤ ተሰወረ።

በጎጆዋ ሥር የታጎሩት ወጣቶች የጉልበት ሰራተኞች እንደሆኑ ተረዳሁ።በለስላሳ የጣውላ ቤት ውስጥ የሚኖሩት ደግሞ የመንደሩ ባለአባት ሻህ ሱፍያን።ወጣቶቹ ያለምንም ክፍያ የእርሻ ቦታውን ይንከባከባሉ።በትላልቅ በርሜሎች በአህያ ላይ ውሃ ያመላልሳሉ።እንጨቶችን ይፈልጣሉ. ...ብዙ ብዙ።

ባለትምባሆው ወደ ጣውላው ቤት ሳሎን ነበር የወሰደኝ።ትምባሆውን የእንጨት ድጋፍ ላይ አስቀምጦ ወደ ውስጥ ገባን።በግዙፍ ኩርሲይ ላይ የተቀመጡ ወፍራም ካባ የደረቡ ጠና ያሉ ሰው አፈጠጡብን።ከጎናቸው ፊቷን በጥቁር ሂጃብ የተሸፈነች እመቤት ተዘናፍላለች። <<ይሄን ብላቴና ደግሞ ከየት አመጣከው አንተ ሺምር>> አለ የንጉስኛ አወራር የሚያወራው ከበርቴ።
<< ከጋሽ ኡመር የእርሻ ቦታ ላይ ነው ያነሳሁት ጌታዬ>> ።
በጎናቸው ከተቀመጠችው እመቤት ጋር ጥቂት አንሾካሽከው <<እስኪ ወደዚህ አቅርበው በደንብ እንየዋ>> አሉ።እመበቲቱ ግርማቸው ከፋርስ እናቶች አይተናነስም << ያ አሏህ ምን ያማረ ልጅ ነው>> ብለው አፈጠጡብን።

<<ሺምር ላሁን መውጣት ትችላለህ>> ብለው ከእርሻው ላይ የነጠቀኝን ሰው ካሰናበቱት በኋላ በሹመኛ አይኖች እያዩኝ <<ስምህ ማነው ልጄ>> አሉኝ።
<<ሐ ሐሰን ኢብን ዐሊይ>>
<<አትፍራ ካሁን በኋላ የእኔ ጥብቅ አገልጋይ እና የእመት አሚናህ የአይን ማረፍያ ትሆናለክ>> አለቃው ነበሩ።
<<እ እሺ>> በደመነፍስ መልስኩ።
ወደ ጆሮዬ ተጠግተው አንዳች ቃል አንሾካሾኩ <<ዋናው ነገር አገልጋይ እንደሆንክ አለመርሳትህ ነው የኔ ልጅ>>።

ከየት እንደመጣሁ ጠየቁኝ ነገርኳቸው።በአግራሞት ተያይተው <ደምግባትህም ፋርሲነትህን ይናገራል> አሉኝ። ወይን ስቀዳላቸው የበሉበትን ሳህን ሳነሳ፡እጃቸውን ሳስታጥብ እስከ አመሻሹ ቆየሁ።

<< በቃ ወደ ማደሪያህ ተመለስ>> አሉኝ በበሩ በኩል አሻግረው የምትጠልቀዋን ጀምበር እያዩ። << ማለዳውን እርሻው ላይ እስከ እኩለ ቀን ከሰራህ በኋላ ወደዚህ ተመለስ>> እመቤት አሚናህ ነበሩ።

ደሳሳዋ ጎጆ ውስጥ ከገባሁ በኋላ ቀስ በቀስ ክፍሉ እንደትላንቱ ጢም ማለት ጀመረ።ቢላልም ትንሽ ቆይቶ መጣ። የፊቱን ውሃ እያንጣፈፈ << ተነስ መግሪብ እንስገድ>> ሲለኝ በአግራሞት እያየሁት <<ነገ እጀምራለሁ ለአሁን አንተ ስገድ>> አልኩት።ግራ ተጋብቷል <<እሺ ያ ሀሰን ቦታችን ጋር ሰው ከመጣ ተይዟል በልልኝ>> ብሎ ወደ ስግደት ገባ። ከፍ ባለው መስኮት በኩል ወና ጽልመት ይታያል...ጨረቃ የት ገባች...ሚዜ ኮከቦቿስ።
ያለሁባት የታመኩች ጎጆ እውነት መሆኗን ያረጋገጥኩት ዳግም በአቧራማ ምንጣፏ ላይ ስንጋለል ነበር።

ቱርክ የኮንያ ተራሮች ሥር

?

ክፍል ④ ይቀጥላል....⚞★

⚞★⚟የኮንያ አበቦች ④

ከፍ ባለው መስኮት በኩል ወና ጽልመት ይታያል...ጨረቃ የት ገባች...ሚዜ ኮከቦቿስ።ቢላል ሶላቱን እንደጨረሰ ከኪሱ ሥር ነጭ ያደፈ ተስቢህ መቁጠሪያ አውጥቶ ተመስጥአውን በረከ።ለደቂቃዎች አተኩሬ አየሁት ደክራታ እና የነተበ ልብስ ያደረገ ባለጥቁር ቆዳ ሰው ነው፡አይኖቹ ለቀይ የቀረቡ ደማቅ ቡኒ ሆነው የታጨቀ የስቃይ ነዶ ይታይ ይታይባቸዋል።ግን ደግሞ ፍፁም ረጋ ያለ ፈገግተኛ እና የአሏህ ቃል ከአፉ የማይለየው።

<<ቆየውብህ እንዴ አፉ በለኝ ባክህ>> ብሎኝ በትላንቷ ቦታችን ተቀመጠ።<<እና ውሎህ እንዴት ነበር ያ ሀሰን>> አለኝ የነተበውን ብርድ ልብስ እስከ ታፋው ድረስ እየለበሰ። የቀን ውሎዬን ነገርሁት።የሻህ(አለቃ) ሱፍያን አገልጋይ እንደሆንኩ ስነግረው እጅጉን ተደሰተ <<አየህ ሀሰን አሏህ በጣም ይወድሃል> > ነበር ያለኝ። ለምን እንደሆነ ስጠይቀው ፊቱን ከመቅጽበት ሲከሰክሰው ታወቀኝ ። <<እሺ ቢቃ ተወው ይቅር..>> አቋረጠኝ << አይ እነግርሃለው ምን መሰለህ ሐሰን እኛ በማለዳው ከዚህ ጎጆ ከወጣን በኋላ የሚገጥመን....>>
ትላንት የከፍሉን ጫጫታ ያበረደው ድምጽ በድጋሚ ተሰማ << ጸጥታ ጸጥታ ለዛሬ የተዘዋወረው የእንግዳው ትውውቅ አሁን ይጀምራል>>።
ቢላል ከገባበት ሃሳብ ሲነቃ አየሁት << ሀሰን እንዳትደነግጥ እሺ ዝምብለህ ቀባጥርላቸው>>።

የግዙፉ ሰው አይኖች ሳያፈጡብኝ በፊት ፈንጠር ብዬ ተነሳሁ። ወደ ጎጆው መሃል እንድጠጋ በእጆቹ ጠቆመኝ።
<< መጀመሪያ እራስህን አስተዋውቅ >> አለኝ አዘቅዝቆ እያየኝ
<< ሐሰን እባላለሁ>> የሁለቱ ፋኖሶች ብርሃን እየተስለመለመ ከፍሉ ላይ እንግዳ ስዕሎችን ይስላል መላልስ ያጠፋል።በየጥጉ የተኮለኮሉትን ሰዎች በደንብ ለማየት ያዳግታል።ተመኘሁ! ማን እንደሆንኩ በቅጡ የሚያስረዳልኝ ሰው ባገኝ ብዬ።
<< ከየት አካባቢ ነው የመጣከው ሀሰን?>> ።የተሰላቸ ላለመምሰል እየጣርኩ << ኢራን የፋርስን ምድር አቋርጬ ነው የመጣሁት>> አልኩት።ይህንን ከመናገሬ ከፍሉ በጉርምሩምታ ተሞላ ።ምናልባት የሩቅ እንግዳ ሆኜባቸው ይሆን? እይታዬ በቢላል አይኖች ላይ አረፈች << አብሽር አትፍራ>> የሚመስሉ ምልክቶችን በፊቱ አሳየኝ።

ግዙፉ የጎጆው ጉልቤ በድጋሚ ጠየቀኝ << ኢራን ኢራን የነሂዝቡሏህ ሀገር ምነው ወዳጄ ትንሽ ልጅ አይደለህ እንዴ ለምንስ ወላጆችህን ማሳዘን መረጥክ>>
የስላቅ ጦር አናቴን የሰነጠቀችው መሰለኝ ። ባባ ከዚህ ጠያፍ ጎጆ ሥር እጄን ይዞኝ ቢወጣ ብዬ ተመኘሁ።በቆምኩበት የሚሰረጉድ እድፋም ኬሻ ላይ የኡሚ እቅፍ ናፈቀኝ።...ኡሚዬ ጣፋጭ አንደበትሽ ወዴት ገባ? ሂልዋ የካይቱ ቀን አድነሸኝ አልነበር ዛሬስ....
<< ተናገር እንጂ ሐሰን ትተከን ኢራን ገባህኮ>>
በግዙፉ ሰው አሸሙር ሙሉ ባለጎጆ አሸካካ።ሳይታሰብ የቢላል ድምጽ ከጭንቀት ገላገለችኝ እንጂ << አሚር ሷሂብ ትንሽ ችግር ስላለበት ስለቤተሰብ አትጠይቀው እባክህን የሚፈልገውን አንድ ነገር ይናገርና ይቀመጥ>>። ቢላል እንዴት እንዲህ ሊናገር ቻለ ብዬ ተገረምሁ።
<<እሺ ሀሰን ምን ትችላለህ እስኪ እንደ ሀገራቹ ሺዐዎች ደረትህን ትደልቅልናለህ ወይስ ቀልድ ነገር ትነግረናለህ?>> ሙሉ ጎጆው በድጋሚ ሳቀብኝ። <<ቀልድ ይሻለኛል ደግሞ እኔ ሺዐ አይደለሁም>>።

ድሮ ድሮ ኡሚ ቀድማን በግዜ የተኛች ቀን ሂልዋ ጃን የሙላህ ነስሩዲንን ቀልዶች ትነግረን ነበር። ቀልዱን ጀመርኩላቸው
<< አንድ ቀን የሙላህ ነስሩዲን ሚስት ከወደ ሳሎኑ ጧ የሚል የወደቀ ነገር ድምጽ ሰምታ <ወይኔ ነስሩዲኔ እኔ ልሰበር> እያለች ወደ ሳሎኑ ፈጠነች።በሳሎኑ ላይ ነስሩዲንን ጃኬታቸውን እያራገፉ አገኘቻቸውና ግራ ተጋብታ ጠየቀቻቸው>> የጎጆው ፍጥረታት አፋቸውን ከፍተው እየሰሙኝ ይመስለኛል። << ነስሩዲን ጧ ያለ ነገር ሰምቼ ነው የመጣሁት ወደቅክ

እንዴ ውዴ' ስትላቸው <ሽረ በፍጹም አልወደቅሁም ጃኬቴ ወድቆብኝ ነው> ይሏታል ።ሚስታቸው በመገረም < ጃኬት ሲወድቅ እንደዚህ ይጮሃል እንዴ> ስትላቸው ጣሪያ ጣሪያውን እያዩ መለሱላት < ያው በሰዐቱ ጃኬቱ ውስጥ እኔም ነበርኩኛ>።

ከፍሉ በካካታ ተሞላ።ሂልዋኒ ቀልድ ካወራች በሁላ ቅንድቦቿን ከፍ እያረገች ፈገግ ትል ነበር። ውብ የብልህ ፊቷ ከፊቴ ውልብ ብሎ ተሰለበ። የጎጆዎቹ ሰዎች <<ሌላም ቀልድ ይነገረን ሌላም>> እያሉ ተንጫጩ ። .....አንድ ቀልድ ደግሜላቸው ወደ ቢላል በክብር ተሸኘሁ።

ከኢሻእ በኋላ ጎጆዋ ቀስ በቀስ እየሰከነች ስትመጣ የሚያንኮራፉ ትንፋሾች እምክ እምክ ከሚል ሽታ ጋር ተቀላቅለው ጆሮ እና አፍንጫ ያስይዛሉ።በቀኝ ጎኔ ጋደም ብዬ ቁጭ ብሎ ኪታብ የሚያነበው ቢላል ድምጽ ተሰማኝ << የቀልድ ልኳ ምግብ ውስጥ እንዳለ ጨው ነው>> ቀጠል አድርጎ <<ሐሰን ያንተ ቀልዶስች ግን ውበት አላቸው አስቀውኛልም ሌላም ትነግረኛለህ አይደል>> ኪታቡን ሲዘጋው ይታወቀኛል <<ለኔ ብቻ ማለቴ ነው>> ። <<መቀለድ ፈልጌ ሳይሆን ግድ ሆኖብኝ ብቻ ነው ያወራሁት>> አልኩት ሳላስበው አይኔ ላይ እንባ እያቀረረ። << ደግሞ አንተስ የምታነበው ኪታብ ምንድነው>>
እንባ ያነቀውን ድምፄ ሲሰማ ደንገጥ እያለ <<ምነው ምነው ሀሰኔ ሰላም አይደለህም እንዴ ቀን ላይ ያጋጠመህ ነገር ነበር ?> > አለኝ።

....ምን ልንገረው? እባክህን ባባን ከውቅያኖሱ ሥር ሰርገህ አውጣልኝ የምነግረው ብዙ አለኝ. .. ኡሚንም ከወደቀችበት ወለል ላይ ቀስቅስልኝ.....ካልቻልክ ደግሞ ወደ ሲፊን መንደር መልሰኝ እባክህን ቢላል! ከሚያስፈሩ የዝምታ ደቂቃዎች በኋላ ለቢላል መልስ ሰጠሁት <<
ምንም አልሆንኩም ቢላል በል ደህና እደር>>።

እህቺ ልብ እህቺ ልብ የትንግርት እና ብዝሃ ሚስጥሮች መቃብር ናት...

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

🌹

🌹

ክፍል ⑤ ይቀጥላል ⸗ ★

★ ⸗ 🌹የኮንያ አበቦች ክፍል ⑤

✍Ⓐ Ⓨ Ⓜ Ⓔ Ⓝ Ⓘ

<< ምንም አልሆንኩም ቢላል በል ደህና እደር>>።
ደክሞኝ ስልነበር ያደርኩት ስክን ባለ ጥቁር ዐለም ውስጥ ነበር።

ቀስ በቀስ የምስቅልቅሉ ጎጆ ቤት ማገር፣ የቢላል የጎን አጋር እየሆንኩ መጣሁ።ፀሃይ በምትበረታባቸው የኮንያ እርሻዎች ላይ ቢላልን ጨምሮ በርካታ ሰራተኞችን እያገዝሁ እስከ እኩለ ቀን ድረስ እሰነብትና ቢላል ለዙሁር ስግደት መተጣጠብ ሲጀምር እብስ እላለሁ።ወደ አለቃዬ ሻህ ሱፊያን እና እመት አሚናህ ክቡር የጣውላ ቤት።

ብዝሃ ቀናቶችን በሥራ እየደከምኩ አሳለፍኳቸው።ከዚያ ግን ድካሙንም ለመድኩት።የእህሉን አውድማ ሳጤን የሷሂብ ኡመር በሻሻ ፊት ድቅን እያለብኝ፣ የእመት አሚናህ ሩህሩህ አስተያየት ኡሚን ስቦ እያመጣብኝ በትዝታ እና በተስፋ ቢስ ብዘና ቆየሁ።

በአንዱ የጎጆ ሥር የምሽት ስብስባችን ላይ ነበር ቢላልን ስለ ቤተሰቦቼ በከፊሉ የነገርኩት።<< ደስ የሚል ቤተሰብ ነበረህ አንድ ቀን መመለስህ አይቀርም የስደት ምክንያትህንም እንደምትነግረኝ አልጠራጠርም>> አለኝ። የተሰጠንን ደረቅ የገብስ ዳቦ እየገመጥኩ <<ቢላል የኡሚ ነአን ዳቦ እንዴት ያለ ለስላሳ ነበር መሰለህ ቢስሚላህ ይሄኮ መንጋጋ ይሰብራል>> ስለው

ከሚያነበው ኪታብ ላይ አይኑን ሳይነቅል በፈገግታ መለስልኝ << ህይወት አንፃራዊ ናት ሐሰኔ በተሰጠህ አመስግን>>
ሲያወራ ቀድሞ ያሰበበት ይመስል ነበር <<ረሱላችን የአሏህ ሶላት እና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን ምን ይላሉ መሰለህ ሀሰኔ>>
ሲፈን መንደር እያለሁ ለአሏህ ቃል እና ሐዲስ ቦታ የምሰጥ ልጅ እንደነበርኩ አልረሳውም፡አሁን ግን ልክ ደጋግ መንፈሶቼን ከኡሚ ጋር አንድላይ ወለል ላይ ገድያቸው የመጣሁ ያህል ይሰማኛል።

ቢላል ቀጠለ<< ረሱል ያስተማሩን 'ቢሆን ኖሮ የሸይጧን ቃል እንደሆነች ነው> > አከል አድርጎ << ሱፊ የአሁን ልጅ ነው ትላንት ከደጋኑ ያመለጠች ቀስቱ ናት ነገ ደግሞ ምትሃትን ያዘለች ቅጧ ያልታወቀ ጠብታ አሊያም ባህር>>
<<ሱፊ ደሞ ምንድነው ቢላል>> አፈር አፈር በሚለው ውሃ ደረቁን ዳቦ እያወራረድኩ ነበር።
<<ሱፊ እንዲህ ነው አይባልም።ሱፊ ማለት እርሱ ዘንድ ወርቅ እና ድንጋይ እኩል ክብር የሚሰናፀፉበት፡ከአረንቋ ብርሌ የሀሴት መጠጥ የሚነነጭ የፈጣሪ ወዳጅ ነው>> ቢላል ስሜታዊ ሆኗል መሰል << የጥበብ የበኩር ልጅ ሱፊ>>።
<< ይቅርታ አርግልኝና ምንም የምታወራው ነገር አልገባኝም ቢላሌ>> ብዬው ለመኝታዬ ተመቻቸሁ። <<አታስብ>> አለኝ <<አታስብ በአንዷ እድለኛ ቀንህ ይገባሃል>>።

ሱፊ የሚለውን ቃል ከዚህ በፊት ሰምቸው እንደማውቅ እርግጠኛ ነኝ።ምናልባትም ከሂልዋ መፃህፍት በአንዱ ላይ አይቼው ይሆናል።የቢላል ንግግሮች እያቃጨሉብኝ ቆየሂ. ..የአረንቋ ብርሌ? ችግር የተሰገሰገበት የጭንቅ ልብ ማለት ይሆን?...

በግራ በኩል ያለው ሰው እራሱን ጥሎ ያንቀላፋል።በቀኜ በኩል በዝግታ ቁርዐን የሚያነብ ሰው ጆሮዬን ነጥቆኛል።ጎርናና ዝግ እና ረጋ ያለ ንባባ። ከጫጫታው ውስጥ ፍንትው ብሎ ይሰማኛል.ቢላል .....<<ምስጋና ለዐለማት ጌታ ይሁን ....አዛኝ እና ሩህሩህ ለሆነው ፈጣሪ....የምንዳዋ እለትም ነጋሴ!>>

ምንዳ? ድሮ የቁርዐን አስተማሪያችን ሰው የዘራውን የሚያጭድ ፍጡር እንደሆነ እያስጠነቀቁ ይነግሩ ነበር። እኔ ለመዝራት አልተፈጠርኩም ይሆናል! ስቃይ ሊዘራብኝ እንጂ።

ቢላል ሳላስበው ብዙ አናቅፆችን አንብቧል
<< ወደ አሏህም ሸሹ>>..... በደጋግ ዘመኖች የማሰላስልባትን የልጅነት አእምሮ ከአሁኔ ጋር ሳነጻጽረው ስለምንም ነገር ማሰብ አስጠላኝ ።ፊቴን አዙሬ በሚንጨላጨሉት ፋኖሶች ላይ አፈጠጥኩ።ብርሃኑን ከበው የሚንዛዙትን የእሳት እራቶች እያየሁ አይኖቼ ሲከደኑ ይታወቀኛል... ከእንቅልፍ መዳፍ ወደቅሁ።

ቱርክ የኮንያ ተራሮች ሥር

🌹

🌹 ክፍል ⑥ ይቀጥላል彡★

★彡🌹የኮንያ አበቦች ክፍል ⑥

✍ Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ

መርጃን!።እንቁ ከጸሊም ባህር ሥር በጠንካራ ሽፋን ተጠብቃ ትኖራለች። ብልጭልጭን እንቁ ለማግኘት የባህሩን ሞገድ ተጋፈጥ አሊያም ዳርቻው ላይ ቁጭ በል.....ኢማም አል ገዛሊይ

ከቢላል ቀድሜ ነበር የባነንኩት።<< ቢላል ቢላል ተነስ እንጂ ጀምበር ሳትቀድምህ>> ከፍ ባሉት መስኮቶች በኩል የሚገባው ንፋስ የነጆውን ንጋት በንጹህ አየር ያድሰዋል።
<<ወይኔ ፈጅር አመለጠችኝ እንዴ ሀሰኔ >> አይኖቹን እያሸ አሻግሮ ለማየት ሞከረና ቀሪ ወቅት እንዳለው ሲያውቅ እራሱን እንደእንጨት በከረደደው ትራስ ላይ አስደገፈ ። << አኡዙቢላህ ምናይነት ሚያስፈራ ህልም መሰለህ ያየሁት>>
<<ምን አየህ ተወው ባክህ ህይወት ትበቃኛለች በለው>>

<< አንተ ነህኮ ሀሰኔ ፅጌሬዳ. ..>> ፅጌሬዳ የሚለውን ቃል ስሰማ ትኩረቴ ጥንቸል እንደሰለለ የጅብ መንጋ ሲሰበሰብ ተሰማኝ << ፅጌሬዳ አጠገብ ቆመህ ነበር አንዲት ሴት <ሀሰን እባክህን አትንቀላት እንዳታሸታትም> ትልሃለች።
<<ከዚያስ ከዚያስ>> አልኩት ፋታ ሳልሰጠው
<<ጽጌሬዳዋን ቀጠፋካትና ፈገግ አልክ ግን ጥቁር ደም ከጣቶችህ ሥር ሲፈልቅ ነበር>>
ደነገጥሁ።ይህንን ህልም ወደዚህ ከመምጣቴ በፊት በጋሪዬ ላይ ፈልሰስ ብዬ አይቼው ነበር << እና ከ ከዛስ ምን ሆንኩ>>
<<ከዛ ግን የጣቶችህን ደም ስታይ በድንጋጤ ቆመህ አየከኝ እኔም ፈገግታ መለስኩልህ....ከዛ ሀሰኔ ከዛማ እንደ ወተት በነጣ የባህር ወለል ላይ ተስወኝጭፈህ ገባህ. ..ሰ>>
<<በቃህ በቃህ ቢላል>> የቅዠት ገጠመኞች እንደሆኑ እራሴን አሳመንኩ << ሱብሂህን ስገድ በቃ>> አልኩት መልሼ ጋደም እያልኩ።
<<እሺ ሀሰኔ ዛሬስ መስገድ አትጀምርም>>
<<ኢን ሻ አሏህ> > በቱርክ ምድር ላይ ለመጀመሪያ ግዜ ይህንን ቃል ተጠቀምኩ <<ማታ ተጣጥቤ እጀምራለሁ>>።
<<አልሀምዱሊላህ >> አለ ከኪሱ ሥር ወፍራሟን መፋቂያውን ሞጭለፍ እያደረገ....

ምሶሶውን ታክኮ በተሰራው ክብ ጠረጴዛ ላይ ቁርሳችንን ከበላን በኋላ ሳህናችንን ከክምሩ ላይ አስቀምጠን ወደ መውጪያው አመራን። << ደሞ ዛሬ ትንሽ ወገቤን አሞኛል ቢላል>> አልኩት ሂድ በቃ ዛሬ አትስራ የሚል መልስ በምላሹ እየጠበቅሁ። << በቃ ለሷሂብ አሚር እነግርልሃለው አይዞህ ዛሬን እረፍ> > አለኝ እንደተመኘሁት። <<እሺ ሹክረን>> ። << በል እንግዲህ መልከኛው አገልጋይ አሏህ ይጠብቅህ ሰላም አለይኩም>> ብሎኝ በፈገግታ ከእንጨቱ አጥሮች ኋላ በሩን ከፍቶ ተሰለበ።

ባለ③ቱን የጣውላ ደረጃ በአንዴ ፈንጠር ብዬ አልፌ ወደ ሻህ ሱፊያን ቤት ለመግባት ፍቃድ ጠየቅሁ።ፀሀዩአ ከኋላ የምታሳድደኝ ትመስላለች።ቱርክ ላይ የዘምሃሪ በረዶ የሚታወቅ አይመስለኝም።ከረምቱ ላይስ ህፃናት ካይቶቻቸውን ከሰማያዊው ሰማይ ላይ ያንሳፍፋ ይሆን? ለመሆኑ እዚህ መንደር ውስጥ ህፃናት ይገኛሉ?...<< ግባ እንጂ የፋርሱ ቀልጣፋ>> የሻህ ሱፍያን የሹም ቅላፄ ነበር ያነቃኝ። በሰፊው ቡተነጠፈው የዐረቢያን መጅሊስ ላይ አባወራው እና እማው ተንፈላሰው በአፋቸው ጢስ የሚወጣውን ቀጭን ጎማ ወትፈዋል፡ጢሱ መልካም መዓዛ ነበረው።ከንጉሳዊው ወንበር ሥር ውሽቅ ብዬ ተቀምጫለሁ። <<ሀሰን ና ከወይኑ አንሳ >> እመት አሚናህ ናቸው እናታዊ ትዕዛዛቸውን ጣል አድርገው ከኮስታራው ባለቤታቸው ሻህ ሱፍያን ጋር ወሬያቸውን የቀጠሉት።

ለሰዐታት የናፈቁኝን ጣፋጭ ሰማያዊ ወይኖች እያጣጣምኩ ካለሁበት ሳልነቃነቅ ቁጭ አልኩ። ዝቅ ተደርጎ በተሰራው ሰፊ መስኮት በኩል ውር ውር የሚሉ የጎጆው ፍጥረታት ከዋናው በር ይወጣሉ። ትንባሆ የማትለየው ባለቦቲው ጨካኝ ሰው ወጣቶቹን እየገፈታተረ አንዳች ነገር እያለ ያንቧርቅባቸዋል። ቀስ በቀስ ግቢው ጭር ሲል አስተዋልሁ። ትከሻው ላይ የታጨቀ ማዳበሪያ አንጠልጥሎ ከጎጆዋ ሥር የሚወጣ ሰው ይታያል፡የበላንባቸው ሳህኖች....

<< ከህ ከህ ያ ሐሰን እላይ ቤት ውጣና ካባዬን አምጣልኝ>> አስበርጋጊው የሻህ ሱፍያን ድምጽ ነበር። << ፊትለፊት ባለው ክፍል ውስጥ በጣውላ እጀታ ተሰቅሏል>>።
ደረጃውን ቀለል አድርጌ እየወጣሁ የጣውላውን ድጋፍ ልስላሴ ደባበስኩት።የኡሚ እጆች ከዚህ ይበልጥ ሲለሰልሱኝ ኖረዋል፡ከዘመን በአንዱ።ፊትለፊቴ ካለው ክፍል ሰፊ በር ጋር ተፋጠጥኩ። በከፊሉ የተከፈተውን በር ቀስ አድርጌ ከፍቼ ወደ ውስጥ ገባሁ። ከፊት ለፊት ከዘራ በሚመስል የተተከለ እንጨት ላይ ጥቁር ካባ ተሰቅሏል።እንደመንጠራራት እያልኩ ካወረድኩት በኋላ ወደ መጣሁበት ለመመለስ ዞር ስል.....
❦ በአበባ ቅርጾች በተሸሞነሞነው አልጋ ጥግ ላይ ተቀምጣ ነበር።የለበሰችው ቀይ ቀሚስ የአበቦቹ ንግስት አስመስሏታል። አንዲት ባለትላልቅ ቡኒ አይኖች ፍጥረት ከያዘችው መስታወት ቀና ብላ አየችኝ..... እኔም እይታዬን ከፈረሰኛ የልብ ምቶች ጋር መለስኩላት። አንዳች የተከረቸመ በር ገርበብ ሲል ታወቀኝ....ጥልቅ የልቤ ግዛት ላይ።

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

ክፍል ⑦ ይቀጥላል.....⸗★

★⸗❦የኮንያ አበቦች ክፍል ⑦

✍Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ

በአበባ ቅርጾች በተሸሞነሞነው አልጋ ጥግ ላይ ተቀምጣ ነበር።የለበሰችው ቀይ ቀሚስ የአበቦቹ ንግስት አስመስሏታል። አንዲት ባለትላልቅ ቡኒ አይኖች ፍጥረት ከያዘችው መስታወት ቀና ብላ አየችኝ..... እኔም እይታዬን ከፈረሰኛ የልብ ምቶች ጋር መለስኩላር። አንዳች የተከረቸመ በር ላይ ገርበብ ሲል ታወቀኝ....ጥልቅ የልቤ ግዛት ላይ።

አይን ለአይን እንደተጋጨን እኩል ወደታች አቀረቀርን።የሻህ ሱፍያንን ካባ ይዤ በችኮላ ከክፍሉ ወጣሁ። ደረጃውን በንፋስ ፍጥነት እየወረድኩ በአንድ እጄ የምትደልቀዋን ልቤን አረጋጋኋት።በክፍሉ ውስጥ ሰዐታትን አሳልፌ ሻህ ሱፍያንን ያስቆጣሁ ያህል ተሰማኝ።ግን ደግሞ ምክንያቱን በቅጡ ባላውቀውም.....ደስ ብሎኛል።

ሻህ(አለቃ) ሱፍያን ካባቸውን እየደረቡ << ያ ሐሰን ዛሬ የአደን ቀኔ ነው ሂድና ፈረሴ እንድትዘጋጅልኝ ንገራቸው>> አሉኝ።አደን? አልኩኝ በውስጤ በተረቶች ላይ ያንበብኳቸውን ለአደን የሚወጡ ንጉሶች በምዕናቤ ከሻህ ሱፍያን ጋር እያነጻጸርኳቸው።

በረጃጅም አጥሮች በተከበበው ግቢ ውስጥ የፈረሱን ልጓም ጨብጬ እንደቆምሁ በስተምስራቅ ቦግ ብላ የወጣችው ፀሃይ እጇን ከአናቴ በላይ እንዳኖር አድርጋኛለች።በለስላሳ ጣውላ ካሸበረቀው የላይኛው ክፍል መስኮት በኩል አንድ ሰው ቆሟል.... አይኖቿን ከርቀት ለማየት ሰገግ ስል አይታኝ ከመቅጽበት ከመስኮቱ ተሰለበች።ፈርሃን እና ሂልዋ አንድ ላይ ሆነው በድብቅ ፈገግታ ያዩኝ መሰለኝ።

ቀኑን ጥቅጥቅ ካለው ጫካ ሥር የሻህ ሱፍያንን የውሃ ቡሃቃ ይዤ እዚህ እዚያ ሥል አሳለፍኩት። ከፍየል የምትገዝፍ የተኳለች ሚዳቆ በጦር ወግተን ካደንን በኋላ ወደ ኮንያ ተራሮች ተመለስን። <<ሐሰን ለካ መልኬ በቃኝ ብቻ አይደለህም አስተዋይና ጀግናም ነህ>> የሻህ ሱፍያን ድምጽ ይርገበገብ ነበር <<ፋርሲዎች ድሮውንም የዋዛ አይደላችሁም>>።ዝም ያለ ፈገግታን መለስኩ።

የደሳሳው ጎጆ መግቢያ ላይ ቆሜ የቅድሟን ፍጥረት በመስኮቷ በኩል ለማየት ሞከርሁ። ቆይ ማን ናት? የሻህ ሱፍያን ልጅ ትሆን? ወይስ የእመት አሚናህ ሞግዚት።.....ምሽቱ ደብዛዛ ነበር ጨረቃ ከጣውላው ቤት አናት ላይ ተገድፋ ጭለማ የማይጋፋውን ብርሃኗን ትረጫለች።በሩ እንደተከፈተልኝ የወከባውን ጎጆ ዘለቅሁ።ቢላል ማረፍያ ቦታችን ላይ ስላልነበረ ብጣሽ ጨርቅ እስከ ወገቤ ድረስ ጥዬ ቁጭ እንዳልኩ የምሽት ጓዴን መጠባበቅ ያዝኩ።

ትንሽ እንደቆየሁ የደከመው የሚመስለው ቢላል ከውብ ፈገግታ ጋር ወደኔ ሲጠጋ አስተዋልኩት።<<ሰላም አለይኩም ሀሰኔ ሰግደህ መሆን አለበት የተደላደልከው>> አለኝ <<መቼስ ጠዋት ቃል የገባከውን አልረሳከውም አይደል>> ።ማታ መስገድ እጀምራለሁ ብዬው እንደነበር ረስቼአዋለሁ << ወአለይኩም ሰላም እ እ አልታጠብኩምኮ ገና>> አልኩት ከተቀመጥኩበት እየተነሳሁ።
<<እንካ እቺን ፎጣ ያዝ ከጎጆው ጀርባ በሚገኘው ሜዳ ላይ ታጠብ ውሃም እዛው ታገኛለህ>> ለስላሳ አረንጓዴ ፎጣ። <<ረሱላችን እና ባልደረባዎቻቸው ብዙሃኖቹ አረንጓዴ ሸማ ያዘወትሩ ነበር የጀነት ሰዎች ልብስም አረንጓዴ ናት>> አለኝ እንደለመደው ፈገግ እያለ። ቢላል የኮንያ ወንድሜ።

የቱርክ ምሽት እንደ ቀኗ አይሞቅም።ቀዝቃዛውን ውሃ ከአናቴ ላይ ቸለስኩት ....ያለመኖር ፍላጎት ከሰውነቴ ላይ ታጥቦ ሲወርድ....የህይወት አዝመራ በልቤ ጉዝጓዝ ላይ ሲያንሰራራ ታወቀኝ። <<በአበቦች መሃል ያየሃት እንስት እጅጉን ውብ ናት አይደል? >> አልኩት ለልቤ ከዚህ በፊት ተሰምቶኝ በማያውቀው እንግዳ ስሜት ግርር እያለኝ....።

አርጓዴዋን ፎጣ ጣል አድርጌ ከታፈነው ጎጆ በድጋሚ ዘለቅሁ። ቢላል ልክ እንዳየኝ ብድግ ብሎ ጥርሱን በረጅሟ ሲዋከ ማጽዳት ጀመረ። <<ኢቃም በል ሀሰኔ>> አለኝ መሬት መሬቱን እያየ.....<<አሏሁ አክበር አሏሁ አክበር>> ፐርሺያኛ ለዛዎቼ ሲሰሙ ከፍሉ ከመቅጽበት ዝምም ሲል ታወቀኝ።

.... ክፍል ⑧ ይቀጥላል彡★

★彡የኮንያ አበቦች ክፍል ⑧

✍Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ

<<ኢቃም በል ሀሰኔ>> አለኝ መሬት መሬቱን እያየ.....<<አሏሁ አክበር አሏሁ አክበር>> ፕርሺያኛ ለዛዎቼ ሲሰሙ ክፍሉ ከመቅጽበት ዝምም ሲል ታወቀኝ።

ሰግደን እንደጨረስን ግዙፉ ሷሂብ አሚር ወደ እኛ እየተጠጋ << ማሻ አሏህ ቅላፄህ ከአምልኮ አሻግሮ ትዝታን ያጠምዳል>> ብሎ ወሬውን ቀጠለ <<እባክህ እስኪ የምትፈልገውን አንድ እንጉርጉሮ ልቀቅብን የጎጆው ሁካታ ሁሉንም አሰልችቷል>>።ከቢላል ጋር ከተያየን በኋላ በአዎንታ ጭንቅላቴን ነቀነቅሁ። ወደ ቢላል ጠጋ ብዬ አንሾካሽኩሁለት << እውነትህን ነው አሏህ ይወደኛል >>።

እመሀል ጎጆው ላይ ከፋኖሶቹ ተጠግቼ በኡሚ የጥንት ሸክላዎች ላይ የማውቀውን መስመር አሃዱ ብዬ ጀመርኩላቸው። ያ መን ገፈለትከ ዱንያ ላ ተቅለቅ.....ጭንቅ አይግባህ አንተ ዱንያ ችላ ያለችህ.....አለም ድሮውም ከብ ናት ና ልንገርህ....በደጅህ ማለፏ አይቀርም ስትዞርብህ.....አትጨነቅ ዞራ ልታልፍብህ።

ብዝሃ የፈገግታ ፊቶች እና ተስፋ የቆረጡ እይታዎች ምሶሶውን ስዞር አብረው ተከተሉኝ።ከቢላል ጋር እያወራን ነበር እንቅልፍ ያሸነፈችኝ።
<<ሀሰኔ ዛሬ ደስ ብሎሃል አይደል> >
<<አዎ ምነው ችግር አለው>>
<<ኸረ በጭራሽ ተደሰት >> ፈጠን ብሎ ነበር የመለሰልኝ << ተደሰት ድፍን ዐለም ያንተ የሆነች ያክል ግና ፈጣሪህን ይዘክ>>።
<<ገለጻው ደስ ሲል ቢላሌ>>
<<ይህንን አባባል አታውቀውም እንዴ የናንተው ሀገር ባለቅኔ ነውኮ ያወራው>>
<<ማነው እሱ ባክህ>>

<<ጀላሉዲን አል ሩሚ ነዋ>>ሲለኝ አይኖቼ ተበለጠጡ። <<ማን ማን ሩሚ ነው ያልከኝ ሩሚ የመስነቪ ባለቤት?>> አልኩት አይን አይኖቹን እያየሁ።
<<አዎ ሐሰኔ ምነው የደነገጥክ ትመስላለህ >>
<<ምንም እህቴ ሂልዋ በጣም ትወደው ነበር >>ድምፄ ሲከስም ታወቀኝ።

ያን ምሽት የሩሚ ቀብር እና የክብር ሐውልት ቱርክ ውስጥ እንደሚገኝ ሲነግረኝ ሂልዋ ቱርክ የገባች ያህል ፈነጠዝኩ።የቆመው እዛው ኮንያ ውስጥ እንደሆነ እና የሩሚ ሃዋርያዎችም መገኛ እራሷ ተራራማዋ ኮንያ እንደሆነችም አወቅሁ።ከመተኛታችን በፊት ደገምኩለት <<አሏህ ይወደኛል ሐሰኔ>> ።ስለ ውቧ የላይኛው ቤት እንስት ምንም ትንፍሽ አላልኩለትም።

❦

ቀናቶች ነጎዱ።የአደን ካባውን እንዳመጣ ለሳምንት ያህል አልታዘዝኩም ነበር።<<ሂድ እስኪ ካባዬን አምጣልኝ>> የሚል ድምጽ ናፈቀኝ። አልጋው ላይ በአበቦች ተከባ የተቀመጠችውን ፍጥረት በድጋሚ ባያት ብዬ ተመኘሁ።

በአንደኛው የሳምንቱ መውጪያ ማለዳ ላይ ነበር ካባውን እንዳመጣ ታዝዤ ወደ ክፍሉ የዘለቅሁት። በአልጋው ላይ ትራሶች እና አንሶላ እንጂ ውብ እንስት አትታይም።ወጥቼ በድጋሚ መግባት ፈለግሁ።ለደቂቃዎች የአልጋው ላይ አበቦች ላይ አፍጥጬ ቆምኩ።አበባዎቹ የት እንደሆኑች እንደማይነግሩኝ ሳውቅ ክፍሉን ለቅቄ ወጣሁ። የደረጃውን ድጋፍ በጥፍሮቼ እየቧጠጥኩ በዝግታ እየወረድኩ ሳለ የሻህ ሱፍያን ካባ ትዝዝ አለችኝ።ፊቴን እንደገና አዙሬ ወደ ክፍሉ ተመለስኩ።ከታችኛው ክፍል አንድ ድምጽ ይሰማል <<ያ ቨለድ (ልጅ) ምነው ዘገየህ!>>

ካባውን በፍጥነት አንስቼ ወደ በሩ ተቻኮልኩ።በሩ ቀድሞኝ ተከፈተ ...ትላልቅ ቡኒ አይኖች አየት አድርገውኝ ወደ መሬት ሲመለሱ ነበር። << ሰ ሰ ሰላም>> አልኳት በደመነፍስ <<ሰላም> > አለችኝ እንደዋሸንት አየር በለሰለሰ ዜማ. ...ካባውን እንደያዝኩ በቆመችበት አልፈ,ያት ሄድኩ ።ትንሽ እንደተራመድኩ ያለምክንያት ወደ ኋላ ዞር አልኩ። እሷም ወደ እኔ ዞራ ነበር ...በሩን ስትዘጋው በመጨረሻዎቹ ክርቸማዎች ላይ ፈገግታዋን ሰረቅኳት....ኮንያ ኮንያም ትስቃለች : አዝመራዎቿ ይቦርቃሉ :የተኳሉ ሚዳቆዎች ይፈነጥዛሉ: ይህንን ፈገግታ ቢያዩ።

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

🌹

🌹 ክፍል ⑨ ይቀጥላል.....ኽ★

★ኽ🌹የኮንያ አበቦች ክፍል ⑨ ✍Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ

ኮንያም ትሲቃለች ፡ አዝመራዎቿ ይቦርቃሉ ፡የተኳሉ ሚዳቆዎች ይፈነጥዛሉ፡ ይህንን ፈገግታ ቢያዩ።

ቀኑን ከሻህ ሱፍያን ጋር ሚዳቆ ስናሯሯጥ አሳለፍነው።የውሃ ቡሃቃቸውን ይዤ እዚ እዚያ እያልጯ ጀምበር መደብዘዟን ያዘች።<< ያ ቨለድ ዛሬ እንኳን ድከሙ ሲለን ነው የመጣነው ምንም የምንይዝ አይመስለኝም>> አሉኝ ሻህ ሱፍያን የጦራቸውን ጫፍ ከመሬቱ ላይ እየሰኩ። <<የመጨረሻ አንድ እንሞክር አለቃ>> እንደተሳለቸው እንዳያስታውቅብኝ እየሞከርኩ ተናገርኩ።በዛው ቅፅበት ቀኗ የደረሰ ግልገል ኣጋዘን ከረጣዥም ሳሮች ስር ድክ ድክ እያለች ብቅ አለች.....ስለታም ጦር አረፈባት።

ወደ ጎጆአችን እየተመለስን ሻህ ሱፍያን ለእኔ የማይገቡ ወሬዎችን ሲቀላቅሉ አስተዋልኳቸው። <<ባይገርምህ የሰራተኞች ማጎሪያውን የወረስኩት ከጀግናው አባቴ ነበር> > ኩራት ይነበብባቸዋል << አባቴም ከአያቶቻችን የተወራረደ የክብር ቅርስ ተቀብሎ እንጂ ከሰው ቀምቶ አይምሰልህ>>።
ጀግናውማ ይህንን አስጠያፊ የታመከ ጎጆ ያወደመው ነው አልኩኝ በውስጤ << እ አለቃ በጣም ይገርማል>>...

ሻህ ሱፍያን ፈረሳቸውን ከአንድ ጥግ ላይ እየጠፈነጓት ነበር እኔ የጎጆው በር ተከፍቶልኝ ስዘልቅ። ቢላል መስገጃው ላይ ቁጭ ብሎ ተስቢሁን ይፈትላል።የተለመደው ግርግር በጥቂቱ ቀንሷል ፡ግዙፉ አሚር ሷሂብ በግራ በኩል ሁለት የሚደባደቡ ሰራተኞችን ሲያገላግል አስተዋልኩት።ቢላል አጠገብ እንደደረስኩ <<የደከመህ ትመስላለህ ሐሰኔ ካልሰገድክ ቶሎ ስገድና እረፍ>> አለኝ
<<ቆይ አለቃችን ሶላት አይሰግዱም እንዴ ቢላሌ >> አልኩት በሹክሹክታ
ፈገግ ብሎ እያየኝ << ሻህ ሱፍያንን መሆን አለበት? አንተምኮ ከቀናቶች በፊት አትሰግድም ነበር ሀሰኔ> > አለኝና ከመስገጃው እየተነሳ ቀጠለ << ረሱላችን •ሶላት እና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን • እንደነገሩን የተባረከ ብሎ ማለት በራሱ ተጠምዶ የሌላውን ሰው ነውር ማየት የተሳነው ነው ብለው ነው>>
<<እሺ እሺ ቢላሌ>> የዚህን ሰው ልብ ምን እንደዚህ አረጋው?።

ከሰገድኩ በኋላ ወደ ቦታችን ሄጄ ቡናማ ኣይኖች ስላላት እንስት እና ስለ ቢላል ንጹህ ልብ ቀላቅዬ እያሰብኩ ተቀመጥሁ። ቀን ላይ እመት አሚናህ የሰጡኝን የወይን ዘለላ ከኪሴ ሥር እያወጣሁ ወሬ ጀመርኩ << ቢላል ከቻልክ እስኪ ስለ ሱፊዎች ሰፋ አድርገህ ንገረኝ >>
ፈገግታ አይለየውም፡ጥርሶቹ ከሁለቱ ፋኖሶች በላይ በጽልመት ውስጥ ያበራሉ፡ ፡የያዘውን ኪታብ ዘግቶ ጭኑ ላይ እያስቀመጠ ትንሽ ወደኔ ፈቀቅ ሲል ተሰማኝ።
<<ሱፊ? ሱፊ የሚለውን ቃል ምሁራኑ እራሳቸው እንደሚሉት ②ሺህ የሚደርሱ ትርጓሜዎች ይኖሩታል።በግርድፍ ትርጉሙ ግን <በፍቅር ወለል ላይ የጸና ኢስላማዊ የኑሮ መርህ> የሚለውን ያስይዘናል>>። ከፍ ባለው መስኮት በኩል ንፋስ በሽውታ ታንጎራጉራለች።ጨረቃዋም ደምቃ ነግሳለች።
<<ሱፊ የሚለው ቃል ሱፋ ወይም •በረንዳ ከሚለው ቃል የተወሰደ እንደሆነ የሚናገሩ ብዙ ናቸው። ምን መሰለህ ሀሰኔ >> አይናማዋን ልዕልት ላለማሰብ እየሞከርኩ ነው።
<<በረሱላችን ዘመን በመዲና መስጂድ ሥር በረንዳ ተበጅቶላቸው የሚኖሩ ምንዱባኖች ነበሩ።ሐበሻዊው ቢላል፡ የናንተው ፋርሳዊ ሰልማን አል ፋሪስ፡ የሮሙ ሱሀይብ እና ሌሎችም ታላላቅ ሶሃባዎች የበረንዳ አዳሪዎች ነበሩ። ማለትም አሏህን ከማስታወስ ሌላ ምንም ጭንቀት ያልነበረባቸው ቤስታቢስቲ ያልነበራቸው ድሃዎች።>>

ስለ በረንዳዎቹ ሰዎች ቅን ልብ፡ውስጣዊ ውበት እና ፍቅር እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ያለድካም ነገረኝ። አንድ ቀን የበሬ ቅልጥም በምጽዋት መልክ መጥቶላቸው አንደኛው ኣጠገቡ ላለው አስቀድሞ ሲሰጥ ፡ ቅልጥሙን አንዱ ለአንዱ ሲሰጥ ተመልሶ ወደ መጀመሪያው ተመጽዋች የመጣበትን ገጠመኝ ሲነግረኝ በአግራሞት አፉን ከፈትኩ።

<<ትክክለኛ ሱፊዎች የእነዚህ ተተኪዎች ናቸው ሐሰኔ። ከራስ በላይ አሏህን የሚወዱ የአሏህን ውዴታም ለፍጡራኖቹ በመራራት የሚገልጹ ሰዎች።ቀዳማውያኖቹ አህለሱፋ ሲባሉ እኚህ ደግሞ የነሱ ተከታይ ሱፊዎች>> ወደቦታው ሲያጋድል ይታወቀኛል << በል ተኛ አሏህ ካለ ነገ እቀጥልልሃለው>>

<< እሺ አሏህ በሰላም ያሳድርህ ቢላሌ>> እንዲህ አይነት ሰዎች በወረቀት ላይ የሰፈሩ ሃሳቦች እንጂ በገሃዱ ዐለም ላይ ተንጸባርቀው የሚያውቁ እውነታዎች አልመስሉህ እያለኝ መኝታዬን አመቻቸሁ።
🎈

🎈ክፍል ①⓪ ይቀጥላል። ⅀★

★⅀ ❦የኮንያ አበቦች ክፍል ①⓪

✍Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ

ህይወት....የምታውቀውን ወይስ የሚሰማህን ትከተላለህ.... የአእምሮ እና የልብ ታላቅ የፍልሚያ ሜዳ

ክቧ የመመገብያ ጠረጴዛ በጠዋቱ ሰራተኞች አጨናንቀዋታል።እኔም ከሰራተኛዎቹ አንዱ የሻህ ሱፊያን አገልጋይ ነኝ።በጎጆው ቤት ቀዳዳዎች የጠዋት ፀሃይ ጨረሮች ተሸቀዳድመው ገብተው ግድግዳው ላይ ተሰክተዋል። ግዙፉ ሷሂብ አሚር የሰማይ ስባሪ የሚያህል የግራ ጡንቻውን እያከከ <<ቶሎ ቶሎ በልታችሁ ቦታ ልቀቁ ዛሬ ከባድ ሥር ይጠብቃችኋል> > ብሎ አንቧረቀ።

ከደቂቃዎች በኋላ ተመጋቢዎቹ ሳሆኖቻቸውን ከቁልሉ ላይ እያስቀመጡ ከጎጆው ቤት ተለቃቅመው ወጡ።
<<ና ሐሰኔ ቶሎ ቦታ እንያዝ>> ቢላል ነበር ኪታቡን እየዘጋ ያናገረኝ።<<እሺ እሺ ግን ዛሬ ትንሽ ሆዴን አሞኛል ቤላል>> አልኩት ከዘመናት በኋላ ያገኘሁት ወንድሜ እየመሰለኝ።
<<ምነው አንበሳው ካልተሻለህ ኢን ሻ አሏህ ማታ ፋቲሃ እንቀራበታለን>> ብድግ ብሎ አዘቅዝቆ እያየኝ ነበር ያንሾካሾከልኝ << ዛሬ በቃ ቀጥታ ወደ ሻህ ሱፍያን ቤት ሂድ የቀኑ ስራ ይከብድሃል ቁርስ ግን ያልፍሃል አሁኑኑ ውጣ አሚር ሳይመጣብህ>>
<<እ እሺ ቢላሌ > >
<< ሁለት ወዶ አይሆንም እሺ ህሰኔ>> አለኝ ሳመነታ አስተውሎኝ.....ይህ ሰው የልብ አንባቢ ነው። <<ሰላም ሁን እሺ ማታ እንገናኝ ቢላሌ>>
<<ኢን ሻ አሏህ>>።

ወደ ሻህ ሱያን በራፍ እንደደረስኩ ቀን የጣላት የበጋ ዳመና እያንጣለለች ነበር።ፀሃዩአም ሙቀቷ ያን ያህል ሆኗል። በሩን ብቆረቁርም <<ይግቡ >> የሚለውን የእመት አሚናህ እናታዊ ድምጽ አሊያም የሻህ ሱፍያንን < <ማነው>> አልሰማሁም። እጀታውን ስቆለምመው በሩ ተከፈተልኝ። << ሰላም አለይኩም>> እያልኩ በዝግታ ገባሁ።የከፍሉ የቅንጦሽ ምንጣፎች እና ንጉሳዊው ወንበር ያለሰው ቁጭ ብለዋል።በተነጠፉት የመመገብያ ሱፍራዎች ላይ የተበሉ የወይን ዘለላዎች እና ከእመት አሚናህ አፍ የማይለየው ጢስ የሚያወጣው ባለ መዐዛው ቀጭን ጎማ ይታያሉ። ዘመናዊ ትምባሆ ብዬ ሰይሜዋለሁ።

በክፍሉ ጭርታ ግራ እየተጋባሁ ጥግ ላይ ካለው ምንጣፍ ላይ ተቀመጥሁ። እንደራበኝ ያወቅኩት ሆዴ እንደ አሮጌ የፊርደውሲ አውቶቡስ ሲያጓራ ነበር። ረሃቤን ለማረሳሳት ከግድግዳው ላይ የተሰቀሉትን በነብር ቆዳ የተሰሩ የአደን ካባዎች እና ቀርከሃ የሚመስለውን የጦር እጀታ ማጤን ጀመርኩ።ከሥሩ ባለው ቁባ መሰል ጋሻ ላይ ከአረብኛ ጋር የሚቀራረብ ጽሁፍ ታትሟል። << አንድ እ ድ ል>> አንብቤ ሳልጨርስ ከደረጃ የሚወርድ የእግር ኮቴ ሰማሁ።ዝግ ያሉ ኮቴዎች። <<ኡማህ ቅድም ነውኮ የመጣሁት> > እያልኩ ፊቴን ወደ ግራ አዞርኩ።ያልጠበቅሁት ቲማቲም የመሰለ ድንቡሽቡሽ ፊት ....ትላልቅ ቡኒ አይኖች።

<< አ አፍወን አንቺ ነሽ እ>> እሷ አጠገብ ስሆን ፋርሲነቴ ይጠፋብኝና ተብታባ ገጠሬ እሆናለሁ። << ሰላም> > አለችኝ ሳታስጨርሰኝ።

<< እነ ኡማህ የሉም እንዴ ዛሬ የት ሄዱ?>> አልኳት በውስጤ መቼም ባይመለሱ ብዬ እየተመኘሁ።
<< ከሩቅ ወዳጅ የምሳ ግብዣ ደርሷቸው ሄደዋል>> ድምፆን ከዚህ በፊት ሰምቼው የማውቀው ሆነብኝ።ምናልባት ቅላጼዋ ላይ የፋርስ ለዛ ቢጨመር የኡሚዬን ውብ ድምጽ ይመስል ነበር።
<<ታዲያ አንቺስ ለምን አልሄድሽም?>>
<< አሞኛል > > የለበሰችው ቀይ ቀሚስ ትኩስ የከረምት አበባ ያስመስላታል። <<አይ ህመም ሳይሆን>> ብላኝ ወደታች አቀረቀረች።
<< ምንድነው ታዲያ?>>
<< ድብርት ። ታውቃለህ ብቸኝነት ሲበዛ ህመም ያላትን ድብርት ይቸርሃል>>
ምን ማለት እንዳለብኝ ግራ ገብቶኝ ቁጭ እንዳልኩ አያታለሁ። << እ እኔ ደሞ ሆዴን አሞኛል>> ።

❦

ከሙሉ ደቂቃ በኋላ በእንጨት የተጠረበ አነስ ያለ ድስት መሳይ እቃ ይዛ መጣች።ነመን አይነት ተክል ከውስጡ አውጥታ << እንካ ይህንን አሽትትበት>> ብላ እጇን ዘረጋች። <<እሺ ሹክረን>> ጣቶቿ ስራ የሚያውቃቸው አይመስሉም። ወርቃማ አንባር ያጠለቀችበት እጇ ..ንጣቱ ሰፋ ባለ ቀይ እጅጌ ውስጥ የተደበቀ ሓጫ በረዶ ይመስላል።

የሻህ ሱፍያን እና የእመት አሚናህ ልጅ እንደሆነች ተረዳሁ። << አሁንስ ተሻለህ አለችኝ>> መድሃኒቱን እየተቀበለችኝ። << አዎ እየቀነሰልኝ ነው>> አልኳት <<ረሃቤም ጠፍቶ ጠግቤአለሁ>> ልላት አስቤ ቀድማኝ አወራች። <<እኔም>> ብላኝ ምንም ሳትናገር ወደ ደረጃው ፈጠነች። ተከተልኳት << ምኑ ነው የቀነሰልሽ?>> ።የደረጃው መታጠፊያ ጋር ደርሳ ነበር << ባይሆን እሱን ተወውና ዛሬ ማታ እንድናወራ ከፈለግክ ከጎጆው ቤት ጀርባ ና>> አነጋገሯ እርጋታ አይታይበትም<<ከኢሻእ በኋላ> >።
<< እ እሺ>> ከንፋለች የሰማችኝ አይመስለኝም <<ስምሽን ግን ማን ልበል?>> የጮህኩ ይመስለኛል የላይኛው ከፍል በር ሲዘጋ ተሰማ<< ያስሚን። ያስሚን የሻህ ሱፍያን ብቸኛዋ ልጅ>>።

<<የሲፊን አበባ> > አልኩኝ ለራሴ በጣውላው ደረጃ ላይ እየተቀመጥኩ።ባባ ጃስሚኖችን ይወድ እንደነበር ሂልዋ ነግርኛለች።እኔ ደግሞ ጃስሚኖችን ማውራት !። ቱርክ የደስታ ዝናብ የሚዘንብባት የተባረከች ምድር መስላ ታየችኝ።በክብ ፊቷ ላይ ያለውን ፈገግታ ሚስጥሩን ፈልቅቄ ማወቅ ፈለግሁ።የሂልዋዬን ነፍስ በአንዲት ልዕልት ውስጥ ያገኘኋት ያህል ተደሰትኩ ።የሚሰማኝ ምንድነው? ለምን ከርሷ ጋር ስሆን ማንነቴን እዘነጋለሁ?።

ከሻህ ሱፍያን ቤት ወጥቼ ወደ ደሳሳዋ ጎጆ አመራሁ።በሩ ከጎጆው በሚበልጡ ጋኖች ተከርችሞ ስለበር ወደ ዋናው መውጪያ አመራሁ።ዞር ብዬ ባይም...በመስኮቱ በኩል ጃስሚን አትታይም።

ከተራራው ሥር ወደ ወከባው የእርሻ ቦታ ስደርስ ሌላ የጫጫታ ዐለም ነበር የጠበቀን።ቢላልን ከአንድ ጋሪ አጠገብ ቆሞ በማዳበሪያ የተጠቀጠቁ ደረቅ ሳሮችን ሲጭን አየሁት።ዝምታ እና ጃስሚን እዚህ መንደር አይታወቁም።

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

❦

❦ከፍል ①① ይቀጥላል.....⸗★

★⸗❦የኮንያ አበቦች ከፍል ①①

@Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ

❦

❦

❦
ከተራራው ሥር ወደ ወከባው የእርሻ ቦታ ስደርስ ሌላ የጫጫታ ዐለም አገኘሁ።ቢላልን ከአንድ ጋሪ አጠገብ ቆሞ በማዳበሪያ የተጠቀጠቁ ደረቅ ሳሮችን ሲጭን አየሁት።ዝምታ እና ጃስሚን እዚህ መንደር አይታወቁም።

ቢላል ወደ ሥራው ቦታ እንደመጣሁ ሲያይ ደስ ብሎት ነበር።እስከ እኩለ ቀን ድረስ አውድማው ላይ ጉድ ጉድ ስንል ከሰነበትን በኋላ ወደ ደሳሳዋ ጎጆ ተመለስን።ለመጀመሪያ ግዜ እኩለ ቀኔን ከቢላል ጋር አሳለፍኩ።
<<ሐሰኔ እነ ሻህ ሱፍያን ከመጡ ሊፈልጉህ ይችላሉ እኮ ለምን መምጣታቸውን አታረጋግጥም>> አለኝ ደረቅ ሩዞችን ከሳህኑ ላይ እየጠራረገ።
የጣውላውን ቤት ከዘለቅሁ ያስሚን <የማታው ቀጠሮአችን ተሰርዟል> ብላኝ የምትሰወር መሰለኝ።<<አይ ቢላሌ ይቆያሉ ቶሎ ሚመጡ አይመስለኝም>>።
በንስር አይኖች እያየኝ ነበር << በምን አወቅህ እንደማይመጡ?>>....ደነገጥሁ።

ወሬውን አረሳስቼ ቢላልን እስከ ግዙፉ መውጪያ በር ድረስ ሸኘሁት።ለቢላል ስለ ያስሚን አልነገርኩትም፡ መናገርም አልፈልግም....ችሎታውም የለኝም።

ከሚሞቀው ጎጆ ሥር ብቻዬን ጋደም እንዳልኩ እንቅልፍ ሸለብ አድርጎኝ የቀን ቅዠቶቼን ያለ ታዳሚ አጣጣምኩ። ልብ ብቻዋን ስትቀር ከሥሯ የተቀበረውን ማዕድን ሰርጋ ታወጣለች።ዘመኑ ምን ቢረዝም ሁኔታው ምን ቢቀየር ባባ ከናፍቆት ጣሪያዬ ላይ ያንጉብባል።የዐለምን አጥናፋት አቋርጠህ ብትኮበልል አሊያም ከሩቅ ሀገር ወሸባ ብትቀልስ እናት አትረሳም፡፡ቤተሰብ ከልብ መዝገብ አይፋቅም።

እየተገፍታተሩ የሚገቡ ያልተረጋጉ ኩቴዎች እና የድካም ኡፍታ የሚያቃስቱ ድምጾች ነበሩ ከእንቅልፌ የቀሰቀሱኝ።ዐረብኛ በተለያዩ ለዛዎች ትወራለች።በደሳሳዋ ጎጆ ሥር።
<<ምነው ያ ወለድ አመመህ እንዴ> > ግዙፉ አሚር ሷሂብ ጠጋ ብሎ አጠገቤ ተቀመጠ።ደንገጥ ብያለሁ ገርሞኛልም።
<< አይ አሁን ተሸሎኛል ሷሂብ>> አልኩት ኢልቡርዚ ተራራ ፊልጋ ያገኘችኝ እየመሰለኝ። <<ጥሩ ዋናው አፊያ ነው አይደል እንዴ>>
አሚራችን የደበረው ይመስላል፡ደፍሬ ጠየቅሁት << አንተም የደበረህ ትመስላለህ ኡጋ ሷሂብ በሰላም ነው?>>።

ጥቂት ዝምታ ሰፈነ።ከአይኖቹ ሸፋን ሥር እንባዎች አምልጠው ለመውጣት ሲታገሉ አስተዋልኩ።የማይሆን ጥያቄ እንደጠየቅሁ አውቄ ደነገጥሁ።በረጅሙ ከተነፈሰ በኋላ ልሳኑ እየተፈታች<< ታውቃለህ ይህች ዐለም ፍጹም አንፃራዊ ናት ከፈጣሪ በቀር። ይህችን ጎጆ ቤት ከውጪ እንዳየሃት የስቃይ እና ችጋር ቤት እንደሆነች ትገምታለህ።ግን በስቃይ ውስጥ ደስታ አለ። በፍቅር ውስጥ እንግልት እንዳለው ሁሉ። >>
ቀጠለ<< ያ ሐሰን ካሁን በኋላ እዚህ ከሳምንት በላይ የምቆይ አይመስለኝም።አንተን ወደዚህ ቤት ያመጣህ ሰው እኔን ደሞ ወደ ሌላ የጉልበት ሥራዎች ሊያዘዋውረኝ ነው።ኮንያን ለቅቄ ልወጣ ነው።>> ያፈነውን ሳግ እየዋጠ << ትናፍቂኛላችሁ ያንተ ውብ እንጉርጉሮም ይናፍቀኛል>>አለኝ። እንባዬ ለምን እንደተንከባለለች አላውቅም ..ለግዙፉ ሰው አነባሽለት ወይስ ያንቺን የስቃይ ነጸብራቅ በእርሱ ሀዘን ላይ አየሻት። << እኛም ትናፍቀናለህ ሷሂብ አሚር>። ፊርጣማ ክንዱ ጀርባዬን መታ መታ ሲያረገኝ ከምዕናብ ዐለም ደንብሬ ወጥቼ ልፊያ እና ጫጫታ የሞላውን ክብ ጎጆ ቤት አስተዋልኩት።

ጀምበር ደብዝዛ በብርትኳናማ ብዕሯ <ልጠልቅ ነው> እያለች ነበር ቢላል በደከሙ ፈገግታዎች እያየኝ ተስቢህ መቁጠሪያውን ይዞ ወደ እኔ ሲመጣ። ይህን ደግ ባለጥቁር ቆዳ ከቀን ወደ ቀን እየቀረብኩት ነው። አመሻሹን የያስሚንን ቡኒ አይኖች በጨረቃ ድምቀት ሥር ላያቸው እንደሆነ ግን አልነገርኩትም።

ከኮንያ ተራሮች ሥር

🌹

🌹ክፍል ①② ይቀጥላል彡★

★彡🌹የኮንያ አበቦች ክፍል ①②

✍Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ

ህላዌ ደብዝዛ፥ደማምቃ ሕመሜ
ኽረ የእናት ያለህ፥ትመለስ ሰላሜ

ጀምበር ደብዝዛ በብርትኳናማ ብዕሯ <ልጠልቅ ነው> እያለች ነበር ቢላል በደከሙ ፈገግታዎች እያየኝ ተስቢህ መቁጠሪያውን ይዞ ወደ እኔ ሲመጣ። ከቀን ወደ ቀን እየቀረብኩት ነው። አመሻሹን የያስሚንን ቡኒ አይኖች በጨረቃ ድምቀት ሥር ላያቸው እንደሆነ ግን አልነገርኩትም።

የቢላልን ትርጉማቸው ጠጠር የሚሉብኝን መሳጭ ዲስኩሮችን እያጣጣምኩ የኢሻእ ወቅት ደረሰልኝ።ከስግደት በኋላ የአሚር ሷሂብን ሸኝት በማሳበብ የጎጆው ሰዎች አንድ ግጥም ጣል እንዳደርግላቸው ጠይቀውኝ እንደበፊቱ ፊራ ተባ ሳልል አዜምኩላቸው። . . .
<<ቢላል ዛሬ ገላዬን ለቅለቅ ማለት እፈልጋለሁ መጣሁ በቃ>> አልኩት ተሰናብቼው ስወጣ በድምጼ የተማረኩ ደካማ ፊቶች እስከመውጪያው ድረስ እየሸኙኝ።

የጎጆውን ጠርዞች ታክኬ ወደ ጀርባ ስሄድ በንፋስ ሿሿታ እና በሌሊት ወፎች ሲርሲርታ የታጀበችው ጨረቃ ሙሉ ሆና ተኮፍሳ ነበር።ከውሃ ባልዲዎች እና ትላልቅ ቡሃቃዎች መሃል ላይ ጎጆውዋን ተንተርሼ ቁጭ አልኩ። ጃስሚን ከመጣች ይህ ሌሊት እንዴት ውብ ሆነ!

ከፊት ለፊቴ በሚታየው ሰፊ የሩዝ እና ሻሂቅጠል ሜዳ ጀርባ ትላልቅ ተራራዎች ተኮልኩለዋል። የሲፊኑ ኢልቡርዚ ግን ብቸኛ ግዙፍ ፍጥረት ነበር። ስለ ጥብቶቹ የካይት ውድድሮቼ እያሰብኩ ሳለ ነበር ከበስተቀኝ በኩል ጉሮሮ ሲጠራረግ የሰማሁት።
<<እኽእኽ ሰላም አለይኩም>> ባለችበት ቆማ እያየችኝ ነው።
<<ወአለይኩም ሰላም ያስሚን እ በሀሳብ ባህር ልሰጥም ስል ነው ያዳንሽኝ>>። እጆቿን ጠላልፋ እንደ ህፃን ግራ እና ቀኝ እየተወዛወዘች <<የምን ሃሳብ ወዴትስ ነው የሄድከው>>
<<እ እሱን ተይው ምናልባት ሌላ ቀን እነግርሻለሁ>> መቼ ከተቀመጥኩበት እንደቆምኩ እንጃ << ነይ ቁጭ በይ እዚህ ጋር>> ተልኳት ቦታው ላይ ሌላ መቀመጫ ስለማይታይ።

<< ብዙ የምቆይ መሰለህ እንዴ> > እየተጠጋችኝ ነው << አልቆይም ትንሽ ከቆየው በሩን ከውስጥ ይቆልፉታል>>. . . . . በሁለት ስንዝሮች ያህል ተራርቀን ለደቂቃዎች አወራን።የጎጆው ቤት ኑሮ እንደሚከብድ ስነግራት ቡኒ አይኖቿ ሃዘን ሲገባቸው አስተዋልኩ።ደስ አለኝ ። ስለኔ ብላ የምታዝን ባለቡኒ አይን ውብ የኮንያ እንስት ስላገኘሁ።
<<ልሂድ በቃ ሰላም አለይክ >> ደንገጥ ብላ የተጠራች ሰው ትመስላለች <<ስምህ ደግሞ ሐሰን ነው አ እነእማ ሲያወሩ ሰምቼአቸዋለሁ>> ብላኝ ፈገታዋን በድቅድቁ ምሽት ላይ ጣለች። በሳቀች ቁጥር ለምን ልቤ እንደምትፈነድቅ አላወቅሁም። <<ወአለይኪ ሰላም እ ጃስሚናህ መች ነው ግን በድጋሚ የምትመጪው>> . . . . የእጅ ውዝወዛዎችን ብቻ መለሰችልኝ። ደስ የሚሉኝ ነገሮች ሁሉ ርዝማኔ የላቸውም ህመሞቼስ? ዬልዳ። ረዥሟ የዬልዳ ሌሊት አንደኛዋ ዥረታማ ስቃዬ ናት።

ለመታጠብ የወጣሁ ሰው እንደሆንኩ ሳስታውስ ነበር ከቆምኩበት የተንቀሳቀስኩት:: የያስሚን እንደ ውቅያኖስ ዳርቻ የነጣ ፊት ከጽልመቱ ፊት ድቅን እያለብኝ ብቻዬን ፈገግ እያልኩ ከጎጆው ዘለቅሁ።የጎን ለጎን ወሬዎች ጦፋዋል መሃል ምሶሶው ላይ ያሉት ፋኖሶችም በመሃላቸው ያለውን ወፍራም እንጨት እንዴት እንደሚያስወግዱት የሚወያዩ ይመስላሉ። << ሀሰኔ ሀሰኔ ከመተኛታችን በፊት አንድ የመጨረሻ ድገምልን>> አንድ ከሲታ ቀውላላ ወጣት ነበር ፊት ለፊቴ መጥቶ የቆመው። << እሺ >>
<< ደሞ አብረከው የምትቀመጠው ሰው የሷሂብ አሚር ተተኪ ሊሆን ነውኮ>>
<< ማን? ቢላል ተቆጣጣሪ ሊሆን? >>. . . . .
❦
<<አንዴ አንዴ ዝም በሉ ትኩረታችሁን ወደ ሐሰን>> አለ ላዜምላቸው እንደሆነ ያወቀው ሷሂብ አሚር ሃዋሪያው በሚመስሉት የጎጆ ጓዶች ተከበ።
ዝግ ባለ እንቅልፍ የሚያመጣ ድምጽ ቀደስኩላቸው <<ደዋኡከ ፊከ ወላ ተዕለም. . . . .ደዋኡከ ሚንከ ወላ ተሸዑር. . . . .መድሃኒትህ ውስጥህ መች አውቅኸውና . . . . .መድሃኒትህ ካንተ መች ተረዳህና. . . . . ወፊከ ኢንጠዋ አለመል አከበር. . . . . .ይህች ግዙፍ ዐለም ውስጠትህ ላይ ሰከና >>

< < ሐሰኔ በኢማም ዐሊይ ግጥም አነቃከኝ አይደል፡አሷህ ይወደዳቸው በጣም የምወደው መስመራቸው ነበር> > ቢላል ነበር የቀኝ አይኑን እያከከ ነ ዜማዬን ጨርሼ አጠገቡ ከመድረሴ ያወራኝ።
<<መቼ የተማርከው ነው ግን?>> አለኝ እየተገረመ።
<< ሂልዋ ደጋግማ ትለው ስለበር አይረሳኝም>>. . .

ህይወት አንጻራዊ ናት፡የዛሬዋ ምሽት ደስ ትላለች ።

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

🌹

🌹ክፍል ①③ ይቀጥላል....

彡★

★彡🌹የኮንያ አበቦች ክፍል ①③

@Ⓐⓨⓜⓔⓝⓙ

አይደለም ክረምቱን፡አሳልፎ በጋን ወዳጅ ያስተከዛል፡ ያደረ ላንድቀን

በሳምንቱ መጨረሻ ማለዳ ደሳሳዋ ጎጆ ላይ የሸኝት ለቅሶ ተካሄደ።ትልቅ ሰው ሲያለቅስ ማየት ስሜትን የሚረብሽ ትዕይንት ነው። ሷሂብ አሚር ኮስታራ እና ጉልበታም የጎጆው አለቃ እንደነበር ሁሉም ሰራተኞች የሚያውቁት ቢሆንም በሁሉም ስምጥ ህሊና ውስጥ የተቀበረ እንቁ መሰል እውነታ አለ •ፍቅር•። አብረከው የሳቅከውን ሰው ልትረሳው ትችላለህ ፡አብሮህ ያለቀሰው አብሮህ የተጎሳቆለውን ግን ዝንተዐለም ከልብህ ጽላት ላይ ታሰፍረዋለህ።

<<አሷህ በድጋሚ ያገናኘን አሚር ሷሂብ> > አለ ቢላል በጥቁር ፌስታል እቃውን ሸክፎ ወደ ውጪ የሚያመራውን ሷሂብ ጀርባ መታ መታ እያደረገ።<<አሷህ ከናንተ ጋር ይሁን>>...

ከቁርስ በኋላ ሥራ ሳልሄድ ቀጥታ ወደ ሻህ ሱፊያን ቤት አመራሁ።ብቻቸውን ቁጭ ብለው ፂማቸውን የሚፈትሉት ሻህ ሱፍያን ከባለግርማው ወንበራቸው ላይ ሆነው ተክዘው ነበር።

<<ሀሰኔ እኔ ወንድ ልጅ እንደሌለኝ ታውቃለህ አይደል> > አሉኝ ወደ መጪያው እንደተከዙ <<ከአሁን በኋላም ሌላ ልጅ መውለድ የምንችል አይመስለኝም ያለችን ያቺው ያስሚን ናት>> ይህንን ስም ስሰማ የጠዋት ሻሂ እንደጠጣሁ ያህል ነቃሁ። ሻህ ሱፊያን ወደ እኔ እያዩ ቀጠሉ <<ያስሚኔን ታውቃታለህ? >>።

መለስኩላቸው << እ አይ ማለቴ አዎ አይቺኣት አውቃለሁ>> ብዬ ተርበተበትኩ። ሁኔታዬን አላስተዋሉትም ነበር <<ለማንኛውም ያ ሐሰን አንተ ጎበዝ እና ታታሪ ልጅ ነህ በሥራህ ጠንክረህ ከቀጠልክ ከጎጆው ቤት ተራ ሰራተኝነት አልፈክ ሌሎች ሃላፊነቶችን መረከብህ አይቀርም ደግሞ...>>

እመት አሚናህ ነበሩ አቋርጠውን የተቀላቀሉን< <ሰላም አለይኩም እንዴት ነው ነገሩ ሚስጥር የምታወሩ ትመስላላችሁ>> እናታዊ ፊታቸው እቤቴ ውስጥ ያለሁ እንዲመስለኝ ያደርገኛል።

<<ዛሬ የገቢያ ቀን ነው ሱፍያን ያስሚን ወደ ሐርማንቺክ መደብሮች መሄድ አለባት >> << ሺምር ጉዳይ ሊያስፈጽምልኝ አንድ ቦታ ልኬዋለሁ ከማን ጋር ልትሄድ ነው?>> ብለው ወደ ባለቤታቸው ዘወር አሉ <<እንጃ ግን የግድ መሄድ አለባት >>እመቤቲቱ ለአፍታ ያህል ካዩኝ በኋላ << ለምን ከሀሰኔ ጋር አይሄዱም>> ብለው የምገባበትን አስጠፉኝ።

ከሁለቱ ባል እና ሚስቶች መሀከል ሆኜ ፡ልቤ ስትደልቅ ድምድምታው የሚሰማብኝ መሰለኝ ።

<< ይቻላል>> አሉ ሻህ ሱፊያን።

ወደ ጓሮ ሄደው ዞርዞር እያሉ ንብረት ሊያዩ እንደሆነ ተናግረው በኩራተኛ የዝግታ አካሄድ ክፍሉን ለቀው ወጡ።

እሜቲቱ <<ና ሀሰኒ የገቢያ ኩታህን ልደርብልህ ብለውኝ >> ወደ ላይኛው ክፍል መውጣት ያዙ።ጃስሚኔ ለምትቀመጥበት ክፍል በስተግራ ባለው ገብተው ብቅ ካሉ በኋላ ጥቁር የኢማሞች የሚመስል ካባ አቀበሉኝ። <<አሁን በእጅህ ያዘው ይሞቅሃል>> አሉኝ ወደ ጃስሚን ክፍል እየዘለቁ።

🌹

ከያስሚን ጋር እንደማይተዋወቁ ሰዎች ተራርቀን ከግቢው እየወጣን ሳለ እመት አሚናህ ከጣውላው ቤት መግቢያ ላይ ቆመው << በሉ አሷህ ሰላም ይመልሳቸሁ> > ሲሉ ይሰሙ ነበር።

ጃስሚን እንደ ሩቅ ሰው ናፍቃኛለች ፡ከጥንት እንደማውቃት ልዕልት በርሷ ክልል ውስጥ ሰላሜን አገኛለሁ <<ያስሚን>> አልኳት በተኮለኮሉ ጋሪዎች በኩል እያለፍን።

<<አቤት ሀሰን>>
<<በእግር ነው ምንሄደው?>>
<<ኸረ ትንሽ ራቅ ይላልኮ>> አለችኝ ወደ እኔ ዞር ብላ ከስር ወደላይ እያየችኝ።በቡኒ አይኖቿ ላይ ጀምበር ስትሰፍር ሉል እና መርጃን ያዘሉ ባህሮችን እንዳየሁ እደሰታለሁ :የተበተኑ ሳፍሮን ይመስላሉ የአይኗቿ መሃል ላይ ያሉት ዝንጉርጉር ቡኒ ቀለማት።
<<ታዲያ በምን ልንሄድ ነው?>>

ጥያቄዬን ከመጨረሴ ከኋላችን በኩል የፈረስ ኮቴዎች ተከተሉ።የፈረሷን ጀርባ በጂራፍ እየላጠ <<ቶሎ ግቡ ጸሃዩኣ ሳትበረታ እንድረስ>> አለን የሻህ ሱፊያን ቅጥር ፈረሰኛ። ከሰረገላው ቀድሜአት ገባሁ.....መርገጫው ከፍ ስላለባት ከውስት ሆኜ እንድሰባት እጇን አቀበለችኝ.... ጃስሚን... ሽምጥ ጋላቢውን ዘመን ማቆም ቢቻል ኖሮ በዚህ ቅጽበት ቀጥ አደርገው ነበር።እጇ ከልስላሴ የሚቀነጠስ ይመስላል ደግሞም ልክ እንደሂልዋን እቅፍ ይሞቃል።

ቱርክ :ጉዞ ወደ ሀርማንቺክ ገበያ

🌹

🌹ክፍል ①④ ይቀጥላል.....彡★

★彡🌹የኮንያ አበቦች ክፍል ①④

@ⒶⓎⓂⓔⓃⓘ

ሽምጥ ጋላቢውን ዘመን ማቆም ቢቻል ኖሮ በዚህ ቅጽበት ቀጥ አደርገው ነበር።እጇ ከልስላሴ የሚቀነጠስ ይመስላል ደግሞም ልክ እንደሂልዋን እቅፍ ይሞቃል።

በመስኮት በኩል የሚታዩት ሰፋፊ እርሻዎች ቀስ በቀስ ወደ መኖሪያ ቤቶች እና ትናንሽ መደብሮች ሲቀየሩ አስተዋልኩ።ምድር ስትተነፍስ እየተሰማኝ የጎጆው ቤት ገፈት ቀማሾች ሁሉ ይህንን ንጹህ አየር ቢምጉ ብዬ ተመኘሁ።
<< አታወራም እንዴ ሐሰን>> በሹክሹክታ የጋላቢውን ፊት በቆሪጥ እያየች አወራችኝ።
<< ውጪ ባለው ዐለም ተመስጩ ነውኮ>>
<< ውስጥህ ያለውን ይመስለኛል በውጪህ የምታየው >> አለችኝ ድምጿቷ ከቅድሙ ከፍ እያለ።
< ውብ ነሽ አንደበተ ጣፋጭ > ከራሴ ጋር እያወራሁ ዝምታን ከፈገግታ ጋር መለስኩላት ።

ግማሽ ሰዐት ከሚሆን ግልቢያ በኋላ ጃስሚን <<ደርሰናል በቃ ሷሂብ አሚን እዚህ ጋር አረጋጋው>> ብላ ከሥሯ ያለውን ዘንቢል አነሳች።ወደ አሚን እያየች <<እዚሁ ጠብቀን በቃ አሚን እኔ እና ሐሰን እቃዎቹን ገዛዝተን እንመጣለን>> ብላ በቡኒ አይኖቿ እንድወርድ ምልክት ሰጠችኝ። ከያስሚን ጋር አንድላይ መሸመት ህልም እየመሰለኝ ልክ አባቱን እንደሚለማመጥ ህፃን ወደ ባለሰረገላው ዞሬ ሚስኪን እይታ ቸርኩት። << እሺ እዚሁ እጠብቃችኋለው ሰላም ይመልሳችሁ> > ብሎ ከኪሱ ሥር ትምባሆውን አወጣ።
🌹
ከዳር እና ዳር የአትክልት መደቦች ከፍ ብለው ወደተሰሩበት የተጨናነቀ ገበያ ደረስን። ያስሚን እንደደከማት ስለገባኝ ዘንቢሉን ተቀብያት ጎዞአችንን ቀጠልን። ቀስ እያሉ የሚያዘግሙ የጎበጡ አሮጊቶች አረማመዳችንን ቀሰስተኛ አድርገውታል። ተራራ የሚያክል ጥቅል የማዳበሪያ ፍራፍሬዎችን የተሸከሙ ሰርቶአደሮች እየገፈታተሩን ያልፋሉ.....ያስሚን ከቀኝ በኩሌ ወደ እኔ እየተጠጋች አወራችኝ።ዘማዋን ከጫጫታማው ገበያ ውስጥ ነጥዬ መስማት አላቃተኝም።
<< ዘንቢሉን በግራ እጅህ ያዘው እስኪ> > አለችኝ ወሬዋ እንዲሰማ ጮክ እያለች
<< ለምን እንዴ?>>
<< ተወው በቃ ቦታው ለማስረዳት አይመችም >> ብላኝ ፊቷን ስትጥለው አየኋት።

በመሃላችን የያዝኩትን ዘንቢል ወደ ግራ እጇ አሳልፌ ያዝኩት! ቀኝ እጇን ከግራ እጇ መንደር ስመልሰው የጃስሚን ጸሃይ ያቀላው ሀሪር እጅ ተቀበለኝ...ዞር ብዬ አየኋት ኩርፊያዋን ሰንጥቆ የሚወጣው ፈገግታ የሲፊንን ንጋት አንግቦልኝ ከአይኖቼ ቀጠና ደረሰ።እጇን ስጨብጥ የሂልዋ የሩማን ገበያ ትውስታዎች ከሃሳቤ ተደቀኑ.....እንደምን ልንገራት? እርሷ ኢታውቅም እንጂ እርሷ ለኔ ጥዬው የመጣሁት ዐለሜ ናት።

ሰው አልባ ጎዳናዎች ላይ የምንንሸራሸር እንመስል ነበር።ከዘይቱን መሸጫ መደቦች ሰፈር እስከንደርስ ድረስ ተያይዘን አወራን። ገበያ ይዛኝ የምትወጣ ሂልዋ የምትባል እህት እንደነበረችኝ ነገርኳት....<< እህትህ ውብ ስም ነው ያላት> >።
ነጋዴዎች የሚያወጡት የተለያዩ ድምጾች ሲጋጩ የሚፈጥሩትን ወዥባራ ህብር እየሰማን ተሳሳቅን..... ③ኪሎ የሚሆኑ ዘይቱኖችን ገዝተን ወደ መጣንበት መመለስ ጀመርን።

የሷሂብ አሚን ፈረስ ከቆመችበት ልንደርስ ስንል << ደግሞ አሏህ ካለ ማታ እናወራለን ደከሞኛል ብለህ እንዳትተኛ>> ብላኝ ፈጠን ፈጠን እያለች ወደ ሰረገላው ተጠጋች። በመጨረሻ ወሬዋ በአዲስ ጉልበት ተሞልቼ ድካሜን አራግፌ ከሰረገላው ዘለቅሁ።
<<ቆየንብህ እንዴ ሷሂብ>> ጃስሚን ነበረች በእጆቿ ሙቀቷን እያራገበች የጠየቀችው።
<< ኸረ አልቆያችሁም ቶሎ ነው የመጣችሁት!>> ... ምናለ መንገድ ላይ አረፍ ባልን፡ ምናለ ሁሉንም ገበያዎች ተዘዋወረን በጨረስናቸው። በጨረፍታ ሳያት እርሷም የኔን ሃሳቦች የተጋራችኝ መሰለችኝ ።አፏን በእጆቿ እየሸፈነች አይኖቿን ወደ መሬት መለሰቻቸው። ለምን ይሆን የምታፍረኝ? እርሷም ትወደኛለች? ወይስ ጭርታዋን ማስወገጃ አባቷ የገዛላት ላሽከር ነኝ.....እንደለመድኩት ከመስኮት ወዲያ ያለውን ዐለም እየቃኘሁ በሃሳብ ትብታቦ መጠላለፌን ያዝኩ።

ቱርክ ከሃርማንቺክ ገበያ መልስ

ክፍል ①⑤ ይቀጥላል ⅀★

★⅀የኮንያ አበቦች ክፍል ①⑤

✍Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ

ለምን ይሆን የምታፍረኝ? እርሷም ትወደኛለች? ወይስ ጭርታዋን ማስወገጃ አባቷ የገዛላት ላሽከር ነኝ.....እንደለመድኩት ከመስኮት ወዲያ ያለውን ዐለም እየቃኘሁ በሃሳብ ትብታቦ መጠላለፌን ያዝኩ።

ከፍጥረታት ከተነጠለው የኮንያ ቤታችን እንደደረስን ያወቅሁት <<ውረድ እንጂ ሀሰን> > የሚለውን የጃስሚን ቀጭን ድምጽ ስሰማ ነበር። የገዛናቸውን ፍራፍሬዎች ተሸካክመን ከቅንጡው የሻህ ሱፍያን ጎጆ እንደዘለቅን እመት አሚናህ ፊት ለፊት ከሚታየው ወፍራም መጅሊስ ላይ ጋደም ብለው አገኘናቸው።ያስሚን ከኋላዬ በኩል <<ኡፍ እንዴት እንደደከመኝ ብታውቅ >> ብላ የያዘችውን ፌስታል አስቀምጣ ወደ እኔ ተጠጋች።በዛው ቅጽበት እመት አሚናህ ፊታቸውን አዙረው ከተኙበት በተንገላጀጀ ድምጽ <<መጣችሁ እንዴ ያስሚኔ>> ሲሉን ያስሚንን ስትደነግጥ አስተዋልኳት። አመሻሹን እንዳልቀርባት በእጆቿ ምልክት እየሰጠችኝ <<አዎ ኡማህ ዝኩኒዎቹን እላይ ቤት ማጠራቀሚያ ላይ ላርጋቸው ቢቃ> > ብላ ከደረጃው ተሰለበች።መታጠፊያዋ ላይ ያንን ጨራሽ ፈገግታዋን ጥላብኝ ስትሄድ ምሽት እና የጨረቃ ድምቀት ናፈቁኝ።
<<ሐሰኔ ና እነዚህን ወይኖች ያዝ፡ ሱፍያን ስለሌ ወደ ጓደኞችህ መሄድ ትችላለክ>>እመት አሚናህ በተኙበት ሆነው ነበር የሚያወሩኝ። <<አልሀምዱሊላህ>> አልኩኝ .....የሚያስብልኝ ሰው እንዳለ ሲሰማኝ።

ከተራ ሰራተኛነት ወደ አለቃነት የተሾመው ቢላል ጃን በሰፊው ሜዳ ላይ ከሰራተኞች እኩል እየፈጋ ነበር ያገኘሁት ። ኮቴዬን አጥፍቼ ቀስ ብዬ ከኋላው ኮርኮር ሳደርገው <<አሏሁ አክበር>> ብሎ ዞር አለ።እኔ መሆኔን ሲያያ ፈገግ እያለ <<መጣህ እንዴ ሀሰኔ>> ብሎኝ ተኮር ብሎ አየኝ።<<ዛሬ ደስ ብሎሃል ልበል? ምን ተገኘ?>> ሲለኝ ባላሰብኩት ጥያቄ የምገባበት ጠፋኝ።
<< እ እንትን ይሄ የቱርክ ገበያዎች እና የሸከላ ህንፃዎች እንዴት ደስ ይላሉ መሰለህ>> ከአይኖቹ ላይ እይታዬን ወደታች ቀብሬ << ከሻህ ሱፍያን ልጅ ጋር ወደ ገበያ ሄደን ነው ያን ሁሉ ያየሁት፡ ብታይ ከመስኮቱ አንዴም አይኔን አልነቀልሉም ቢስሚላህ የቦታዊቹ ውበት>>።
<<ዋናው መደሰትህ ነው ሐሰኔ ።በል እንግዲህ አረፍ በል ትንሽ አዝመራዎችን ሰብስብ አድርገን ወደ ጎጆአችን እንመለሳለን>> አለኝ ከያዝኩት የወይን ዘለላ ላይ አንዷን ወይን ቀንጠስ አድርጎ እየወሰደ።

❦

ምሽቱ የሌሊት ንፋሱን አዝሎ በሌሊት ነፍሳቶች ሲርሲርታ ታጅቦ ከደጃችን ደርሷል።ከኢሻእ ሶላት በኋላ ቢላል ኪታቡን እያነበበ ሳለ ነበር የመውጣት ፍቃድ የጠየቅሁት። << ሐሰኔ እንዳትቆይ እሺ ደሞ ብርድ ይመታሃል ያንን ፎጣ ጣል አድርግ>> ብሎኝ ወደ ንባቡ ተመለሰ። ጸባዩ ይገርመኛል ቀን ላይ ከሻህ ሱፍያን ልጅ ጋር ወደ ገበያ ሄድኩ ስለው ምንም አልጠየቀኝም ፈጣሪ ለከተባቸው ትዕይንቶች እጅ የሰጠ ይመስላል። ጃስሚኔን ያውቃት ይሆን?

ከነጆው ጀርባ ባሉት የውሃ ቡሃቃዎች መሀል መቀመጫ አበጃጅቼ ያስሚንን መጠባበቅ ያዝሁ።ምሽቱ ይበርዳል። ንፋሱ እያንከባለለ ከሜዳው ላይ የሚያመጣቸው ቅጠሎች ውፍ ውፍ ሲሉ ይሰማኛል። ከተራራው አናት ላይ ያሉ ደመናዎች በጨረቃዋ ብርሃን ሰማያዊ ገጾች ላይ የተሳሉ የጥበብ ሥራዎች ይመስላሉ። <<የአሷህ ግዛት ትልቅ ናት አይደል >>አልኩት ለራሴ.....

<<እህ እህ ሰላም አለይኩም እዚህ ቤት >> አዎ ድምጿ ከቀርከሃ ዋሽንት ዜማ ይለሰልሳል። ቀና ብዬ እያየኋት <<ወአለይኪ ሰላም ያስሚን >> አልኳት።እጆቿን በሆዷ ላይ ጠላልፋ ኩምትር ብላ ቆማ የበረዳት መሰለችኝ።<<ደግሞ እዚህ ቤት አልሸኝኮ ውጪ አይደል እንዴ ያለነው ጃስሚናህ?>>
ፈገግ ብላ በስሱ ሳቅ ስትል በጨረቃ ወገግታ የትንፋሿን እንፋሎት አየሁት።አይኖቿን ጠበብ አድርጋ <<ደስ የሚሉህ ቦታዎች ሁሉ ቤቶችህ የሞቁ ጎጆዎችህ ናቸው ዋሻ ይሆን ኮረብታ ተራራም ይሁን ሜዳ ከምትወደው ሰው ጋር ስትዘልቃቸው እጅ ነስተው ይቀበሉሃል> > ።
ንግግሯን በደንብ አልተረዳሁትም።ቦታውን ነው እኔን ያወደሰችው?
ከተቀመጥሁበት እየተነሳሁ <<እሺ እሺ ዛሬ ደሞ ከማን ጋር ነው የዋልሽው ባክስ> >አልኳት የሂልዋ ግራ ኢጋቢ ንግግሮች ትዝ እያሉኝ።..... <<ከማንም ጋር አልዋልኩም ግን ስለ አንፍ የቅርብ ሩቅ ሰው እየሰብኩ ነበር>> ለደቂቃዎች ቆመን ካወራን በኋላ የነጆው በር ሲከፈት ሰማን።ግድግዳውን ታክኮ ወደኛ የሚመጣ ኮቴ ስንሰማ በድንጋጤ እየተያየን ጃስሚን ቀድማኝ አወራች። <<ና ሐሰን ሜዳውን እናቋርጥ አንድ ላይ መታየት የለብንም >> ብላ ተንሾካሾከች ። << ግንኮ ያስሚ...>> ኣላስጨረሰችኝም እየንተተችኝ ከሚኮረኩረው ሳራማ ሜዳ እጇን ይዛኝ ገባች።

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

❦

❦ክፍል ①⑥ ይቀጥላል彡★

★彡❦የኮንያ አበቦች ክፍል ①⑥

✍Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ

በነፍቆት ጣሪያ ላይ፡ስቃይ ይጋልባል
ቅርብ ወራጁን ለጋ፡እሩቅ ያላስባል

ግድግዳውን ታክኮ ወደኛ የሚመጣ ኮቴ ስንሰማ በድንጋጤ ተያየን። <<ና ሐሰን ሜዳውን እናቋርጥ አንድ ላይ መታየት የለብንም >> ብላ ተንሾካሾከች ። << ግንኮ ያስሚ...>> ኣላስጨረሰችኝም እጇን ይዛኝ እየነተተችኝ ከሚኮረኩርረው ሳራማ ሜዳ ይዛኝ ገባች።እንደ ህጻን ከኋላዋ አስከትላኝ ረዣዥሞቹን ሳሮች ከፋፍተን ከአንድ አጠር ያለ ዛፍ ሥር ደረስን። ያስሚን በትንፋሾቿ እየሳቀች <<በጀርባው በኩል እንቀመጥ በቃ የመጣው ሰው ግን ማነው ያየን ይመስልሃል>> አለችኝ።
<<ማንስ ቢሆን ምን ልዩነት ያመጣል ጃስሚን>>

ጨረቃ ከፊት ለፊታችን ሰፋ ብላ ሞልታ ተሰቅላለች።ያስሚን ትከሻዬን ስትደገፈኝ ጥንቱ ላይ በሰፊው ኢራኒይ አልጋ ላይ የማጣጥመውን ድሎት እና ሰላም አገኘሁ። <<አንቺ ግን የኔ ምንድን ነሽ ጃስሚን>> አልኳት ቃላቶቹ ከአፌ እያመለጡኝ። << እንጃ>> የፍርሃት ዜማ ከውስጧ ይንቆረቆር ነበር << እንጃ ሐሰን ብቻ እ>> ራሷን ከትከሻዬ ላይ አነሳች <<እ ካንተ ጋር ስሆን ደስ ይለኛል።የብቸኝነትን ዐለም እዘነጋዋለሁ>>።

ምንም አልመለስኩላትም።ለደቂቃዎች ዝምታ ከነገሰ በኋላ በድጋሚ አወራች።ነቃ ያለች ትመስላለች <<ባለፈው የሰጠውህ ጎመን ሚመስል መድሃኒት አስታወስከዋ? >>

<<አዎ ወዲያው ያሻለኝ መድሃኒት አይደል ?>>

አፏን ይዛ በጥግ አይኖቿ እያየች ሳቀችብኝ።ፈገግታዋ የምሽቱ ድምቀት ነው።<< ወይ ሐሰን ተሸውደሃል ምንም መድሃኒት አይደለምኮ ጥቁር የንመን አትክልት ዘር ነው>> ግራ እየተጋባሁ አተኩሬ ሳያት ማብራራት ጀመረች። << እምነትህ ነበር ከበሽታው ያዳነህ።መድሃኒት ላምጣልህ ስልህ አመንከኝ። እምነት ለመንፈስም ይሁን ለስጋ ፍቱን መድሃኒት ነው>>

<< ተጫወትሽብኝ >> ብዬአት ገፋ አደርጌአት አፈር እንደማለት ስል <<መድሃኒቱን እንዳመንከው ታምነኛለህ ግን ሀሰን>> አለችኝ።

<<አዎን ጃስሚናህ የመድሃኒቱ ቀማሚ ማን ሆነና>>።

ጉንጮቿ ቀያይ ቲማቲም መስለው ልሳኗ ዝምታን መረጠ። ቡኒ አይኖቿ በክብ ፊቷ ላይ ተዘናፍለው የመሄጃ ፍቃድ ጠየቁኝ <<ልሂድ በቃ ዛሬኮ አረፈድኩኝ። ግን በቃ ሌላ ምንም የምትነግረኝ ነገር የለም እ>>። በልቤ ሳወራ አላታውሳለሁ። የምነግርሽ አለኝ እወድሻለሁ ግን ደሞ እፈራለሁ። እኔ የሲፊኑ ሐሰን ነኝ የሒልዋ ፍንጣሪ! የወደድኩትን ሁላ ለማጣት የተፈጠርኩ። << እ አ አዎ ምንም ምነግርሽ ነገር የለም ሂጂ ቶሎ ሰዐቷ ሄዳለች>> ፊቷን ጥላዋለች።<<እሺ ቻው ሰላም አለይክ>> ....ልቤ ግን <ጃስሚኔ ተመለሺ> እያለ ሲማፀናት ነበር።

❦

የነጆውን በር ቀስ ብዬ ከፍቼ ገባሁ።የቤቱ ድባብ ፈጽሞ ከሌላው ቀን የተለየ ነበር።አዲሱ አለቃችን ሷሂብ ቢላል ከምሰሶው ፈንጠር ብሎ በተንዘነዙ ጨርቆች ላይ ልክ እንደ መድረሳ አስተማሪ ተቀምጦአል። አጠገቡ እንድቀመጥ ምልክት ሰጥቶኝ የሚያወራውን ቀጠለ። <<እናንተ ሰዎች ሆይ ይህች ዐለም የውሸት ክምር እና የብልጭልጭ ጎተራ ናት።ከቀጣዩ ዐለም ስትነፃፀር ከጭላጭ ውሃ ብሎም ከንመንዘር ፍንጣሪ ታንሳለች>> ድምጹ ባለግርማ ጎርናና ተወርዋሪ አይነት ነው። << ረሱላችን ሶላት እና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሆንና ይህች ዐለም የአማኝ እስር ቤት እንደሆነች ነግረውናል፡ ታዲያ ለምን ድሎትን እንጠብቃለን? እስኪ ንገሩኝ ስለምን እናማርራለን?>> .....ለግማሽ ሰዐት ያህል በምሽቱ ጣሪያ ሥር ዝምታ እና የቢላል አስፈራሪ ምክር ወንበር ያዙ።

በድጋሚ ጎጆዋ በሹክሹክታ እና በሚያንኮራፉ ትንፋሾች ህይወት ተዘራላት። <<አንተ ልጅ ግን ማንን ለማግኘት ነው የምትወጣው> > አለኝ ብርድልብሱን ጨብጦ ለመኝታ እየተዘገጃጀ።

ድንጋጤዬን ዋጥ አድርጌ መለስኩለት። <<አንድ ጓደኛ አለኝ ሻህ ሱፍያን ጋር የሚኖር ዝምብለን የባጥ የቆጡን ማውራት ደስ ነው ሚለን>>

<<ከሆነም ጥሩ አንድ ቀን ታስተዋውቀኛለህ>> <<እ እሺ ኢንሻ አሏህ ችግር የለውም>> ።ስለዋሸሁት ደስ አላለኝም።

ስለ ጃስሚን መድሃኒት እና እንደ ቀይ ወይን የሚጣፍጡ ንግግሮቿ እያሰብኩ ከአሮጌው ብርድልብሴ ሥር ፈገግታ አንግቤ ተኛሁ።ቢላል ከዚህ ሌላ ምንም አልዋሸሁኩም።

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

👇👇👇

❦❦❦❦❦❦❦❦❦❦

□ክፍል ①⑦ ከ ⑤⓪ የአንባብያን ላይክ በኋላ ይቀጥላል።

❦❦❦❦❦❦❦❦❦❦彡★

★彡❦የኮንያ አበቦች ክፍል ①⑦

ፍልሰቱ ካየሩ ከተራራው ነበር
ሌላም አጣሁ እንጂ ስሻገር ከድንበር

<<ወንድሞቼ በሰላም ያሳደራችሁን ፈጣሪ ማመስገን እንዳትዘነጉ። በማለዳውም አንድን ዝካሬ ብትሆንም አነብንቡ ከዝንጉዎች መዝገብ ላትጻፉ ዘንዳ>> ቢላል ከንጋት ቀድሞ አስነስቶን ተግሳጹን እየለገሰን ነው። ቢላል ስለ ያስሚን ቢያውቅ ያዝንብኝ ይሆን? ወይስ ያንን ውብ ፈገግታውን አሳይቶኝ ያልጠበቅሁትን መልስ ይሰጠኛል?።

ቢላል የጎጆውን ሰራተኞች በሙሉ የአሏህን ቃል የማስተማር እቅድ አውጥቶ በፍጥነት ተግባራዊ አደረገው።እኔም የቻልኩትን ያህል አግዘዋለው። እስከ ቁርስ ሰዐት ድረስ ከተማማርን በኋላ ከመብላታችን በፊት ወርቃማ የረሱልን [ሶላት እና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን] ንግግሮች ሁለት ③ቱን ያስታውሰናል።

<<አሏህ የማንኛችሁንም ውጪያዊ ገጽታ፡ ሐብት እና ውበት አያይም።ይልቁንም አሏህ ወደ ልቦቻችሁ ይመለከታል>> ነበር መጨረሻ ያሰማው ነብያዊ መልዕክት።

በዝምታ ቁርሳችንን ከበላን በኋላ ወደ ሰፊው አውድማ አንድ በአንድ አመራን። ወደ መውጪያው ስነሳ ነበር ቢላል ያናገረኝ <<ሐሰኔ ቆይ ጠብቅ መጨረሻ እንወጣለን>>

<<ለምን እንዴ?>>

<<የአንድ ስብስብ አሚር ከኋላ ሊሆን እንጂ ከፊት ሆኖ ሊኾፈስ አይገባውም! አሚርነት ሓላፊነት እንጂ ብልጫነት አይደለምና>>

<<ካልክ እሺ> >ብዬው እይታዬን ገርበብ ባለው በር በኩል አሳልፌ የጃስሚን መስኮት ላይ አሳረፍኩ።የፋኖስ ብርሃን አይታይም፡ ፀሃይም ክንዷ አልጠነከረም።የጣውላው ቤት ነዋሪያን ከእንቅልፋቸው የተነሱ አይመስልም ነበር።

ከሰፊው አውድማ ላይ ስንደከም ዋልን።እኩለ ቀን ላይ ሁሉም ሰራተኞች ተሰብስበው በቢላል ኢማምነት ሲሰግዱ መንፈስ የሚያድስ ትዕይንት ይስተዋል ነበር።ወደ ጎጆዋ ቤት ተመልሰን ምሳችንን ከበላን በኋላ ግዜ ሳላጠፋ ወጣሁ። ያስሚንን ባያት ደስ ይለኛል። እነ ሻህ ሱፍያን ቤት ውስጥ ባይኖሩ ደሞ እፈነጫለሁ።

ሻህ ሱፍያን እና እመቤቲቱ ተጠጋግተው ቁጭ እንዳሉ ከከበርቴው ጎን የተነከረ ብዕር እና የተጠቀለለ የቆዳ መጻፊያ ይታያል። << ግባ ግባ ሀሰን ስንፈልግህ መጣህ አሉኝ> > ከባለቤታቸው ላይ አይናቸውን እየነቀሉ። እናትዬው ቀጠሉ << አረብኛ መፃፍ ትችላለህ እንዴ ሀሰን?>>

ቆፍጠን ብዬ መለስኩላቸው <<አዎን ኡማህ በሚገባ >>

<< አ ሃምድሊላህ ማሻአሏህ ያ ወለድ>> የሻህ ሱፍያን ፊት ሲበራ አየሁት።ከፊታቸው ጮራ ጋር የጥንቱን የሲፊን መንደር መድረሳዬን አስታወስኩት። የሚያስተምሩን ሽማግሌ ኡስታዝ የሂልዋ ወንድም እንደሆንኩ ካወቁ በኋላ ከሌሎች ተማሪዎች ለይተው ይንከባከቡኝ ነበር።<<ምናልባት ወንዱ ሁመይራእ ቢሆንስ>> ይሉ እንደነበር ታወሰኝ።

<< ና እንጂ ምነው ፈዘዝክ አሁን የምነገርህን ቃላት አሳምረህ ታሰፍራቸዋለህ>> አሉኝ ሻህ ሱፍያን በቀኝ በኩል ቦታቸው እየጠቆሙኝ። <<ቁርስ በደንብ በልተሃል ግን>> እመት አሚናህ ናቸው..... እናቴን ወለሉ ላይ ትቼአት ከመጣሁ በኋላ የምወደውን ቁርስ አልበላሁም! <<አዎ በልቻለሁ ኡማህ>>።

❦

ለግማሽ ሰዐት ያህል የወዳጅ ደብዳቤውን ስሞነጫጭር ቆይተን መቋጫው ላይ የደረስን መሰለኝ። ሻህ ሱፍያን የሚወዱት ወዳጃቸው ይመስላል << በአሏህ ፍቃድ በቀጣዩ ወር መባቻ መጥቼ እጎበኛሃለው።ያንተው የልብ ወዳጅ ሻህ ሱፍያን>>።

ጽሁፉን በድጋሚ እያረምኩ ሳለ ነበር ከውጪ በኩል ወደ በሩ የሚጠጋ የፊረስ ኮቴ የተሰማው። << መልዕክተኛው መጥቷል መሰለኝ >> ብለው እመቤቲቱ ብድግ አሉ።

ከፊትለፊታችን የቆመው መልዕክተኛ የቀሳውስት የሚመስል ከፍ ያለ ቀይ ቆብ እና ቀይ ሱሪ እስከ ጉልበቱ በሚደርስ ቀሚስ ያደረገ ነበር። በጎን ወገቡ ላይ የታጠቀው ጎራዴ የጥንቶቹን ጦረኛ የንጉስ ዘቦች ያስታውሳል። የተጻፈውን ደብዳቤ ጠቅልሎ ከኪሱ ካስገባት በኋላ እጅ ነስቶ ወደ መውጪያው ለማምራት አኮበኮበ። ሻህ ሱፍያን ጠየቁት <<አንተ ሰው ደብዳቤው መቼ ይደርስልኛል?>>

<< በፈጣሪ ፍቃድ ከሳምንት በኋላ ይደርሳል ጌታዬ።የሚዘገየው ዛሬ ወደ ኢራን ስለማመራ ነው>> ብሎ የመውጪያ ፍቃድ መጠባበቅ ጀመረ።

< ኢራን > የሚለውን ቃል ስሰማ ቅጽበታዊ ውጋት ውስጤን አናወጠው። ፊቴ ሲቀላ ታወቀኝ። መልዕክተኛው የሂልዋዬን እና የፊርሃንን ምድር ሊረግጥ የኡሚን እና የባባን መቃብር ሊያልፍ ነው።

ሻህ ሱፍያን የምስጋና ፊት እያሳዩት <<እሺ ሷሂብ አሏህ በሰላም ይመልስህ>> አሉት። <<ሐሰን አንተም ወጣ ማለት ትችላለህ ዛሬ ወሳኝ ሥራ ነው የሰራከው አስደስተከኛል>>.....በበሩ በኩል ፈጥኜ እየወጣሁ ሳለ መልዕክተኛው የፈረሱ ጀርባ ላይ ለመፈናጠጥ እግሮቹን እያነሳ ነበር.....

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

ክፍል ①⑧ ይቀጥላል.....⸗★

★⸗★⸗❦የኮንያ አበቦች ክፍል ①⑧

✍@Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ

ህይወት አርንጓዴ ወዛም ብትመስለኝ
እጇን ስዘረጋ መከራ ነደፈኝ

ሻህ ሱፍያን የምስጋና ፊት እያሳዩት <<እሺ ሷሂብ አሏህ በሰላም ይመልስህ>> አሉት። <<ሐሰን አንተም ወጣ ማለት ትችላለህ ዛሬ ወሳኝ ሥራ ነው የሰራከው አስደስተከኛል>>.....በበሩ በኩል ፈጥኜ እየወጣሁ ሳለ መልዕክተኛው የፈረሱ ጀርባ ላይ ለመፈናጠጥ እግሮቹን እያነሳ ነበር.....

ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም።በደመነፍስ ወደ ጎጆው ቤት አመራሁ፡ ቢላል አለቃ ከሆነ በኋላ ጎጆዋ ውስጥ እረፍት የሚወስዱ ሰራተኞች አይጠፉም።ከቢላል መቀመጫ አጠገብ ነጭ ወረቀት እና መፃፊያ ይገኛ በፍጥነት መልዕክተኛው ላይ ለመድረስ ወጣሁ። ትልቁን የውጪ በር ከፍቼ በረርኩ.... በቀጭኑ አቧራማ መንገድ ላይ አቧራው ከፍ ብሎ ይቦን ነበር።③⓪ እርምጃ ርቀት ላይ መልዕክተኛው ከፈረሱ ላይ ተቀምጦ አንድን ሰው እያነጋገረ ነበር.....ሩጫዬ የጥንቱን የካይት ውድድር አስታውሶ አጠነከረኝ <<ሷሂሂብ አንዴ ጠብቀኝ>> እያልኩ ከነፍኩ።አጠገቡ ስደርስ ለመፈርጠጥ እየተዝጋጀ ልጓሙን እያፍታታ ነበር <<ሷሂብ ሷሂብ አንዴ ቁምልኝ እባክህን>> አልኩት እያለከለኩኝ።

ከፈረሱ ጀረባ ላይ ተኮፍሶ ወደ ታች አፈጠጠብኝ። <<ሷሂብ እባክህን አንዲትን መልዕክት ከኢራን ምድር አድርስልኝ እባክህን> > ።ልመናዬን እንደሰማ በንቀት እይታ እየነነተለኝ ልክ እንዳልሰማ ሰው ለመሄድ ገመዱን ለቀቅ አድርጎ በዝግታ መጋለብ ጀመረ።

በዚያች ቅጽበት ሆድ ባሰኝ የእንባዬ ፍጥነት ከፈረሱ ኩቴዎች ይቀድማል <<ሷሂብ እባክህን ኢራን ውስጥ የምናፍቃቸው እህቶች አሉኝ። በምላሹ የፈልግከውን እሆንልካለሁ>>

መልዕክተኛው ሲያሽካካ ይሰማል <<ከናንተ ደሞ ምን ይገኛል ሃ ሃ ሃ>>።

ያለኝን ሃይል አውጥቼ እንባ በተናነቀው ጩኸት አንቧረቅኩበት <<ጨካኝ ነህ ጨካኝ እህት የለህም? የምትወደው ሰው ናፍቆት ህመም ሆኖብክ አያውቅም?>> እጇን እያወራጨው ነበር። <<አንተ ምናልባት ከጉዞህ መልስ የእናትህ ሙቅ እጆች ይዳብሱህ ይሆናል እኔ ግን የሚዳብሰኝ የእናት እጅም ይሁን የሚያጠነክረኝ የአባት ምክር አልታደልኩም! ጨካኝ>>።

ተስፋ በቆረጠ የኮሰሰ አካሄድ ዞር ብዬ ሁለት እርምጃዎች እንደሄድኩ ከኋላዬ ድምጽ ሰማሁ።ነገዴውን መዞ ሊቆራርጠኝ ቢሆንም ግድ የለኝም። <<ያ ወለድ ይቅርታ። ደብዳቤህን አደርስልሃለው አቀብለኝ>>። ዞር ስል ከአናቴ በላይ እንደደመና እያንጎበበ ነበር።የሰማሁትን አላመንኩም። አቧራማው መንገድ ላይ በጉልበቴ ተደፋሁ <<እሺ እሺ ሷሂብ ይኸው ልፃፈው በጣም አጭር መልዕክት ነው ታገሰኝ>> አልኩት እንባዬን እየጠራረግሁ።

አፈር የሚንሸራሸርበት ወረቀት ላይ መሞንጨር ጀመርኩ <<ሂልዋኒ ሰላም አለይኩም ። ሐሰን ጃን ነኝ ያንቺው ውድ ትንሹ ሐሰን። አለሁልሽ አልሞትኩም እህቴ። ይህንን ደብዳቤ እንዳየሽው ከእቅፍሽ አስገብተሽ አሙቂው ።እኔ ባላቅፍሽም ብዕሬ ያንቺን እቅፍ ያግኝ ከአንድ የሩቅ ምድር ላይ ሆኜ ሁሌም አስብሻለሁ ። የናፍቆት ሰላምታዬን ለፈርሃንም አድርሺልኝ እወድሻለሁ!>> እንባዬ እወድሻለሁ የሚለውን ቃል አርጥቦ አበላሸብኝ።አጠገቤ የቆመው ፈረሰኛ <<አፍጥነው ያ ወለድ> > ሲለኝ ወረቀቱን አጥፌ ላቀብለው ተነሳሁ....በድጋሚ ወረቀቱን ፈትቼ አንድን ቃል ጻፍሁ <<አዎ እወድሻለሁ>>።

<<አመሰግናለሁ ሷሂብ>> ። የመጨረሻ ንግግሩ ነበር <<ኢራን የትኛው መንደር ውስጥ ናት እህትህ?>>
<< ሲፊን ሲፊን የካይት መሸጫዎች የሚበዙባት መንደር። ለአንደኛው ባለሱቅ እናቷ ለሞተችባት ሂልዋ አድርስልኝ ብለህ ስጠው> > አልኩት ከአቧራው ውስጥ ኮስታራ ፊቱ ፈንጥቆ እየታየኝ። ትርክም ትርክም የሚሉ የፈረስ ኩቴዎች ተከተሉ.....ብቻዬን ቀረሁ።

❦

መጻፊያውን ከጎጆው መልሼ ወደ ቢላል ሰፊ አውድማ ሳመራ የተፈጠረው ሁሉ ህልም እየመሰለኝ ነበር።ከመውጪያው በር በኩል የለመድኳትን የያስሚን መስኮት ሳማትር ያቺን ቀይ ጃስሚን አየኋት። አይን ለአይን ስንጋጭ የማልችለውን ፈገግታዋን ጥላብኝ ተሰወረች። የዛሬውን ትዕይንት አሻግራ አይታ ይሁን?

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

🎈ክፍል ①⑨ ይቀጥላል.....彡★彡★

★彡🌹የኮንያ አበቦች ክፍል ①⑨

✍Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ
ተስፋን ብሰንቃት ደስታን ፈላልጌ
ነገ ና አለችኝ በጣዕር ተጠፍንጌ

🎈 ከ② አመታት በኋላ፡ኮንያ

አመታቶች አለፉ። በርካታ ነገሮች እንደተቀየሩ አስተውያለሁ።የነጆዋ ቤት ግን በእርጋታ ከተተካው ጫጫታዋ ሌላ ያው ፍጥረታት እንደታነሩባት ነው። አዎ ቢላሌ ልቀይር ካለ ዐለምን ይቀይራል። የተቆጣ ሞገደኛ ውቅያኖስን ያባብላል።

ጃስሚኔ አሁንም አለችልኝ።የህይወትን አሊፍ ባ እንዳስተማረችኝ መች ይሆን የምነግራት?።እህቴም ውድ የነፍስ መጠግያሜ ናት ። ለ ዐመታት በድብቅ ፍቅር ውስጥ ማንም ሳያውቅብን እንዳሳለፍን ሳስተውለው ብርድልብሴ ውስጥ ሆኜ አፌን እከፍታለሁ።በቱርክ ህይወቴ እርግጠኛ ሆኜ የማወራው የቢላልን ንጹህነት እና የጃስሚንን ፍቅር ብቻ ነው።

እመት አሚናህ እና ባለቤታቸው መጠነኛ ድካም ይታይባቸዋል።እቤታቸው ስደርስ እመት አሚናህ ከላያቸው ላይ የቱርክ እናቶችን ሸማ ጣል እያደረጉ ነበር።
<<ሐሰኔ ዛሬ ባክህ አንድ ወዳጃችን በጠና ታሞ ልንጠይቀው እየሄድን ነው ትገባለህ ወይስ ውጪ ትሆናለህ>> አሉኝ።
ጃስሚንን ካየኋት ሳምንት አልፎኝ ስለነበር ውስጥ መሆኑን መርጬ ወደ ውስጥ ገባሁ።ሻህ ሱፍያን በጥቁር ቀለም የተነከረውን ከዘራቸውን አቀላጥፈው እየያዙ <<አንበሳው ዛሬ ልናረፍድ እንችላለን።የእርሻውን ሰዎች ነቃ አድርጋቸው ከሻህ ሱፍያን እንደተላክህ ስለሚያውቁ ሲያዩህ ድካማቸው ነው የሚለቃቸው> > አሉኝና ቅንጣት እዝነት ጠብ ያለበት እይታ ቸረውኝ መልሴን ሳይጠብቁ ከቤቱ ወጡ። የእርሻው ተቆጣጣሪ ከሆንኩ አመት አልፎኛል።

ጃስሚኔ ብትመጣ ብዬ እየተመኘሁ ከመጅሊስ ዳር ላይ ወደ ደረጃው እይታዬን ዘርግቼ ቁጢጥ አልኩ።....ያቺን አበባ ለደቂቃዎች ብጠብቃትም አልመጣችም ፡ምናልባት ከፍሏ ውስጥም የለችም ይሆናል ብዬ ወደ እርሻው ለመሄድ ተነሳሁ። ሳላስበው ብዙ ሰዐት ያቃጠልኩ መሰለኝ።

የበሩን እጀታ ልስበው ስል ነበር የጃስሚንን ኩቴዎች የሰማሁት።ባለሁበት እንደቆምኩ ከኋላዬ መጥታ ወገቤን አቀፈችኝ።
<<እኔ ስመጣ ነው እንዴ ምትሄደው አንተ ሰውዬ> > ፊቷ ጀርባዬ ላይ ይሞቃል።
<<አንቺስ ልሄድ ስል ነው እንዴ የምትመጪው> >
እጆቿን እያስለቀቅኋት አይኖቿን ለማየት ዞርኩኝ። ቡኒ አይኖቿ ወደ ቀይ አድልተው ያለቀሱ ይመስላሉ።ልክ አይኔን ስታየኝ አጎነበሰች።
<<ጃስሚኔ ምንድነው እሱ የተፈጠረ ነገር አለ እንዴ??>>
ዝም ስትለኝ ነበር ጉንጯን በእጆቼ ከፍ አድርጌ አተኩሬ ያየኋት። ፊቷ ይናገራል <ልሄድብክ ነው> ሲለኝ እየሰማሁት ነው ልሳኗ ቢደብቀኝም።<< ጃስሚ ተይ አታስጨንቂኝ የተፈጠረውን ንገሪኝ>>ስላት አይኖቿ እንባ ማቅረር ያዙ። ደነገጥሁ። ከውጪ በር የሚሰማውን የሰራተኞች የእረፍት ጋጋታ ስሰማ ሳልፈልግ ልሰናበታት ሆነ <<እሺ በቃ ስንገናኝ እናወራለን እባክሽን እንደዚህ አትሁኚ እሺ>>
በመጨረሻ አወራች << እሺ ማታ ግን ምናልባት በሰው ላስጠራህ እችላለው ኡሚ የሆነ ቦታ ስለምትልከኝ ከሀሰን ጋር ልሂድ ብዬ አስፈቅዳታለሁ>>

<<እሺ እሺ ቻው አሁን ግን እያየሁሽ ሳቂ >> እጆቿን ይዤ ነበር? ስለቃቸው በቀኗ ጸሓይ ሥር በረደኝ። ፈገግታ ሀዘኗን ሰንጥቆ ሲወጣ የደስታን ሃያል ክንድ ቀመስኩት። <<ሰላም አለይክ ሀሰኔ >>።

❦

ስለያስሚን እያሰብኩ በአውድማው ላይ በትካዜ ዋልሁኝ።ቢላል ቁዘማዬ ግራ ገብቶት በየደቂቃው <<እርግጠኛ ነህ ምንም አልሆንክም>>ሲለኝ ነበር።እኔ በሃሳብ ሰራተኞች በጉልበት ፈረስ ስንጋልብ ውለን ምሽቱን በጎጆአችን ሥር ተኮለኮልን።

<<ዛሬ የእረፍት ቀናችሁ ነው።የተማርናቸውን ነገሮች በእነደዚህ አይነት አጋጣሚዎች ላይ ተግባራዊ እናድርጋቸው> > አለ ቢላል ፊቱን ወደኔ እየመለሰ።ጎጆዋ የፍቅር ኩራዞች ተለኩሰውባታል ።የሚደባደቡ እና የሚነቋቆሩ ፍጥረታት በሚጎራረሱ የአይን ወዳጆች ተተክተዋል።

የቢላል ድምጽ አነቃኝ< <ሐሰኔ ስለ አንድ ንጉስ ታሪክ ልንገርህማ>>
ያደፈውን ጠንካራ ትራስ በቀኝ ክንዴ ደገፍ እያልኩ እሺታዬን አሳየሁት...

...< <በድሮ ግዜ አንድ ግዛተ ሰፊ ታዋቂ ንጉስ ይኖር ነበር።ታዲያ ይህ ንጉስ ከዝርጥጥ ግዛት እና ሺህ አሽከሮች ባለፈ ልቡን የምትጠግንለት የአይን ማረፊያ ሚስት አልነበረውም።

አንድ ቀን ወደ ጥቅጥቁ ጫካ ለአጋዘን አደን አንደኛውን አሽከሩን አስከትሎ ይወጣል...>>

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

❦

❦ክፍል ②⓪ ይቀጥላል....ᨒ★

★ᨒ❦የኮንያ አበቦች ክፍል ②⓪

✍Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ

የቢላል ድምጽ አነቃኝ< <ሐሰኔ ስለ አንድ ንጉስ ታሪክ ልንገርህማ>>
ያደፈውን ጠንካራ ትራስ በቀኝ ክንዴ ደገፍ እያልኩ እሺታዬን አሳየሁት...

...< <በድሮ ግዜ አንድ ግዛተ ሰፊ ታዋቂ ንጉስ ይኖር ነበር።ታፊያ ይህ ንጉስ ከዝርጥጥ ግዛት እና ሺህ አሽከሮች ባላፈ ልቡን የምትጠግንለት የአይን ማረፊያ ሚስት አልነበረውም።

አንድ ቀን ወደ ጥቅጥቁ ጫካ ለአጋዘን አደን አንደኛውን አሽከሩን አስከትሎ ይወጣል።ከብዙ ድካም በኋላ ከኋላው በኩል የቅጠል ኩሽኩሽታን ይሰማና ቀስቱን እየለጠጠ በፍጥነት ይዞራል። የተመለከተው ግን የዱር ኢጋዘንን ሳይሆን አንዲትን መልከመልካም ጎስቋላ እንስትን ነበር። በመጀመሪያ እይታው ከሴቲቷ ጋር ፍቅር ይዘውና ወደ ቤተመንግስቱ ይዟት ይሄዳል።>>

< <ሐሰኔ እየሰማከኝ ነው አይደል>> አለኝ ንቃቴ ላይ ንቃትን እየጨመረልኝ።
<<አዎ አዎ በናትህ አታቋርጥ አጉተ ደሞ> >።
<<እሺ እ.....>> የጎጆው ቤት በር ሲንኳኳ ሁለታችንም እኩል ተያየን።
<<ምነው ደነገጥክ ሐሰን?>>
<<እንዴ አንተምኮ ደንግጠሃል>>
<<እኔማ ንጉሱ ለሰርግ ሊጠራን የመጣ መስሎኝ ነዋ>> አለኝ በር ከፋቹን ሰራተኛ በፈገግታ ምልክት እየሰጠው።
<< አው ጫካው ውስጥ ያገኛትን ሴት ሊያገባት ነው ማለት ነው >> አልኩኝ በአግራሞት አፌን እየያዝኩኝ።

ቢላል በሩ ጋር ቆሞ ለደቂቃዎች ካወራ በኋላ ተመለሰ። <<እ ቢላሌ ምንድነው ነገሩ>> ስለው <<ሂድ አንተም ተፈልገሃል እንዳትቆይ ምናወራው ነገር ይኖረናል>> ብሎኝ አንገቱን ደፍቶ ተቀመጠ። ቢላል ያዘነ ይመስላል። እባክህን አትዘን.....አንተም ጀስሚኔም በአንድ ቀን ካዘናቹብኝ ሌላ የማን ፈገግታ ቀረኝ?.....እስከመውጪያው ድረስ እሱን እሱን እያየው ነበር ።

❦

የእንጨት በሩ ሥር በጭለማው ተሸፍና ቆማ እጆቿን ታወናጭፋለች።ያስሚን።ያስጠራኝ መልዕክተኛ ወደርሷ እያመለከተኝ ከኋላዬ ቆሟል። አጠገቧ ደረስኩ <<አየህ ቃሌን አላጠፍኩም አገኝሃለው ብዬህ አልነበር? >> አለችኝ በአይኖቿ ሰላምታ እየቸረችኝ። <<እሺ እንውጣ መሸቷልኮ ቶሎ ደርሰን እንምጣ>>
<<ምነው ከኔ ለመለየት ቸኮልክ እንዴ>> ብላኝ በዝምታ መጓዝ ጀመረች።ኩርፊያዋ ጨለማውን ይባስ አደቅድቆታል። ከጥቂት ግዜያት ወዲህ በሆነው ባልሆነው ማኩረፍ ጀምራለች ።
እያንሾካሾኩኝ ነበር <<ስሚኝማ ጃስሚናህ ከኋላችን የሚከተለን ሰውዬ ባይኖር እቅፍ አድርጌ እቆነጥጥሽ ነበር> > ...
በትንፋሾቿ ቀስ ያለ ሳቅ ስትስቅ የሲፊንን ንጋት አስታወሰችኝ ። እወድሻለሁኮ ብላት ብዬ ተመኘሁ. .....እጆቿን ይዤ የፍቅሬ ሰራዊት ከቱርክ ሻሂ ቅጠሎች እንደሚበረከቱ ብነግራት አልሁኝ።
<<ሐ ሐሰን>> አለችኝ ፈራ ተባ እያለች ።
<<ምንድነው እሱ የምትነግሪኝ ነገርማ አለ>>
<<እ ሰሞኑንኮ ባባ እ እ>>
<<ባባ ምን? >> ፍርሃቷ እኔም ላይ ተጋብቷል።
<< ባባ ሊድረኝ ነው።። ሰሞኑ ወሬው ሁሉ ስለሰርግ ሆኗል > >

እግሮቼ አካሄድ እየጠፋባቸው የምረግጠው ምድር ታች ርቀት ላይ የተዘረጋ መሰለኝ።ንግግሯ ቅንድብ የሚልጭ አስደንጋጭ ነበር።ልቤ የፍርሃት ከበሮዋን ስትደልቅ ልሳኔም ተኮላተፈች <<ምምን ምንድረው ምታወሪው ..... ኸረ ባባ አይድርሽም አዎ ኡማህም አትፈቅድለትም>>
በጭለማው ሽፋን አይታይም እንጂ የእንባ ዘለላዎች መንታ መንታ ሆነው ከአይኔ ሥር እያመለጡ ነው። <<ለምን ዝም ትዪኛለሽ አንድ ነገር በይኝ እንጂ>>
ድምፄን ከፍ ስላረግሁ ከኋላችን በትንሽ ርቀት ላይ የሚመጣውን ዘብ ጎንተል አድርጋ ተነፈሰች። <<ሐሰን ይሄ በዚ ሰዐት ሚወራ ነገር አይመስለኝም>> አለችኝ። ታዲያ ለምን ነገርሽኝ ጃስሚን አልኩኝ ለራሴ.....በዝምታ ከተላከችበት የከበርቴ ጎጆ ደርሰን በዝምታ ተመለስን. ....ስንለያይ ግን ቡኒ አይኗ ሲያወራኝ ነበር <እወድሃለው...ታስፈልገኛለህ>። <<ቻው በቃ ሰላም አለይኪ>> ብዬአት ወደ ጎጆዬ ዘለቅሁ።

ከቢላል የንጉሱ ታሪክ በኋላ ያለው ትዕይንት የኢራን ቲያትር እየመሰለኝ ማረፊያዬ ጋር ተቀመጥሁ።
<<መጣህ ሐሰኔ እንካ ያዝ ይህንን ደርብ ዛሬ ብርዱ ይቋረጣል >>አለኝ ፈገግታውን በጥርሶቹ ሥር ደብቆ።
<<ደሞ ምን ገጠመህ ፊትህ ጨልሟልኮ> >
<<አይ ደከሞኝ ይሆናል ባይሆን ያንተን ንገረኝ >>አልኩት በተሰላቸ ድምጸት።

<<እ ምን መሰለህ ሐሰኔ>> ከፍ ባለው መስኮት በኩል አመጸኛ ንፋስ ያፏጫል። ጨረቃን የጋረዷት ተንቀሳቃሽ ስስ ዳመናዎች በምሽቷ ንግስት ውበት የቀኑ ይመስላሉ። ቢላል ንግግሩን ቀጠለ << አሚር ሷሂብ ትዝ አለህ አይደል ሀሰን። እኔም በቃ እንደሱ ከዚህ ጎጆ. .....>>

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

🌹

🌹ክፍል ②① ይቀጥላል.....ⷮ★

★ⷮ🌹የኮንያ አበቦች ክፍል ②①

✍Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ

<<እ ምን መሰለህ ሐሰኔ>> ከፍ ባለው መስኮት በኩል አመጸኛ ንፋስ ያፏጫል። ጨረቃን የጋረዷት ተንቀሳቃሽ ስስ ዳመናዎች በምሽቷ ንግስት ውበት የቀኑ ይመስላሉ። ቢላል ንግግሩን ቀጠለ << አሚር ሷሂብ ትዝ አለህ አይደል ሀሰን። እኔም በቃ እንደሱ ከዚህ ጎጆ ሊያዘዋውሩኝ ነው መሰለኝ።በዚህ ①⑤ ቀን ውስጥ ሻህ ሱፍያን. . .>>
ሙሉ ንግግሩን መስማት አልሻም።<<በቃህ በቃህ ጠርጥሬ ነበር ድሮም ከናንተ ምን ይጠበቃል> > አልኩት። <<እኔ ምን አጠፋሁ ሐሰኔ :ደሞ እናንተ ለምን አልከኝ ሌላ ያስከፋህ ሰው አለ እንዴ? >>።

እናቷ እንደጠፋችባት ግልገል ቀና ብዬ የልምምጥ እይታዬን ስቸረው ፊቱን በእዝነት ረመጥ ስትጠበስ አየኋት ። <<እንዴ ሐሰኔ ልታለቅስ ነው እንዴ ና እቀፈኝ እስኪ>> ብሎኝ ከሰፊ ደረቱ መሀል ወሸቀኝ.....አነባሁ ምክንያቶቹ ሺህ ቢሆኑም እንባዬ ከመንታ አታልፍም።

<<ደሞ ሻህ ሱፍያንን ለማስረዳት እሞክራለሁ ፡በዛላይ የትም ብሄድ እንደማንረሳሳ ታውቃለህ መቼስ> > በታምቡሬ በኩል ጎርናና ድምጽ ለደቂቃዎች ተንቆረቆረ። በመጨረሻም ከእቅፉ ሥር ወጥቼ የውሸት ፈገግታዬን አሳየሁት።

<<ሐሰን> > አለኝ አሁንም ብቻውን እያወራ። << የወደድከ ግዜ ጥሎህ የማይሄደውን ውደድ።ፍጥረታትን ስታፈቅር ውዴታህን ከአይንህ አሳልፈህ ለልብህ ስጥ። የአይን ወዳጅህ ከእይታህ ሲርቅ በናፍቆት ይገድልሃል። የልብ ወዳጅ ግን ዝንተዐለም ካንተ ጋር ይኖራል>>

ስለጃስሚን የሚያወራ መሰለኝ።እንደተረበሸኩ ሳያስታውቅብኝ በተስማማ ሰው አይነት አንገቴን ነቅንቄ <<በቃ ነገ እናወራለን እንተኛ> >አልኩት። የሌሊቱን ግማሽ በጭንቀት ውርጅብኝ ስወገር አሳለፍኩት.....ለቢላል ስለ ጃስሚን ልንገረው ወይስ በራሱ ግዜ ይወቅ?.....።

❦

ጠዋቱ ብርዳማ ነበር።ከሌሊት ስግደት በኋላ በዝምታ ለደቂቃዎች ጸሎታችንን አደረስን።የቱርክ ወፎች ጫጫታ አያልፋቸውም ፡እንደ ሲፊን አዝማሪ ወፎች ግን አያዜሙም። <<ሐሱዬ ተነስ እንጂ የኔ ጎበዝ አባትህ ገና ከመሄዱ ሰነፍክ እንዴ.....ና አብረን ቁርስ እንብላ የነሂልዋን እንጨርስባቸው>> የሚለው የኡሚ ዝማሬ ከየትኛውም ወፍ እንጉርጉሮ ይሻላል።

ዛሬ ከያስሚን ጋር ሐርማንቺክ ገበያ የምንወጣበት ቀን ነው።ወደሻህ ሱፍያን ጎጆ ለመዝለቅ እየተጣደፍኩ የቀረበውን ደረቅ ሩዝ እንደነገሩ ጎራርሼ ከደሳሳው ጎጆ ወጣሁ። ቢላል ትልቁ የእንጨት በር አጠገብ ከሻህ ሱፍያን አረመኔ አሽከሮች ጋር እያወጋ ነበር።እንዳላየ ሆኜ አልፌ ከነያስሚን የጣውላ ቤት ሥር ደረስኩ።

የእመት አሚናህን ወይኖች ተቀብዬ ያስሚን ከደረጃው እስክትወርድ መጠበቅ ያዝኩ።
<<ሀሰን ዛሬ በጠዋቱ የደከመህ ትመስላለህ ።ገበያ ለመውጣት ዝግጁ ነህ አይደል> >እመት አሚናህ ነበሩ።
<< አዎ አዎ ኡማህ አልደከመኝም እሄዳለሁ>>
ሻህ ሱፍያን ተከተሉ <<ማደሪያው ቤት ውስጥ ያልተመቸህ ነገር አለ እንዴ ሀሰን?>>
ቢላልን ከመነጠቅ በላይ ምን ስቃይ አለ? <<አ አይ ምንም ነገር የለም>> ሻህ ሱፍያን ይህንን ቤት የረገጥሁ ቀን የተናገሩኝ ትዝ አለኝ <ሐሰን ምንም ብትሆን የኔ ሰራተኛ መሆንክን እንዳትዘነጋ>። <<ጥሩ> > ብለው በዝምታ ቁጭ አሉ።

ከደቂቃዎች በኋላ ባዶ ዘንቢል ያንጠለጠለችው ጃስሚን ቡናማ ቀሚሷን በወጉ በተጠመጠመ ሂጃብ ለብሳ ከደረጃው ወረደች።የሚገዛዙትን አትክልቶች ከእመት አሚናህ ጋር ካወሩ በኋላ እመት አሚናህ ከጎን የድብቅ ኪሳቸው ሥር የተጣጠፉ ብሮችን አውጥተው ሰጧት። <<ብሩን ለሀሰን ስጪው እስኪ እንዳትጥዪው...ውጡ ደሞ ጸሃዩአ ሳትበረታባቸሁ>>።ገንዘቡን ስታቀብለኝ አውርተን የምናውቅ የምንተዋወቅ ሰዎች አንመስልም ነበር።እኔ አጎብዳጅ አሽከር.....እሷ ቀብራራ የሻህ ሱፍያን ኮረዳ የገበያውን ጋሪ እስክንሳፈር ድረስ እንደዛው ነበርን።

ከቅጥረኛው ፈረሰኛ አሚን ጋሪ ከወረድን በኋላ በነጻነት ማውራት ጀመርን።
<<ሐሰን>>
<<ለበይኪ ጃስሚን> >
<<እ ምን አሰብክ ግን>> ስትጨነቅ ይበልጥ ውብ ናት
<< የሆነ መላ መፍጠር አለብን>> ..... እጇን ይዛኝ ወደ ማላውቀው ቅያስ እየወሰደችኝ ነበር <<ኸረ መንገድ ተሳስተናል...>>
<<ኡሸሸ ዝም በል ባይሆን ቶሎ ቶሎ በመራመድ ተባበረኝ> > ብላኝ ከፊት ከፊት ሆና እንደ አሚን ጋሪ ጎተተችኝ። አምናታለሁ....የምትወስደኝ ቦታዎች ሁሉ የውበት ፍንጣሪዎች ናቸው።

ከአንድ ሰፊ የድንጋይ ንጣፍ ቅያስ ላይ እንደደረስን አይኔን እንድጨፍን ነገረችኝና ይዛኝ በዝግታ መራመድ ጀመርን። <<አሁን አይንህን ክፈት> > ስትለኝ ቀስ አድርጌ መክፈት ጀመርኩ..... <አ አሏህ> አልኩኝ ከፊት ለፊቴ የቆመውን ግዙፍ የጀላሉዲን አል ሩሚ ሐውልት ሳስተውል... ሁለት ስንዝር የሚረዝም ቢጫ ኮፊታ አጥልቆ ዙሪያውን የሚሸከረከር ኮብላይ ሽማግሌ ይመስላል..... <<ሩሚ ነውኮ ሀሰኒ የሂልዋህ የእውቀት አባት> ... <አህ አዎ ሩሚ..>.....

ኮንያ የሩሚ ማስታወሻ ሐውልት ሥር

ክፍል ②② ይቀጥላል.....ኝ★

★ኝ❣የኮንያ አበቦች ክፍል ②② ✍Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ

ከአንድ ሰፊ መታጠፊያ ላይ እንደደረስን አይኔን እንድጨፍን ነገረችኝና ይዛኝ በዝግታ መራመድ ጀመርን። <<አሁን አይንህን ክፈት> > ስትለኝ ቀስ አድርጌ መክፈት ጀመርኩ..... <አ አሏህ> አልኩኝ ከፊት ለፊቴ የቆመውን ግዙፍ የጀላሉዲን አል ሩሚ ሐውልት ሳስተውል... ሁለት ስንዝር የሚረዝም ቢጫ ኮፈታ አጥልቆ ዙሪያውን የሚሽከረከር ኮብላይ ሸማግሌ ይመስላል..... <<ሩሚ ነውኮ ሀሰኒ የሂልዋህ የእውቀት አባት>> <<አዎ አውቄዋለሁ >> አልኳት እንግዳ ስሜት ልቤን እየኮረኮረኝ። <<ቆይ እስከዛሬ እንዴት አላመጣሽኝም> > << ወደ ግዙፉ የሩሚ ሃዋርያዎች መድረክ ልወስድህ ነበር ግን ሌላ ቀን ይሻለናል ይረፍድብናል>> ብላኝ ወደ ገበያ ጉዞአችንን እንድንቀጥል በአይኗ ምልክት ሰጠችኝ።

ከፊት ለፊቴ የቆመውን የሩሚ ሐውልት እየተሰናበትኩ ጫጫታ ወደበዛበት የሃርማንቺክ ጎዳና ጉዞአችንን ቀጠልን።ለደቂቃዎች ሁለታችንም አላወራንም ነበር።ያስሚን ፀጥታውን አደፈረሰችው
<<ምነው ደስ አላለህም እንዴ?>>
<<ኸረ ደስ ብሎኛል ሂልዋ የሩሚን ሐውልት ብታየው ምን ያህል እንደምትደሰት እያሰብኩ ነበር> >
<<እህትህን በጣም እንደምትወዳት ያወቅሁት ያኔ ለመልዕክተኛው ደብዳቤህን ለመስጠት አፈር ስትቅም ያየውክ ቀን ነው>> በስስ አይኖች እያየችኝ <<እንደ ሂልዋ የምትወደው ሌላ ሰው የለህም ሀሰኒ>> ስትለኝ የላብ ነጠብጣቦች ግንባሬን ሲያቀዘቅዙት ተሰማኝ። <<እ እ አለኝ በጣም የምወዳት ውብ እንስት አለች፡ ደስታዬን ከፈገግታዋ ሥር የምሸምትባት የኮንያ አበባ>>
<<ማናት ስሟን ንገረኛ> > አለችኝ በአንደበቴ አውጥቼው የማላውቀውን የተዳፈነ ፍቅር በጆሮዋ ለመስማት እየጓጓች። ምን ያህል እንደምወዳት እንደምነግራት ለአፍታ አስቢው ቄንጠኛ የኢራን ቃላቶችን መራርጬ አፌን ከመክፈቴ አንድ በውሃማ ፊስታል ቀያይ እንጆሪዎችን የያዘ ነጋዴ ትከሻዬን እየመታ< < ቅመሱት በጣም ጣፋጭ ፍሬ ነው ትወዱታላችሁ> > ብሎ በመከራ የተገነባውን የሃሳብ ቤታችን አፈራረሰው። ያስሚን ፊቷ ተጨማደደ <<አባባ አንፈልግም ሹከረን> > ስትላቸው በቆሪጥ አይቼአት ፈገግ አልኩኝ። <<ግማሽ ኪሎ ይስጡን እንጂ አንቺ ደሞ እዩው እስኪ ቅላቱ ብቻ ይበቃልኮ> > .....።
❣
ኢንጆሪዎቹን እና የተባልናቸውን ፍራፍሬዎች ሸማምተን በዝምታ ወደ አሚን ጋሪ እየተመለስን ነበር።ጸሃዩኣ በአናታችን ላይ ሰፍራ ጉዳዷን ትለቃለች።ያስሚን እንደደከማት ታስታውቃለች። <<አንዴ እዚው ጠብቂኝ> > ብዬአት ፈንጠር ብሎ ካለው ፍራፍሬ ነጋዴ ደማቅ የተገመሰ ቀይ ሐብሐብ ገዝቼላት መጣሁ።
<< ይሄን ስትገምጪበት ድካምሽ ይለቅሻል የኔ ሚጢጢ>>
<<እንኳን ማን ግዛልኝ አለከ>> እናቱ ያረፈደችበት ሕማን ትመስላለች
<<አሃ አትፈልጊም በቃ እኔ ልብላዋ> > ብዬአት ወደ አፌ ሳስጠጋው ከመቅበት ተስፈንጥራ ቀማችኝ። ወደ ወገቧ እየደበቀችው <<አንተ ራስህ መልኬ በቃኝ ነገር ነህ> > ብላኝ ሳቅ አለች።

ከአንድ የገበያ ጥግ ላይ በሚረማመዱ ገብያተኛ እግሮች ሥር ቁጭ ብለን ሃብሃባችንን በልተን ተነሳን። ስንርስ የነበረው በያስሚን እጅ ስለነበር አፈን የህፃን ልጅ አስመስላዋለች። <<ቅድም ግን ለምን መልኬ በቃኝ ነህ አልሽኝ?>> አልኳት ከተቀመጥንበት የሰላጣ ክምር ላይ እየተነሳን። <<ስለሆንክ ነዋ ። አባቴ እኔን ሊድር ይቋምጣል አንተ እዚ በሰላም ተቀምጠሃል>>
<<እሺ ምን ላድርግ ንገሪኝ እስኪ። አንዳንዴ የኔን ማንነት ትረሺዋለሽ መሰለኝ>> ስሜቴ ቦግ እንዳለ ታውቆኛል << ሐሰን ማለት ተራ ሰራተኛ ነው ሰማሽ! ምን እንዳደርግ ጠብቀሽ ነው ቆይ??>>.....ፈጠን ፈጠን ብዬ ቀድሜአት ወደ ሚጠብቀን ፈረሰኛ ገባሁ። ትንሽ ቆይታ እሷም ፊቷን እንደጣለች ተቀላቀለችን።

<<በሰላም ነው የቆያቸሁት ልጆች።ፊታችሁ ራሱ ከገበያ ሳይሆን ከጦርሜዳ መልስ ነው የሚመስለው>> አሚን ለመቀለድ ቢሞክርም ፈገግ ያሉ ፊቶችን አላገኘም። < <ትንሽ ደካክሞናል አሚን ሷሂብ ከቻልክ በፍጥነት ወደ ቤት አድርሰን>> ብዬ የውሸት ፈገግታዬን አሳይቼው ጉዞአችንን ቀጠልን።

ከኮንያ ድብቅ መንደራችን እስክንደርስ ዝምታ ሰፍኖ ነበር።ያስሚን በቀስታ እየተጠጋችኝ ጆሮዬ ሥር ታንሾካሹካለች <<እሺ በቃ ይቅርታ ሀሰኒ እኔስ ቆይ ያላንተ ማን አለኝ>> ዝምታን መረጥኩ።ውስጤ በረብሻ ሲናወጥ መች ይሰማትና።

<<ልጆች ውረዱ እንጂ ደርሰናልኮ >> የአሚንን ጥሪ እንደሰማን <<ነዋ እሺ ማታ እዛ ቦታችን ካልመጣክ ሁለተኛ ምታገኘኝ መስሎካል> > ብላኝ እየተነጫነጨች ወረደች ።

ምሽቱን በድብርት ኩሽኩሽ ብዬ ከቢላል አጠገብ ተቀምጫለሁ።ቢላል ከዚህ ቀደም ጀምሮልኝ የነበረውን የንጉስ ታሪክ እንዲቀጥልልኝ ጠይቄው በእሺታ ጉሮሮውን ጠራርጎ ጀመረልኝ።

<<ታዲያ ያ ታዋቂ ንጉስ እና ጫካ ውስጥ አይቷት የወደዳት ጎስቋላ ውቢት ድል ያለ ሰርግ ተደግሶላቸው አንድ ላይ መኖር ጀመሩ። ነገር ግን ከወራት በኋላ ያቺ ውብ ንግስት በጠና ህመም ታመሰች። ንጉሱም በሚስቱ ህመም ምክንያት በጭንቀት ተኮራመተ። በሀገሬው ለነበሩ ጠቢባን ሁላ <የባለቤቴን ጤና ለመለሰልኝ አንድ ሳጢን የወርቅ እና የከበሩ ድንጋይ ድልቦችን አበረክትለታልሁ። እኔ ዘንድም የቀረበ ባለሟል ይሆናል> ሲል ለፊፊ.....

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

❣ክፍል ②③ ይቀጥላል.....彡★

★彡❣የኮንያ አበቦች ክፍል ②③

✍Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ

<<ታዲያ ያ ዝነኛ ንጉስ እና ጫካ ውስጥ አይቷት የወደዳት ጎስቋላ ውቢት ድል ያለ ሰርግ ተደግሶላቸው አንድ ላይ መኖር ጀመሩ። ነገር ግን ከወራት በኋላ ያቺ ውብ ንግስት የጠና ህመም ታመመች። ንጉሱም በሚስቱ ህመም ምክንያት በጭንቀት ተኮራመተ። በሀገሬው ለነበሩ ጠቢባን ሁላ <የባለቤቴን ጤና ለመለሰልኝ አንድ ሳጢን የወርቅ እና የከበሩ ድንጋይ ድልቦችን አበረክትለታልሁ። እኔ ዘንድም የቀረበ ባለሟል ይሆናል> ሲል ለፊፊ። ንግስቷን ለማከም አሉ የተባሉ ጠቢባን ቢሰባሰቡም ንግስቷ ከቀን ቀን ህመሟ ይብስ ጀመር።

የገረጣውን የባለቤቱን ፊት ማየት ያላስቻለው ንጉስ በአንድ ማለዳ ላይ ወደ አሏህ ቤት ይሄድና ጌታውን አልቅሶ ይለምነዋል። ሚስቱን እንዲያሽርለትም ይማጸናል።በዛን ሌሊት ንጉሱ በህልሙ አንድን ጠና ያለ በእርጋታ የታጠነ ጠቢብ ወደ ቤተመንግስቱ ሲዘልቅ ያየዋል። በንጋታውም ይህንኑ ያለመውን ጠቢብ ወደርሱ ዘንድ ቀርቦ ያገኘዋል ። <<ሚስቴን ካሻርክልኝ የፈለግከውን አበረክትልሃለው።ከበታቼም እሾምሃለው> >ሲል ሊያጓጓው ሞከረ። ጠቢቡም መለሰ <ጥበብ ምላሽን አትፈልግም። መድሃኒትም በፈጣሪ እጅ እንጂ በሌላ አትገኝም። ይልቁንስ ሚስትህን ሰከን ወዳለ ሥፍራ በመውሰድ ለቀናቶች ብቻቸንን በመተው ተባበረኝ ።አንተም አብረኽን መሆን ትችላለክ>

ንጉሱ እንደተባለው ሐኪሙን እና ጎስቋላዋን ሚስቱን ይዞ ወደ አንዲት ሰላማዊ የቱርክ መንደር ይዘአቸው ገባ።በሀኪሙ ሁኔታ እጅጉን ግራ ተጋብቷል....እጁ ላይ ምንም መድሃኒት አይታይም።ቅጠላቅጠሎች የሚያስቀምጥባት ሳጢንም የለችውም።

ሐሰኔ ልብ ብለህ አዳምጥ በጠቢቡ እና በታማሚዋ ንግስት መሀከል የነበረው ምልልስ የንጉሱን ህይወት የቀለበሰ ነበር።

<አንቺ ሴት ንገሪኝ ምንሽን ያምሻል፡ ፊትሽ መገርጣቱ የአይንሽ መቅላቱ ማቃጠልሽ ምነው?>

ንግስቷ አይኖቿን ከማስለምለም ሌላ ምንም አትናገርም።

ጠቢቡም ከቀናት ጥያቄዎች በኋላ በአንደኛው ቀን እጁን በንግስቷ ደረት ላይ አድርጎ እንዲህ አላት።
< የተከበርሽዋ ንግስት ህክምናውን ሌላ ቀን ለማድረግ ወስኛለሁ።አሁን የምጠይቅሽን ጥያቄዎች ግን መልሺልኝ> >

ቢላል እየሰማሁት እንደሆነ ለማረጋገጥ አየት አድርጎኝ ሰብሰብ ብሎ ተቀመጠ ታሪኩንም አፈን ከፍቼ መከታተል ያዝኩ።ቢላል ከዚህ ቀደም እንደዚህ ረዥም ታሪክን ነግሮኝ አያውቅምና!

< ንግስት ሆይ ሃገርሽ ወየት ነው?>

<ኢራን> አለች በደከመ ድምጽ

<የትኛው ግዛት ውስጥ ተወለድሽ። ሰመርቀንድ ነሽ ዬራሳን ። ጢብሪዝ ነሽ ወይስ ቴህራን? አሊያም የቆንጆዎቹ ምድር ኒሻፑር ወይንስ ኢስፈሃን?>

<ኒሻፑር ነበር የተወለድኩት> አለች አሁንም በደከመ ድምጽ።

<ንገሪኝ እስኪ አ የየትኛው አዋቂ ልጅ ነበርሽ። የኒሻፑርን ጥበበኞችስ ታውቂያቸዋለሽ? ባላቅኔው ኡመር ኻያምን አስታወስሽው? አቡልወፋእንስ? ያንን የቡዝጃኒ ገጣሚ. . . . > ንግስቷ ለጠቢቡ ንግግሮች ምንም ምላሽ ሳትሰጥ ተንጋላለች። ጠቢቡም በመጨረሻ <ስመጥሩን ወርቅ ቀጥቃጭ ኢማሩልፋርስንስ አይተሽው ታዉቂአለሽ> አላት ። ንግስቷ ምላሽ ባትሰጥም የጠቢቡ ፊት ግን በዛው ቅጽበት ተቀያየረ። አጠገባቸው የነበረው ግራ የተጋባው ንጉስም< ምነው አንተ ሰው ፊትህ ልክ አይደለምኮ> አለው።

ጠቢቡም መለሰ <ንጉስ ሆይ ልሳንህን ብትዘጋም ልብህን መከርቸም አይቻልህም። ንግስትህ በወርቅ አቅላጩ መልከመልካሙ ኢማር ፍቅር ተነድፋለች። ከመሞቷ በፊት ወጣቱ እንዲመጣ ትዕዛዝህን አስተላልፍ።>

ንጉሱም እንዴት ይህንን እንዳወቀ በአግራሞት ጠየቀው።ጠቢቡም መለሰለት <ንጉስ ሆይ! እጇን በደረቷ ላይ አኖርኩት! የመድሃኒቷን ስም ስጠራላትም የልብ ምቷ ጣቶቼን አነዘራቸው። እሷ ባትናገርም ልቧ ወዳጁ ሲጠራ ነጋሪቱን ጎስሞባታል>

❦

በጠቢቡ ምልከታ ወጣቱ በእግር በፈረስ ተፈልጎ ከተገኘ በኋላ ወደ ንጉሱ ግዛት ተይዞ ቀረበ. . . . . ።

ቢላል በረጅሙ ሲተነፍስ ደሳሳዋ ጎጆም አብራው ተነፈሰች።ዞር ብዬ ሳማትር የጎጆው ሰዎች በታሪኩ ተመስጠው ዙሪያችንን ከበው ተቀምጠው ነበር።

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

❣ክፍል ②④ ይቀጥላል. . . . . ⸗★

★⸗❦የኮንያ አበቦች ክፍል ②④

✍ Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ

ቢላል በረጅሙ ሲተነፍስ ደሳሳዋ ጎጆም አብራው ተነፈሰች።ዞር ብዬ ሳማትር የደከሙ የስራ አጋሮቻችን በታሪኩ ተመስጠው ዙሪያችንን ከበው ተቀምጠው ነበር።

የቢላል ትረካ የስንብት ትመስላለች።እንድናውቅለት የፈለገው አንድ ምስጢረ ህይወት እንዳለም አነጋገሩ ያሳብቃል። ታሪኩን ቀጠለ

<<ይህ ወጣት ንጉሱ ዘንድ ተይዞ ከቀረበ በኋላ በንጉሱና ጠቢቡ ምክክር ከንግስቲቷ ጋር ከእይታ ሳይርቅ እንዲቆይ ተደረገ።ወራቶች አለፉ . . . .በዚህ መሀል ሀገረ ገዢውና ጠቢቡም ተግባቦታቸው ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ንግስቲቷም በወጣቱ ፍቅር የጠወለገው ፊቷ በየቅጽበቱ እየፈካ መጣ። በአንደኛው ማለዳ ንጉሱ ጠቢቡን አስጠርቶ እንዲህ አለው <አንተ የምድረ ቱርክ ጥበበኛ አሁን የሚስቴ ጤንነት ተመልሶላል በድጋሚ ከእቅፌ የማስገባበት መንገድ ምንድነው>

ጠቢቡም ጥቂት አሰላስሎ ተነፈሰ <ንጉስ ሆይ ሴቲቷን ከለግላጋው ወጣት ከለያየናት በድጋሚ መታመሟ አይቀርም፡ በሰልካካው ፊቱ ተማርካለችና፡ ልቧ የውበት እስረኛ ሆኗልና። ንጉስ ሆይ የወጣቱን ውበት የሚገሸልጥ ፡ፈርጣማ ገላውን የሚያመነምን መድሃኒት እንሰጠዋለን። ያኔ ውበት አፍቃሪዋ ትሸሸዋለች ፡ ወደ አንተ እቅፍም ትመለሳለች>. . . . . .

እንደተባለውም ሆነ ፡ወጣቱ የክፉው ቅመማ ገፈት ቀማሽ ሆነ።ንግስቲቱ ኩምሽሽ ብሎ የተቀመጠውን አስጠሊታ ወጣት ስታይ< አሁን ጨርሶ ተሸሎኛል አክሊሌን ደፍታችሁ ከንጉስ አልጋ ላይ አስተኙኝ> አለች። . . . . . ንጉሱ ንጉሱ ግን በጠዋቱ የቱርክን ምድር ለቆ ኮበለለ ለጠቢቡ የጻፈው መልዕክት ተከታዩን ይመስላል <እኔ የጠፊዋ ዐለም ምርኮኛ ነበርኩ።አንተ የነጻነቴ አባት. . . .ተምሬአለሁ! ከአሁን በኋላ ስለምን ግዜያዊ ውበትን ላሳድድ!? ስለምንስ ከተሰባሪ ወንበር ላይ ቁጭ ብዬ ልዘዝ!? ወጥቼአለሁ ኮብልያለሁ ያንን ውበቱ የማይከስመውን ፈጣሪ ውበት ፍለጋ!>. . . . . .ጠቢቡም የድሮውን ንጉስ የአሁን ኮብላዩን አገኛለው ብሎ ሲማሰን እንደወጣ ቀረ።>

አሏሁ አክበር. . .አሏሁ አክበር የደሳሳዋ ጎጆ ዝምታ ገነፈለ።ቢላል በፈገግታ እይታ ዙሪያውን ከዳሰሰ በኋላ አተኩሮ እያየኝ ፊቱን ከታች ወደላይ ነቀነቀልኝ <አዎ ይሄ ነው እውነተኛ ፍቅር> እያለኝ ነው። ያስሚን አሁንም ድረስ እወድሻለሁ።

ቤታችን እንደተረጋጋች ሁሉም ቦታ ቦታውን ያዘ።ከስግደት በኋላ ቢላል ምክሩን ከመጀመሩ አስቀድሜ ለመውጣት ፍቃድ ጠየቅሁት።እሺታውን ሲያሳየኝ ግዜ ሳላጠፋ የያስሚንን አይኖች እየናፈቅሁ ወጣሁ። ከንጉሱ ታሪክ በኋላ ልቤን ጠፍንጎ የያዘኝ ጭንቀት እንዳለ ይሰማኛል።ቢሆንም ጃስሚንን ከሚያሳጣኝ ነገር ጭንቀትን እንደምመርጥ እራሱ ልቤ ያውቀዋል።

ያስሚን ቀድማኝ ነበር የመጣችው። <<ሰላም አለይኪ እዚህ ቤት>> አልኳት የበረዳቸውን እጆቿን በትንፋሿ እየሞቀች እየፈተለች ሳለ። <ወአለይክ ሰላም> ካሁኑ ልታኮርፍ ትመስላለች < አንተ አርፋጅ እስካሁን ተበሳጭተሃል እንዴ> አለችኝ አጠገቧ እንድቀመጥ እየተጠጋችልኝ። መልሴን አልጠበቀችም << ደሞ ምነው እዚህ ቤት አልክ ውጪ አይደለን እንዴ?> >

ይህንን ጥያቄ ከዚህ ቀደም እራሴ ጠይቂኣት ነበር። ያስሚን ውስጥ ሃዘንተኛዋን ፈርሃን አያታለሁ። ያስሚን አይኖች ውስጥ ውብ የጃስሚን ሜዳዎች ይታዩኛል። ፈገግታዋ እንደሃገሯ ደረቅ ንፋስ ያንገዳግዳል። እጇ. . . . . <<እንኳን ቢቃ ተሳስቼ ነው> > ብዬአት እጆቿን ወስጄባት ከደረቴ አስጠጋኋቸው። አይኗን ማየት ግን አልቻልኩም።ዞር ብዬ ነበር የተቀመጥኩት።. .ተደግፋኝ እንደተቀመጥን በሰዐት የማይተመኑ ዘመናቶች ያለፉ መሰለኝ።ብርዱ እየበረታ ነው. . . .ምንጮች ሲንቆረቆሩ፡ የተራራው ሥር አውሬዎች በድቅድቁ ጽልመት ሥር እየቦረቁ እንደሆነ ያስታውቃል. . . . ጃስሚን ዝምታውን አሸነፈች <<ሐሰኒ ከአሁን በኋላ እንዳትጨነቅ እሺ ሁሉም ነገር ይስተካከላል። ደሞ ይህንን ሳምንት ከእማ ጋር ዘመድ ቤት ስልምንቆይ ስመጣ ነው የምንገናኘው ።>>

<<እሺ ግን እንዳትቆዪ አሏህ በሰላም ይመልሳችሁ።>>

<<ቆይ ቆይ አልናፍቅህም እንዴ>> ወደ ፊቴ በጣም ተጠግታ ቁልጭልጭ እያለች ነበር። ከቀይ ሂጃቧ ሥር አምልጣ የወጣች ቁንጥር ጸጉር በምሽቱ ንፋስ ስትወዛወዝ <አስገቢያት> ብዬ ጠቆም አደረግኋት። <<እ ንገረኛ ወይስ አልናፍቅህም>>

ሰዎች ለምን ልባቸው አስረግጦ የሚያውቀውን እውነታ በጆሮአቸው ለመስማት ይናፍቃሉ? ስል አሰብኩ

<< ትናፍቂኛለሽ ጃስሚናህ። ባትመለሺ የሚገለኝ አይነት ናፍቆት>> ድምፄን ለምን ለዘብ እንዳረኩት እንጃ።

ስታፍር ያልተበላሸውን ሂጃቧን መነካካት ትወዳለች።አንደኛው እጇ በጭብጠ ሥር እንዳለ የፍርሃት ውሃ ያመነጫል. . . .በዛ ቀዝቃዛ ምሽት።

<<ለምንድነው ግን እንደዚህ የምናፍቅህ>>

. . . . . .ይህንን ጥያቄ አልመለስኩላትም ነበር። የጎጆዋን በር መከፈት ስንሰማ ተያይዘን ከሚኮራኮረው ሜዳ እየሳቅን ገባን. . . .ያን ምሽት እርሷ የማታውቀውን ውበቷን ከሰፊው ዛፍ ሥር ሆነን አስረዳኋት።ሁሌም አጠገቧ እንደምሆን ምዬ ነገርኳት። የማውቃቸውን የፋርሲ ግጥሞች ሁላ ሰደርኩላት. . . ከሩቁ ከሚታዩ የተራራው ሥር ምሽቱ የሰራቸው አስፈሪ ትዕይንቶች ከዛፍ ቅርጾች እስከ ደመናው ከፍታ እየጠቆምኩ አሳየኋት።ያላሳየኋት የልቤ ግዛት ላይ የሰፈረውን የፍቅሯን ዘማች ብቻ ነበር።

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

🌹ክፍል ②⑤ ይቀጥላል.....彡★

❦የኮንያ አበቦች ክፍል 25

✍ Aymeni

ማን ነበር ሲገርፈኝ የናፍቆት አለንጋ
ትዝታው ሲጠብሰኝ ጎኔን ሚያረጋ

. . . ከሩቁ ከሚታዩ የተራራው ሥር ምሽቱ የሰራቸው አስፈሪ ትዕይንቶች ከዛፍ ቅርጾች እስከ ደመናው ከፍታ እየጠቆምኩ አሳየኋት።ያላሳየኋት የልቤ ግዛት ላይ የሰፈረውን የፍቅሯን ዘማች ብቻ ነበር።

ያስሚን <ስለምንም እንዳታስብ> ካለችኝ በኋላ ቀለል ብሎኛል።ያንን አይረሴ ምሽት ከምዕናቤ በቀላሉ ላባርረው አልቻልኩም። ልሂድ በቃ ብላኝ ከሳራማው ሜዳ ላይ እግሮቿን ከነከረችበት ሰዐት አንስቶ ናፍቃኛለች።

ከቢላል ጋር ቁርሳችንን ከበላን በኋላ ወደ ሻህ ሱፍያን ቤት ቀድሜ ወጣሁ። የጣውላው ቤት ያለእመቤቲቱ የሙት ጓዳ መስሏል። ስለ እርሻው እና አንዳንድ ንብረቶች ከጠያየቁኝ በኋላ <<ሐሰን ሂድ እስኪ ካባዬን አምጣልኝ ዛሬን ጫካ ውስጥ ብናሳልፍ ምን ይመስልሃል>> አሉኝ ወደ ትዕዛዝ በሚያጋድል አወራር። <<እሺ እሺ ሻህ እንደፍላጎትዎ>> ብዬ ካባው ወደተሰቀለበት ከፍል ደረጃውን ተሳፈርኩ። በእንጨት መስቀያ ላይ የሚታየው የአደን ካባ ከከፍሉ ጥግ ላይ ብቻውን ተንጠልጥሏል። በአበባ ስዕሎች ያሸበረቀው አልጋ ጥግ ላይ ያስሚን የለችም። ንግስቷ የረሳችው አልቃሻ ግዛት ይመስላል።

ከፍሉ ላይ ሳፈጥ ጃስሚን ከሰማይ ዱብ የምትልልኝ ይመስል ለሙሉ ደቂቃ ያህል ቆየሁ።ለራሴ<አሏህ በሰላም ይመልስሽ> እይልኩኝ የተላኩበትን ይገፎ ከፍሉን ለቅቄ ወጣሁ። አኩርፌአለሁ፡ኩርጊያዬን ያስሚን እንደማታይልኝ ባውቅም.....ሻህ ሱፍያን 2 ፈረሶች እንዲዘጋጁላቸው አዘዙ...ጎን ለጎን እያወጋን በባዝራ ሶምሶማ ከአደን መንደር ደረስን። የዛሬ ወሬያቸው ይለያል
<<ሐሰን ከናንተ ጎጆ ምድብ ውስጥ ቢላል የተባለ ጎበዝ ይገኛል አይደል።አለቃችሁን ማለቴ ነው።እርሱ ከተሾመ በኋላ የሰራተኞች ስብዕና አመጽ የሚባል ነገር ቅንጣት አልታየበትም።>> ታዲያ ለምን ቢላልን ይወስዱብኛል? ስል አሰብኩ
<<ከቢላል ጋር ትግባባላችሁ እንዴ?>>
ጥያቄው ወሽመጥ ቆራጭ ነው። <<አው ሻህ ከማንም ይልቅ ከእኔ ጋር ይቀራረባል>>
<<ያ ቨለድ ሊሰናበታችሁ እንደሆነ አውቀሃል ማለት ነው> >
ጭንቅላቴን ነቅነቅ አድርጌ በዝምታ አንገቴን ደፋሁ።
<<ለምን መሰለህ ሐሰን ።አሚራችሁ የጎጆውን ቤት የሚመጥን ሰው እንዳልሆነ ሺምር ነግሮኛል።ያንን የመሰለ ሰዎችን የማሳመን እና በልቦቻቸው የመጫወት ተሰጥኦ በዛች ደሳሳ ጎጆ ስር መዳፈን አይገባውም። ወደ ግዙፉ የሩዝ ማሳ እና የእንጨት ማከማቻ ላዘዋውረው ነው ያሰብኩት>>..... ጥቂቶች አዳኞች ናቸው። ይህች ዐለም ታዳኞች ይበዙባታል። ደካሞች እና የመሰከነ ልብ ባለቤቶች ሲታደኑ ይኖራሉ።

<<ልክ ኖት ቢላል እኛን አይመጥንም> >አልኳቸው በአስመሳይ ፈገግታ ተቀብቼ።ያ ጎንባሳ ሰፊ ትከሻ ፊቴ ከነ በሻሻው ፈገግታ ፊቴ ላይ ድቅን እያለብኝ።

❦
ምሽቱን በጎጆአችን ሥር ቀለበት መስርተን እየተጨዋወትን የሌሊቱ አጋማሽ ላይ ደረስን። ቢላል ሊሰናበተን እንደሆነ ያወቁ ጓዶች የኮሰሰ ፊታቸው በ2ቱ ደካማ ፋኖሶች ብርሃን ሥር ይታይ ነበር።ዋ እናንት ፋኖሶች ስንቱን ጎበዝ ሸኝታችሁ ይሆን? የስንቱንስ እንባ ታዝባችኋል.....አንድ ቀን አንድ ቀን እናንተንም ይነጣጥሏችኋል!

<<ሐሰኔ ትላንት በህልሜ አንድ ነጭ የወረደ ጺም ያላቸው ሸይኽ ሲያቅፉህ አየውህኮ። >>
<< ያለ እድሜዬ በጭንቀት ልጃጅ ነው ማለት ነዋ? >> አልኩት የመኝታ ቦታችንን እያስተካከልሁ።
<<ትቀልዳለሃ የምሬን ነው ባክህ። ምንኛ ያማረ ህልም መሰለህ!>> ቢላል ከሄደ በኋላ እንደምናፍቀው ያስታውቅበታል። አይን አይኔን ያየኛል።
የህልሙን ፍቺ ለማወቅ እየጓጓሁ <<እሺ ትርጉሙን ንገረኛ> >ብዬ ከፊት ለፊቱ ቁጢጥ አልኩ።

<< ህልም ለሰዎች አይነገርም።ምቀኛዎችህ በውስጣቸው ያንኑ ይመኙብሃልና።ሕልም እንደፈታከው ነው ይባል የለ።ጥሩ ህልም ደግሞ የፈጣሪ መልዕክት ነውና ለሰዎች አስፈትተህ አታርክሰው። የአሏህን ውሳኔ በሁለት እጆችህ አቅፈህ ለመቀበል ዝግጁ ሁን።ምስጋናም ከምላስህ አትለይህ። >>

ወሬውን ወደ ምክር ሲቀይረው የንግግር ጥበቡ ልሳኑ ላይ ይታያል። <<ሐሰን ባይሆን አንድን ልትረሳው የማይገባ ከመልዕክተኛው •ሶላት እና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን • የተቀዳ የፈጣሪ ቃል ላስታውስህ.....

<<እሺ ቢላሌ በደስታ>>....

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

🌹ክፍል 26 ይቀጥላል.....

★彡❣የኮንያ አበቦች ክፍል ②⑥

@Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ

ወሬውን ወደ ምክር ሲቀይረው የአወራር ጥበቡ አነጋገሩ ላይ ይታያል። <<ሐሰን ባይሆን አንድን ልትረሳው የማይገባ ከመልዕክተኛው •ሶላት እና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን • የተቀዳ የፈጣሪ ቃል ላስታውስህ።

የልቅዕናው ባለቤት አሏህ እንዲህ ይላል °° አንተ ባርያዬ ! ይህችን ዐለም ለኔ ውዴታ ብለህ የተውካት እንደሆነ በርሷ ውስጥ ያለውን ሁላ ለአንተ አጎብዳጅ አደርግልሃለው! ዱንያም ከእግሮችህ ሥር ትንፏቀቃለች። ግና ይህችን ዐለም በእኔ ውዴታ የቀይርክ ከሆንክ ዱንያን ለማግኘት ምንም ያክል ብትለፋ እኔ ከፃፍኩልህ በቀር የዳቦ ፍርፋሪንም አታገኝም!°°

ሐሰኔ ይህች ዐለም እጅጉን አስመሳይ ናት። የምታሳይህ የሌላትን ያክል ነው። ለዚህም ነው ከእለታት አንድ ቀን መልዕክተኛው •ሶለኋሁ አለይሂ ወሰለም• ለባልደረባዎቻቸው የዱንያን ኢምንትነት ሲያሳዩ ጣታቸውን ውሃ ላይ ከነከሩ በኋላ ተከታዩን የነገሯቸው °°ዱንያ ማለት ልክ ጣቴን ከውሃው ካወጣሁ በኋላ እንደምትንጠባጠበው እንጥፍጣፊ ውሃ ናት°°

የሐሰን ምክር ሲበረታብኝ ውስጤ ቀስ በቀስ መረበሽ ከጀመረ ሰነባብቻለሁ።የልቤን መዝገብ ገላልጦ እያየብኝ ያህል ይመስለኛል። <<ያስሚንህን ከህይወትህ ላይ ፍቀህ አውጣት> > ብሎ ማንኳረቅ ብቻ ነው የቀረው፡ባያውቃትም።

<<ሐሰኔ ነቢዩሏህ ኢሳ(እየሱስ) አለይሂ ሰላም ለሃዋርያዎቻቸው ያሏቸውን ታውቃለህ?>>

ከእርሳቸው በኩል የተሰሙ ምክሮች ከዚህ በፊት ሰምቼ ስለማላውቅ በጉጉት <<ንገረኝ እንጂ ምን አውቄ>> አልኩት።

<< ይላሉ።ዱንያን በጃጆች አሮጊት ተመስላ አየኋት። ጠየቅኋትም <ወዳጆችሽን ምን አደረግሻቸው?> መለሰችልኝ °°ቀተልቱሁም ቢኢሽቂ°° በፍቅሬ ገደልኳቸው>> ሐሰን ይህንን እንደተናገረ ፈገግ ብሎ አየኝ።ካሁን በኋላ ስለ ዱንያ አላወራብህም አይነት አስተያየት።

ቢላል ከኛ ጋር የሚቆየው እስከ ሳምንቱ መውጪያ ብቻ ነው።አሁን ከሱ ሥር ስሆን በተራራ ወገብ ላይ የታዘለች ጠጠር እንደሆንኩ ይሰማኛል።ቢሆንም የሱን እቅፍ እወደዋለሁ። የጎጆው ሰዎች የቢላል ልጆች እንጂ ሌላ አይመስሉም።በእድሜያቸው ጠና ያሉ ጎልማሶች ሳይቀሩ ይንሰፈሰፉሉታል። የህላዌ ጎዳናን የዘረጋላቸው፡ምሉዕ የደስታን ድግስ ያበላቸው ጀግናቸው አድርገው ይስሉታል።

የነሻህ ሱፍያንን ቤት ተከርችሞ ስላገኘሁት ደስ እያለኝ ወደነቢላል የስራ ቦታ አመራሁ።ቢላል ጥሎኝ ሲሄድ ያስሚን እንደምትመጣልኝ እያሰብኩ እራሴን አጽናናሁ።ያስሚን ከእመት አሚናህ ጋር ከመሄዷ በፊት የነበረውን ምሽት አሰብኩት.....ስትሰናበተኝ ቡኒ አይኖቿ እንባ አቅርረው ነበር.....<<እንዴ ጃስሚኔ ተመልሰሽ የማትመጪ አስመሰልሽው እኮ>> ስላት በስስ አይኖች እያየችኝ መለሰችልኝ ...ድምጿ ላይ ፍርሃት ያንጥብብ ነበር

<<እወድሃለውኮ ሐሰኒ>>.... ዝምታ ነበር የመለስኩላት። <<ቻው ሰላም አልይኪ ጃስሚኔ ቀዩላ አበባዬ>>....

ከአቃጣዩላ ጸሃይ ሥር የያስሚንን እንቡጥ ፊት በምእናቤ እየሳልኩ በደመነፍስ ከእርሻው ቦታ ደረስኩ።ቢላል ቀድሞ አይቶኝ ስለነበር የያዘውን አስቀምጦ ላቡን እያንጣፈፈ ወደኔ መጣ። << ሰላም አለይክ አንበሳው ምነው ያለ ሰዐትህ መጣህ> >
<<ወአለይከ ሰላም ። ሻህ ሱፍያን ቤቱን ዘግተው የት እንደሄዱ እንጃ>>
<< ያላንተ ጉዳያቸውን ማስጨረስ ለምደው ይሆናላ!>> አለኝ ምላሼን በጉጉት እየጠበቀ
<<ኸረ ባክህ ድሮውንስ! በል አሁን ቀልድህን ትተህ አንድ ሥራ ስጠኝ>>.....እኩለ ቀን ድረስ እየተሳሳቅን ስንሰራ ዋልን።
❦
ቀኑ ደስ ይላል።ከአንዲት የደረቀች ቅጠል አልባ ዛፍ ሥር ቢላል አንጠልጥሎ የመጣቸውን የሙዝ ዘለላዎች አንድ በአንድ እየላጥን ከስንብት ወሬዎች ጋር አጣጣምናቸው።አጠገቤ ያለው ሰው ጥላዬ እስኪመስለኝ ድረስ ተላምጄው ነበር። ከአመታት በፊት ጥዬው የመጣኋቸውን ጥሩ ነገሮች ሁላ ቢላል ልብ ውስጥ ይታዩኛል። ኢራን ምድር ላይ ጨክኜባቸው የነበሩ ውብ ነገሮች ደግሞ በሻህ ሱፍያን ብቸኛዋ ልጅ አይኖች ሥር ሆነው ያሳሱኛል።ሂልዋ....ያስሚን....ፈርሃን. ..ያስሚን... ② ደብዛቸው የጠፉ እናትና አባት...ሷሂብ ኡመር የሜዳው አንበሳ።

ቅጠል አልባዎቹ ቅርንጫፎች በመሬቱ ላይ ጥላቸውን ሲያሳርፉ ብዙ እጆች ያሉት ጥቁር አውሬ ይመስሉ ነበር።ለቢላል ሳሳየው ውብ ፈገግታን እያሳየኝ ጸጉሬን ደባበሰኝ <<ንጹህ ነህ።ልክ እንደ ወለላ....አሏህ ከፍ ያለን ቦታ አዘጋጅቶልሃና ልብህን አጠንክራት።ንጹህ ልቦች የፈተና ቋት መሆናቸውንም አትዘንጋ>> ።

በጎን ለመጣጣል ሜዳው ላይ ስንላፋ የእርሻው ጓዶቻችን በድካም መንፈስ ከፈገግታ ጋር እያዩን ነበር..... ቢላሌ ወንድሜ።

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

❣ክፍል ②⑦ ይቀጥላል.....⸗★

★⸗❣የኮንያ አበቦች ክፍል ②⑦

Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ

ቅጠላ አልባዎቹ ቅርንጫፎች በመሬቱ ላይ ጥላቸውን ሲያሳርፉ ብዙ እጆች ያሉት ጥቁር አውሬ ይመስሉ ነበር።ለቢላል ሳሳየው ውብ ፈገግታን እያሳየኝ ጸጉሬን ደባበሰኝ <<ንጹህ ነህ።ልክ እንደ ወለላ....አሏህ ከፍ ያለን ቦታ አዘጋጅቶልሃና ልብህን አጠንክራት>> ።

ሳምንቷ ጸዳልማ ነበረች።በአንድ ጎን ደግሞ የያስሚንን ናፍቆት ማከማቻ ስልቻ። በሻህ ሱፍያን ፍቃድ ቢላል እስኪሰናበተን ድረስ አብሬው እንድውል ሆነ።አብዛኛውን ግዜ የሰማይ ስባሪ በሚያህለው በዛፎች በተከበበ፡ በዛ የኮንያ ተራራዎች ከላዩ ላይ ተደቅነውበት ከሚታየው ሜዳ ላይ እናሳልፋለን። እስከ ጀምበር ጥልቀት ሥራ እና የዛፍ ስር ወሬዎች ይከታተላሉ። ጨረቃ ምሽቱ ላይ ስትነግስ አረፍ ባልንበት የፍቅር እንጀራ እንቋረሳለን።

የቢላል አንደበት ልክ እንደማር ብርዝ ይጣፍጣል።ዝም ሲል ዝምታው ያወራል።ሲናገር የሚያፈሰው ጥበብ ሌላውን ዝም ያስብላል። በአንዱ የጁመዐ ምሽት ላይ ጠየቅሁት።
<<ቢላል ግን ይኸውላ ነገር የምታውቀው መቼ እያነበብክ ነው::ንገረኝ እስኪ የተወለድከው መጻህፍት ቤት ውስጥ ነው እንዴ?>>

የቢላል ፊት ቀኗ ሲጠቁርባት አስተዋልኩ።ደንገጥ ብዬ <<ማይሆን ነገር ተናገርኩ መሰለኝ ቢላሌ በአሏህ ይቅርታ...>>
<<ምንም አላደረግህም።የውልደቴ ትዝታ ሲታወሰኝ የእናቴ ስቃይ ስለማይረሳኝ ነው>> ከጎጆዋ ጥግ ላይ ፊቱን ጎንበስ አድርጎ ነበር የሚያወራኝ።
ፊራ ተባ እያልኩ ጠየቅሁት << እ እሺ በቃ ግን ስለእናትህ ልትነግረኝ ትችላለክ?>>

ቢላልን ተስፋ የቆረጠች ፈገግታ ሲያሳየኝ አላስታውሰውም።ከዚያች ቀን በቀር።
<<ምን ልነግርህ ትፊልጋለህ ሐሰኔ። በልጅነት ያጣኋት እናቴን ሀዘን ከሚነበብበት ጎስቋላ ፊቷ እና እንደ ሳር ጎጆ ከሚሞቀው እቅፏ ውጪ የማስታውሰው ነገር የለኝም። ገና በልጅነቴ ነበር ከእናቴ የነጠሉኝ።>>

ከአፍታ ዝምታዎች በኋላ ለመናገር ደፈርኩ።<<ለሁሉም ነገር አሏህ ያውቃል። ቢላል አንተ ማለት እኮ ምን ልበልህ በቃ ብዙ ነገሬ ነህ>>
ባለበት ሆኖ ሊያቅፈኝ እጆቹን እየዘረጋ ወደኔ ዘንበል አለ።እንባ በተናነቀው ድምጸት ጆሮው ስር ስሞታዬን አሰማሁ
<<አንተ ስታዝን ማየት ያማል ቢላሌ።ያንተ እንባ ሲፈስ የጎጆአችን ምሶሶዎች ይነቃነቃሉ...>>
<<ኡሸሸ ሀሰን ።ስለሁሉም ይቅርታ.....አሁን ዝምብለህ አቅፈኝ>> ።
❦

ከሰዐታት በኋላ እራሳችንን በጀርባችን ጋደም ብለን ጣሪያ ጣሪያውን እያየን ስናወራ ነበር ያገኘነው።
<<ሐሰኔ አንድ ኢማሙ ማሊክ የተባሉ ታላቅ የሐዲስ ሊቅ ምን ይላሉ መሰለህ።አሏህ ይውደዳቸውና።°° እውቀት ማለት የዘገባ ብዛት አይደለም።እውቀት ብርሃን ናት አሏህ በሻው ሰው ልብ ላይ የሚያስቀምጣት ብርሃን°°>>

<<እና ደሞ ሐሰኔ ደካማዎች የጉልበተኞች፡ ድሃዎች የባለጸጋዎች መስታወት እንደሆኑ እወቅ።ምንዱባኖች ባይኖሩ ሐብታም ለማን ይለግሳል? ሐብት እንዳለውስ በምን ያውቃል?። ጉልበትህን የምታውቀው አንድን ደካማ ስታሸንፍ ብቻ ነው። ደካማው ያንተ መገኘት ምስጢር ነው።ስለሆነም በተሰጠህ ችሮታ አመስግን እንጂ አትመጻደቅ።
በነቢዩሏህ ዩሱፍ ዐለይሂ ሰላም ግዜ ነው።አንድ ከሩቅ ሐገር የመጣ ወዳጃቸው ከረጅም ግዜ መነፋፈቅ በኋላ ያገኙታል።ከግብጽ ምድር ወዲያ ያመጣላቸውን ስጦታ ከተጠቀለለበት ውስጥ አውጥቶ ያቀብላቸዋል። ስጦታው መስታወት ነበር። ውብ ፊታቸውን የሚያሳያቸው መስታወት ።

አስተውል ሐሰኔ።መስታወት ፊትህን ሊያሳይህ ይችላል።እውነተኛ ጓደኛ ግን ውስጠ ማንነትህን ያንጸባርቃል።መጥፎ ማንነቶችህን ይፍቅልሃል።ጓደኛ ህይወት ነው፡ተመን የሌለው የፈጣሪ ስጦታ።>>

ለሰዐታት ጋደም ብለን ካወራን በኋላ በየትኛው ሰዐት ላይ እንቅልፍ እንደወሰደን አላስታውስም።
ያንን ሌሊት ያየሁትን ህልም ለቢላሌ አልነገርኩትም።ያስሚን ተውባ ተሞሽራ ከፊት ለፊቴ ቆማለች።ያዘነች ትመስላለች። <ዛሬ በጣም ነው የምታምሪው> ልላት ብዬ እግሮቼን ለእርምጃ ሳሰናዳ ከኋላዬ የጨበጠኝ እጅ እንዳለ አስተዋልኩ.....ዞር ስል ያየሁት አንድን ከወተት የነጣ ዝርግፍ ጺም ያለው ሽማግሌ ነበር። <እንኳን ደህና መጣህ ልጄ> ብሎ የባባን ድምጽ በሚመስል አባታዊ ቅላፄ ሲናገር ከእንቅልፌ ነቃሁ።

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

❣ክፍል ②⑧ ይቀጥላል.....⸗★

★⸗❦የኮንያ አበቦች ክፍል 28

✍ Aymeni

....ዞር ስል ያየሁት አንድን ከወተት የነጣ ጺም ያለው ሽማግሌ ነበር። <እንኳን ደህና መጣህ ልጄ> ብሎ የባባን ድምጽ በሚመስል አባታዊ ቅላፄ ሲናገር ከእንቅልፌ ነቃሁ።

ቢላል ቀድሞኝ ተነስቶ መዝከሪያውን ይፈትላል።ጭለማው በከፊሉ ተገፎ ስስ የጀምበር ብርሃን በመስኮት በኩል እየገባ ነው።
<<ሐሰኔ ቶሎ በል ስገድና ወጣ እንበል። እስከ ቁርስ ድረስ ዞር ዞር እንበል እስኪ >>
<<በመቼው ነጋ ባክህ ።እሺ ልተጣጠብ እንቅልፍ አልጨረስኩም>> አልኩት አይኖቼን እያሸሁ። የለመዳትን ኪታብ ከፍቶ በሌላኛው እጁ ሙስበሃውን እየፈተለ ያነባል።

ስግደቴን ከጨረስኩ በኋላ ከሩቁ ቁጭ እንዳልኩ በአይኔ <እንውጣ> ምልክት ሳሳየው ኪታቡን አስቀምጦ ብድግ አለ።የነጀዋን በር ገመድ አላቀን ኩቴ አጥፍተን ወጣን።ከወፎች ዝማሬ ውጪ ዐለም ጸጥ ረጭ ብላለች። ያኔ ወደዚህ ቦታ ያመጣኝ ሺምር ከበሩ ጥግ ላይ ቁጭ ብሎ ትምባሆውን ያቦናል።ከዐመታት በፊት በጋሪዋ ሥር የተናገራቸው የስላቅ ንግግሮቹ ጆሮዬ ላይ አቃጨሉ <አታስብ ወደ ትምህርት ቤት ነው የምንወስድህ...ሃ ሃ ሃ>።

<<እናንተ ወዴት ነው ምትሄዱት> >ብሎ አተኩሮ ካየን በኋላ <<ኦ ቢላል ነህ እንዴ ምነው በሰላም?>> ብሎ ፊቱን ለማፈግግ ሞከረ።
<<አዎ ትንሽ አየር እንውሰድ ብለን ነው አለቃ>>
<<ይቻላል። አጠገብህ ያለው ልጅ አዲስ አልሆነብኝም. ...የት ነው በናትህ ማውቀው. ...>> አይኑ በጠዋቱ የቲማቲም ፍልቃቂ ይመስላል <<ኦ ኦ የፋርሱ ህፃን ሱብሃናላህ እንዴት ነው ያደገው ባክህ>> ....ለደቂቃዎች ካዳረቀን በኋላ ዋናውን በር ትተን በጓሮ መሄጃው በኩል አመራን።በስተምዕራብ ሰማዩኣ ጠቋቁራ በግግር ዳመናዎች ተከባለች። ከኋላችን ያለው ዐለም ጸሃይ ወጥቶለት የሚቦርቅ ይመስላል ።ህይወት ህይወት ይሸታል።

ወደ ጫካው ለመግባት ሰፊውን ሜዳ ልናቋርጥ ስንል የጀስሜኔን ቦታ አጮልቄ አየኋት። የወዳደቁ ፕላስቲኮች እና የውሃ ቡሃቃዎች ይታያሉ።መሃላቸው ላይ ያስሚን ያለች ይመስል እንደመንጠራራት ብዬ አየሁ።ቢላል አላስተዋለኝም ።ተፈጥሮን ገምግሞ ፈጣሪውን እያወደሰ ይመስላል <<በሰማያት እና ምድር አፈጣጠር በቀን እና ሌሊት ትክክቶሽ ውስጥ ለአስተዋይ ልብ ባልተቤቶች ምልክት አለች>> የሚለውን አንቀጽ እየደጋገመ ይ በዝግታ ያነበንባል.....እኔ በተራራው ግዝፈት ይሁን በዛፎች ሁሽሁሽታ የምወዳትን ሴት እንቡጥ ፊት አስታውሳለሁ ።

ከያስሚን ጋር ተደብቀን የምንመጣበት ዛፍ በሜዳው እና ጥቅጥቁ ጫካ መሃል ብቻውን ቆሟል።ቢላል እዚህ ጋር ቁጭ እንበል ቢለኝ ብዬ እየተመኘሁ ምኞሬ ስሳይሰምር ቦታውን ርቀን ሄድን።ዛፉን በጸሃይ ብርሃን አይቼው አላውቅም።ግንዱ ከደሳሳዋ ቤታችን ምሶሶዎች ይወፍራል።ቅርንጫፎቹ ተያይዘው ቆልምም ብለዋል።
<<ዛሬ አታወራም መሰል ሐሰኔ>> አለኝ ሃሳቡን ወደ እኔ ለመሰብሰብ እየሞከረ።
<< እ ኸረ አወራለሁ አንተ ዝም አልከኝ እንጂ>>
<<እያት እያት ጥንቸሏን ገና እንዳየችን ፈረጠጠችኮ>> በእጁ እየጠቆመ አሳየኝ።
<<አሁን እኛ ምናችን ያስፈራል>> ስለው ሰፊ ፈገግታ እያከለ <<እኔ ጠቆር ስለምል ይሆናላ>> አለኝ።
<<ቀልድ አንተ።ሰው ሲጀመርም አስፈሪ ፍጡር ነው ባክህ።ምናልባት ከዚህ በፊት ጓደኛዋን ሻህ ሱፍያን ሲገሉባት አይታ ይሆናል የፈራችው>>ብዬ ፈገግታውን መለስኩለት።
<<ከርሳቸው ጋርማ የሆነ ያያያዘከ ነገር አለ።ትበረታባቸዋለህ>>
በልቤ < ልጃቸውን ከሰጡኝ ከነመፈጠራቸው እረሳቸዋለሁ> ብዬ ዝምታን መረጥኩ።ቢላልን በአንድ አጋጣሚ ያለኝን አልረሳውም <መልካም ሚስት የህይወት ማጣፈጫ ናት።የጉድለትህ ማሟያ።እሷን የሚያገኙት ግን ውበትን የዘነጉ የልብ ተመልካቾች ብቻ ናቸው>>

አ አላህ ያ ቀን ውብ ነበር።ከቢላል ጋር ጫካ ለጫካ እየተሳሳቅን ቁርስ አለፈብን።ለዐመታት ያየሁት ፈገግታ ያን ቀን ወደ ከትክት ሳቅ ሲቀየር አስተዋልኩት። ዳመና በሚነኩ ዛፎች ሥር ሰማዩን ተፋጠን ተኝተን፡ ከላይ እየተንሳፈፉ የሚወርዱትን ደረቅ ቅጠሎች በትንፋሻችን ለመግፋት እየሞከርን የራሳችን ጨዋታ ፈጠርን። <<ኡህ >ብዬ እየጮህኩ በምላሹ የጫካው ገደል ማሚቱ ድምጼን ሲያስተጋባ ቢላልን እያየሁት እስቃለሁ። እሱም ከልቡ እየሳቀ <<ኸረ ሐሰኔ ተው ጂኒዎቹን አትጥራብን>>ይለኛል።
ፈጠርን የራስን ጨዋታ...ፈጠርን የማይነጥፍ ትዝታ.....ልቤም ነገረችኝ....በቃ ይህ ነውኮ °የረመጥ ሥር ደስታ°።
❦
ሳምንቱ እንደብልጭታ ጥርሱን አሳይቶን አለፈና የማይቀረው ማለዳ ደረሰ።ቢላል በጠዋቱ ኪታብ እና ልብሶቹን በነጭ ጨርቅ ሸካክፎ ሊሰናበተን እየተዘጋጀ ነበር። በመጀመሪያ ቀን ከተዋወቅንባት ቦታ ላይ ያረጀቺን ብርድ ልብስ ተጠቅልዬ ቁጭ ብያለሁ።አገጩን በእጆቼ ላይ አስደግፌ ከጥግ ጀምሮ የጎጀውን ሰዎች ሰላም ሲል ቁልጭልጭ እያልኩ እያየሁት ነው..... ልቤ ትደልቃለች እንደኩብላዩ ንግስት።

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

❣ክፍል 29 ይቀጥላል. . . .彡★

★彡❣የኮንያ አበቦች ክፍል ②⑨
✍Ⓐⓨⓜⓔⓝⓘ

ሳምንቱ እንደብልጭታ ጥርሱን አሳይቶን አለፈና የማይቀረው ማለዳ ደረሰ።ቢላል በጠዋቱ ኪታብ እና ልብሶቹን በነጭ ጨርቅ ሸካክፎ ሊሰናበተን እየተዘጋጀ ነበር። በመጀመሪያ ቀን ከተዋወቅንባት ቦታ ላይ ያረጀቺን ብርድ ልብስ ተጠቅልዬ ቁጭ ብያለሁ።አገጩን በእጆቹ ላይ አስደግፌ ከጥግ ጀምሮ የነጀውን ሰዎች ሰላም ሲል ቁልጭልጭ እያልኩ እያየሁት ነው..... ልቤ ትደልቃለች እንደኩብላዩ ንጉስ ንግስት።

ፊቱ ደብዘዝ ብሎ አይኖቹ ላይ የነበረው የተስፋ ብርሃን ጭላንጭሉ ይታያል።የነጀውን ሰዎች እያቀፈ እና ጠና ያሉትን እጃቸውን እየሳመ አንድ በአንድ ተሰናብቶ እኔ ግድም ደረሰ። ቁጢጥ እንዳልኩ በአይኖቹ ጣሪያ ሳየው 'እቀፈኝ እንጂ' የሚሉ ረጃጅም እጆቹን ዘረጋልኝ። ብርድ ልብሴን ወደኋላ አመናጭቄ እቅፉ ሥር ገባሁ።ጀርባዬን ሲያሻሸኝ ድሮ ድሮ ሂልዋ ከቱሀራን መድረሳ ስትመለስ የምትሰጠኝ ፍቅር ታወሰኝ።አንገቴን ስትስመኝ የናፍቆት እሾህ በረግረግ የፍቅር ቁጠማ የተቀየረ ይመስለኝ ነበር።

<<ሐሰኔ ጠንካራ ሆነህ እንደምትቆይ አልጠራጠርም።ከኔ በኋላ የነሱ አሚር አንተ ባትሆንም እንኳን የነጀው ሰዎች ሃላፊነት ካንተ ጫንቃ አይወርድም። አደራ አደራ የብልጭልጭ ዐለምን አታላይነት። በሷ ማዕበል መጠፍነግን ካልፈለግህ ስግደቶችህ ላይ ወደ ኋላ አትበል።ፈጣሪንም ከማስታወስ እንዳትቦዝን የርሱ ስም የሁለቱም ዐለም ዘብ ነውና። ውዱን መልዕክተኛም ሶላት እና ሰላም በእርሳቸውላይ ይሁንና ሁሌም ከልብህ ጓዳ አኑራቸው።ከምላስህም ስንዘራ ከልብህ ውሸባ አይጥፉ ብርሃናማው የፈጣሪ መንገድ መሆናቸውን አትርሳ>>

እጆቹን በትከሻዬ ላይ አድርጎ ነው የሚያወራኝ።በመጨረሻም አንድ እጁን እያወረደ <<ትናፍቀኛለህ ሐሰኔ >> ብሎ መሬት ያስቀመጠውን ጓዝ ዳግም ጠቀለለ <<ሰላም አለይክ>>።ቢላል በነን በኩሌ እንደ ሲፊን ንፋስ ሽው ብሎ ሲያልፍ እንባዎቼ ሳላስባቸው መንደርደር ጀመሩ።ትኩስ...ጉንጭ የሚያሳሱ እንባዎች። ጥሎኝ ወደ ሚሄደው ቢላል በደመነፍስ ዞሬ እሩጫ የመሰሉ እርምጃዎችን አስከተልኩ ።

ስጠራው የቆዳ ጫማውን አድርጎ ጀርባውን ሰጥቶኝ ወደ መውጪያው እያመራ ነበር።
<<እህ ቢላል >>።
ሙሉ አካሉን ወደኔ አዞረ።
<<እኔምኮ ትናፍቀኛለህ>> ዜማዬ የራሴን አንጀት ሲሰረስረው ዝምያለው እንባዬ ማቆሚያውን አጣ።አሁን ቢላልም አልቻለም።ከአይኑ ቀጠና ያሉትን እንባዎች ገና ሳይወጡ ቶሎ ቶሎ ይጠርጋቸዋል።

በዝግታ አጠገቤ ከደረሰ በኋላ አናቱ ላይ የጠመጠመውን አረንጓዴ አማኢማ አውልቆ ሰጠኝ።<<ይህንን ጨርቅ ባየከው ቁጥር አጠገብህ እንዳለው አስብ።ውዴታህን ከአይንህ ግዛት ወስደህ ልብህ ላይ አኑራት>>.....
ከደቂቃዎች በኋላ ከሻህ ሱፍያን ጋር ወደ ጣውላው ቤት ገብተው ቆይተው ጥቂት እንደተጋረዱ ቢላል ሲወጣ አየሁት።ከዚያም ከዛማ ፈጠን ፈጠን ባሉ እርምጃዎች ግዙፉን የመውጪያ በር ከፍቶ ከአይታዬ ተሰወረ።

ቱርክ ኮንያ ተራሮች ሥር

❣❣❣❣❣❣❣❣❣❣❣
የመጨመረሻውን ክፍል በአሏህ ፍቃድ ነገ አመሻሹ ላይ ይጠብቁን
❣❣❣❣❣❣❣❣❣❣彡★

★彡❦የኮንያ አበቦች ክፍል ③⓪

ሳላገኝህ በፊት ህይወተ-ደብዛዛ
ስትመጣ ሚቅላላው
ሚስጥሩ ምንድነው?

እለተ ጁመዐ።ከሌሊት ስግደት በኋላ እንቅልፍ አልወስድ ብሎኝ አይኖቼን የውሽት ጨፍኜ ማለቂያ በሌላቸው ሃሳቦች ተጠፍንጌያለሁ።የቢላልን ምክሮች የለመዱ ጆሮዎች በማለዳው ነቅተው፡አይኖች ያጡትን ማመን ተስኖአቸው ቦዘዋል።የጎጆው ቤት ልቦች ቢነቁም ልሳኖች ቃልት አጥተው እንደተለገሙ ያስታውቃሉ።እስከ ቁርስ ድረስ ለመተኛት እየተጣጣርኩ ነበር ገና በጠዋቱ የአበባዋ መዓዛ የተናፈሰብኝ።ያስሚን።

ዛሬ ላገኛት እንደሆነ ሳስበው ጭርፍራፊ የእንቅልፍ ጠብታዎች ሰውነቴን ጥለው ፈረጠጡ። ከራሴም ጋር አወራሁ <ጃስሚኔ አሁን አንቺ ውስጥ ቢላልንም አየዋለሁ።ለርሱ ያልነገርኩትን የውዴታ ጫፎች ለአንቺ አሰማሻለሁ።ላጣሽ አልፈልግም እወድሻለሁ>።

ያስሚንን ዛሬ እንደምወዳት እና የህይወት አጋሬ ልትሆን እንደምፈልግ ልነግራት አስቤ ቆርጬአለሁ።እርሷን ለማግኘት ምንም አይነት መሰዋእትነት መክፈል እንዳለብኝ ከስጋ እስከ ነፍስ አራሴን አሳምኜ ከተኛሁበት ተነሳሁ።ቢላል መጽሃፉን የሚያስቀምጥባትን ዝቅ ያለች አሮጌ የእንጨት መቀመጫ በቀኝ እጇ ደገፍ ብዬ ቁጭ አልኩ። ምናልባት ሻህ ሱፍያን ልጃቸውን አይሰጡኝ ይሆናል...እመት አሚናህም <ምነው ደፈርከኝሳ> ሊሉ ይችላሉ .....ህይወት በመላምት ብትመራ ኖሮ እኔ በአሁኗ ሰዐት ሲፈን ውስጥ እዚህ እዚያ የምል የኡሚ እና የባባ ጎረምሳ፡የታዋቂዋ ሂልዋ ወንድም ነበርኩ።ህይወት ግን ከእቅድ ይልቅ በተጻፈው ብርሃናዊ መዝገብ የምትመራ የሆድና ጀርባ ትዕይንቶች መድረክ ናት።

የወፎቹ ጫጫታ በርትቷል።የግቢው በሮች ሲከፈቱ እንደበሽተኛ ያቃስታሉ።የጎጆዋ ቤት ሰዎች ቀስ በቀስ ህይወት ሲዘራባቸው ፊታቸውን ለመታጠብ የሚወጡ እና እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚነቃቁ ፍጥረታትን ታዘብኩ።ሳህኖችን የሚያጥበው ሷሂብ በማዳበሪያ የተጠቀለሉትን እቃዎች ተሸክሞ ከክፍሉ ወጣ ።በዝግታ ድምጽ ያንጎራጉራል <<ሊሃከዛ ኹሊቅተ አው ላ...ፈኩን ቢስሚከ መሸኩራ.....ለዚህም ተፈጠርክ ለሌላ ..በስምህ ምስጉንነት ይጉላ>።

ለምን ያህል ሰዐት ቁጭ እንዳልኩ አላውቅም።የቁርስ ሰዐት እንዳለፈ ግን በጸሃዩአ ብርታት ያስታውቃል።ጎጆዋ ቀስ በቀስ ጢም ማለት እንፈጀመረች ሳህኖቹን አጣጥቦ የጨረሰው ሷሂብ <<ዛሬ በያላችሁበት ነው ቁርሳችሁን የምታጣጥሙት።ሺምር እዚህ ቤት ገብተው የማያውቁ ምግቦች ልንቀማምስ እንደሆነ ነግሮኛል>> ብሎን አጮልቆ ያስገባትን አንገት ወደ ውጪው መለሳት።

<< ሷሂብ ቢላል በሰላም ገብቶ ይሆን ልጇ>>። አውርቼው የማላውቀው ጎልመስ ያለ የተረጋጋ ሰው ነበር ነካ አድርጎ ያስደነገጠኝ።
<<እንጃ ወዴት አካባቢ እንደሚሄድ ለኔም አልነገረኝም>>
<<አሏህ በሰላም ይስገባው። አንተም ደብሮሃል መሰለኝ ልጇ ህይወትን ቀለል አድርገህ ያዛት። የአሏህ ካዝና ምሉዕ ነው ከችሮታው ለመቅዳት አትሰናፋ>> ብሎኝ መልሴን ሳይጠብቅ ፈገግታውን አስይዞኝ ከመጣበት ጥግ ተነስቶ ተመለሰ።

ጥቂት እንደቆየን ከቧ ጎጆ ከፊትለፊታችን በተደረደሩ ነጫጭ ባዶ ሳህኖች ተሞላች።ብዙም ሳንጓጓ ነበር ② የሺምር ሰራተኞች እንፋሎት የሚወጣቸው ትላልቅ የብረት ድስቶችን ይዘው ወደከፍሉ የዘለቁት። <<በደንብ ብሉ ዛሬ ሻሕ ሱፍያን ድፍን ኮንያን ቢያበሉ ደስታቸው ነው>> ብሎ ድስቱን ካስቀመጠ በኋላ አነስተኛ ጓድጓዳ ሳህን በሚያክል ጭልፋ ምግቡን መጨለፈ ያዘ.....

በያለንበት ሆነን የቻልነውን በላን።የማላውቃቸው የሚጎራርሱ እጆች እና የፈገግታ ጨረር የሚልኩ ፊቶች ይስተዋላሉ።ቢላሌ አጠገቤ ቢኖር ስለ ምግቡ አስተያየት እንሰጣጥ ነበር።የኢራን ሩዞች ከዚህ ይበልጥ ረጃጅም እና ጣት አስቆርጣሚ የመረቅ ማባያዎች እንዳላቸውም እነግረው ነበር፡ በየደቂቃው ከትኩሱ ስጋ ላይ ዘንጥዬ እያስጎረስኩት.....<<እቺን ጉረስ እስኪ>> የሚል ድምጽ ከቁም ህልሜ አነቃኝ። ቀደም ብሎ የመጣው ጎልማሳ ሰው ነበር።አሁን ግን ፍጹም ደስተኛ ወጣት ይመስላል።
❦

ከወደውጪው በኩል መለከት ሲነፋ እና አንባሮች ሲንኮሻኮሹ መሰማት ተጀመረ።ምክንያቱን ባላውቅም አንዳች ያላወቅሁት ዝግጅት እንዳለ ጠርጥሬአለሁ። እንደዚህ አይነት የፌሽታ ንፋስ ከነፈሰብኝ ቆይቻለሁ።የደስታ ስብስቦች ናፍቀውኛል። ትዕይንቱን ለመታደም ጥግ ላይ ባገኘሁት ውሃ እጄን ተጣጥቤ እየተቻኮልኩ ወደ መውጪያው አመራሁ።

የነሻህ ሱፍያን የጣውላ ቤት ስር የቆሙ ባለአባቶች ከዘራቸውን ይዘው እንደተኮፈሱ በአግድም ወንበር ላይ ተቀምጠዋል።ግቢው ውስጥ የሚገኙ የወዳደቁ ቅጠላ ቅጠሎችና የእንጨት ስብርባሪዎች ተነስተው ትኩስ ቀያይ ጽጌረዳዎች ተርከፍክፈዋል። መንፈስን የሚይያድስ መዐዛም ካልታወቀበት ሲነፍስ የወዳጅን ልብ ያናውዛል.....ጃስሚኔ በቶሎ ነይልኝ፡ የሙሀረም ንፋስ ያወረዳቸው የቱሊፕ ቡኒ ቅጠል አይኖችሽ ናፍቀውኛል፡ ከቤቱ ውስጥ የሚወጣውን እልልታ እየሰማሁ በዛሁ ቅጽበት ፍቅሬን ለያስሚን ብገልጽላት ተመኘሁ።

ከተበረገደው ግዙፍ የእንጨት በር በኩል አልፌ ውጪውን ስደርሰው ከሩቁ በኩል በዝግታ የሚመጣ ሰረገላ በአካባጅ ብናኝ አቧራዎች ተሸፍኖ ታየኝ።ከኋላዬ በኩል የሚመጣው የእልልታ እና የአንባር ኩሽኩሽታ በየመሃል በሚነፉ ጡሩምባዎች ደምቆ የእልልታው ሞገድ እየበረታ ነው። ከደቂቃዎች በኋላ ከኋላዋ በእመቤቶች እና ባለአባቶች የታጀበች መሬት በሚነካ ቀይ ቀሚስ የተሞሸረች ልዕልት ከጎን እና ጎኗ በሻህ ሱፍያን እና እመት አሚናህ ዘብ ተጎናፍራ መጣች። ጃስሚን! ኦ አሏህ ጃስሚን እዚህ ምን ትሰራለች? እኔን ከምድር ፈንቅላ የምታገኘኝ ይመስል አንገቷን ደፍታ አይኖቿን ከልክላኖለች።

ማንም የማያውቀው የማይዳሰስ መንፈስ የሆንኩ ያህል ተሰማኝ።እጃቸውን የሚያወዛውዙ እና አበቦችን ወደ ጃስሚን የሚወረውሩ እናቶች እየገፈታተሩኝ ከአጠገቤ ሲያልፉ፡ የማስተዋል አቅሜም ከወከባው ጋር ሲቀጭጭ ልቤ በፍርሃት ተናወጠ የማየውን ማመን አልቻልኩም።ያስሚን ዛሬን በፍቅሬ ጥላ ሥር ላኖርሽ፡የናፈቅሽውን ቃል ላሰማሽ እንደነበር አታውቂም እንዴ!

በወርቃማ ጌጣጌጦች ካሸበረቀው ሰረገላ ስትዘልቅ አጃቢዎቿ የማላውቀውን ቱርኪ ግጥም አዘነቡ። ሰረገላው ጥቂት ፈቀቅ እንዳለ በቀይ ከርዳዳ ጀለቢያ እና ጥምጣም የተዋበ ሰው ወደ እኔ መቅረብ ሲጀምር አስተዋልኩ <<ሐሰኔ በኢጋጣሚ አይቼክ ሰላም ሳልልህ አልሄድም ብዬ ነው። በጣም ብዙ የምነግርህ ነገር አለ። ሻህ ሱፍያንኮ በሄድኩበት መንደር ኮንያን የሚያክል የእርሻ ቦታ እና ተቆጥረው የማያልቁ ከብቶችን አበርክተውልኝ ጎጆ ቀለሱልኝ። እ እናደሞ ሙሽራ ሆኜልካለሁ... ደሞኮ ልጅቷን ገና አሁን ነው የማያት ....በል በቃ መጥቼ እጠይቅሃለው ብዙ የምናወራው ነገር አለ። ሙሽራዬ እየጠበቀችኝ ነው >> በእያንዳንዱ የቢላል መርዶ መገጣጠሚያዎቼ ተሸበረኩ። አንገቱን ወደኔ ኔ አዙሮ እየሄደ ነበር የምሚያወራው<<ሐሰኔ ያንን እኔ የማላውቀውን እሱን ለማገኘት በምሽት የምትወጣለትን ጓደኛህን ሰላም በልልኝ እሺ>> .....አይኔ እንደፈጠጠ የእንባ

ከረቲጦቹን የመፍታት ወኔ አጥሮት ደርቋል።

በደመነፍስ ከጎጆው ቤት ደርሼ በታፈነው ቤት መግቢያ ላይ በጉልበቴ ተደፋሁ። ያስሚን ጩኸቴን ብትሰማው ከሰረገላዋ ወርዳ በመጣችልኝ <<ንገሩኝ እስኪ ንገሩ ኝ ፍቅር ምንድነው። ህይወትስ ከየት ነው መዳረሻስ ይኖረው ይሆን?>> የብሶት ቃላቶቼን እንዳወጣሁ የሚለበልቡ እንባዎች ከፊቴ ገጽ ላይ ጎረፉ።እናቱን እንዳጣ ህጻን መሬቱ ላይ ተዘርግቼ ተንፈቀፈቅሁ።
በዛው ቅጽበት በማጣት የተደቆሰቺ ልቤ የጥያቄዬን መልስ አንግባ ሹክ አለችኝ።<<ፍቅርማ እራሱ ፍቅርን የፈጠረው ፈጣሪ ነው>>የጎጆው ሰዎች ሊያነሱኝ ይጣጣራሉ።ልቤም ታወራኖለች <<ህይወት መነሻዋ ፍቅር ...መድረሻዋም ፍቅር። ወደ አሏህ የምታደርስ ብሩክ ተዐምራዊ ታንኳ>>.....

❦
እራሴን ያወቅሁት ጎልማሳው ጓድ እና ሳህን አጣቢው ሷሂብ ቀዝቃዛ ውሃ ሲቸልሱብኝ ነበር።ከታች ወደ ላይ ሆኜ ብዝሃ ፊቶች ሲያፈጡብኝ ከአራስ ቤት የወጣ ህጻን እንደሆንኩ ገመትኩ።

ከ3ቀናት በኋላ.....

ያንን ባለነጭ ጺም የነፍስ አባቴ፡የህይወት መምህር ለማግኘት ጓዜን ጠቅልዬ ተነሳሁ።ቢላል የሰጠኝን አማኢማ ጠቅልዬአልሁ፡ምክሮቹንም ከልቤ አኑሬ። ከጎጆው ሰዎች ጋር አንድ በአንድ እንባ ተራጭተን ልሰናበታቸው የመውጪያውን በር ጨበጥሁ። ሷሂብ መዚሂር የተባለ የጎጆው ወጣት ከሻህ ሱፍያን የማጎርያ ግቢ ሊያስመልጠኝ በእገዛ መንፈስ ከጎኔ ቆሟል .....ይህ ሰው የጠባቂውን ሺምር አይኖች ሲከልልልኝ እግሮቼ የመውጪያውን መስመር ይዘው

ነበር ....ከሩቁ የእመት አሚናህ ድምጽ ይሰማ ነበር< <ሺምር ሂድ እስኪ ያንን የፋርስ ሸጋ ጥራው። ሻህ ሱፍያን እየጠሩህ ነው በለው....ያስሚኔ ከሄደችብን በኋላማ ላሱም እንደልጇ ይናፍቀኛል...አይ ሃሳኒ>>....

❦
በሩቅ መንገድ ላይ ከአመታት በፊት ወደ ኢራን ምድር የላኩትን የሂልዋ መልዕክተኛ አግኝቼው ነበር።
ሂልዋ 2 ልጆችን ወልዳለች...ሀሰን እና ፈርሃን
2ፈርሃኖች ግን አይኖሩም ሚስኪኗ ፈርሃን እራሷን አጥፍታለች...
እንደናፈቅኋት ነገረችኝ...ናፍቆት ምንድነው?

በምላሹ በጻፍኩላት ደብዳቤ ላይ የመጨረሻ ቃላቶቼ በድጋሚ ከእንባ ጋር የተጎዳኙ ነበሩ...እንዲህ ተብለው የሚነበቡ (وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أشد حُبّٗا لله. እነዚያ ያመኑትም አላህን በመውደድ ይበልጥ የበረቱ ናቸው።) የተባረከው አንቀጽ በበቀራህ ምዕራፍ ላይ እንደሚገኝ የነገረኝ ፈገግተኛው ቢላል ነበር። እርሱ ሕይወትን ሲሰጠኝ. ...እኔ ያስሚንን ሳያውቀው ሰጠሁት።

በእግረ መንገዴ ሷሂብ ኡመርን አግኝቼአቸው ነበር።ደክመዋል ....በቀሰስተኛ አነጋገር<አሏህ ካንተ ጋር ይሁን>ብለው ሸኙኝ። ከአመታት ኩብለላ በኋላም ጋራ ሸንተረሩን ሜዳ ኮረብታውን አልፌ ታላቁን የሱፊ መምህር በሰከነች ሚህራብ ሥር ሆነው ጸሎት ሲያደርሱ ያገኘኋቸው.....በምኩራቡ ግፍግዳዎች ላይ በውብ የአረብኛ ጽሁፍ ያሸበረቁ 99 የአሏህ ስሚች ይታያሉ <<ሰላም አለይኩም አባህ> >
.....<<እንኳን ደህና መጣህ ልጄ>>።

ተፈፀመ ዘንደኒ ሚግዛራ, ,ህይወት ግን ትቀጥላለች

✍አይመኒ ጁምዐ/ረቢዐል ዐወል/1447 ሒ